# የፍጹም ሰው ቁመና

እናመሰግናለን፡ ወንድም ኔቪል። ጌታ ይባርክህ።

ዛሬ ጠዋት ወደ ማደሪያው መመለሳችን ጥሩ ነው። ድንቅ የሆነ “ሰላምታዬ፡” ለሁላችሁ ይድረስ። በዛሬው ቀን—በጌታችን ፊት መገኘት፡ ታላቅ ቀን እንደሚያደርግልን እምናለሁ። ዛሬ ጠዋት ያዘጋጀሁት ትምህርት አለ። ትምህርቱ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ፡ በቀጥታ… ወደ ትምህርቱ እንገባለን። ምናልባት… እንደምታውቁት፡ ብዙዎች ከመቆማቸው የተነሳ፡ እንዳይበሳጩብን። በቀጥታ ወደ ትምህርቱ እገባለሁ።

2 ዛሬ ማታ፡ **የህይወቴ መሪ**፡ በሚል ርዕስ ላይ ለመስበክ ተዘጋጅቼአለሁ። በዛሬ ምሽት አገልግሎት፡ መገኘት የሚችሉ ሁሉ፡ እንደሚገኙ፡ ተስፋ አደርጋለሁ። የቤተ ክርስቲያናችሁ፡ አገልግሎት ካለባችሁ ግን፡ በቤተ—ክርስትያናችሁ ጉዳይ… እንድትገኙ፡ እንመክራለን። በተጠራችሁበት አገልግሎት ተገኝታችሁ፡ ብርሃናችሁ እንዲበራ ማድረግ፡ ግዴታችሁ ነውና።

3 እንደው፡ ተመልሳችሁ በመጣችሁ ቁጥር፡ መቀመጫ ስፊ ቦታዎችን ለማዘጋጀት፡ በተደጋጋሚ ተስፋ እናደርጋለን። ይሁን እንጂ፡ የባለ አደራዎች ቦርድ ያልቆፈሩት ሰፍራ የለም። ቦታ እየጠበበን፡በጣም ተቸግረናል። ወደ አንድ ቦታ ይልካሉ፡ እነርሱም ተቀብለው፡ ወደ ሌላ ቦታ ይልኩታል፡ ውድቅ ይሆንብናል። እና መልሰው **ወደዚህ** በላኩት ጊዜ፡ እንደገና፡ ተቀባይነት አግኝቶ ይመለሳል። አቤት፡ ያሳለፍነው ጊዜ! ሁሌም እንደምታውቁት፡ ሰይጣን፡ ሁልጊዜ እውነት የሆነውን ይዋጋል። ትክክል ስለሆናችሁት ነገር፡ ዘወትር አስታውሱ…

4 አንቶኒ የት ገባህ ብዬ ስለ አንተ እያሰብኩ ነበር። አባትህን ሰላም ሰትለው አይቻሃለሁ። በዚህ ጥግ በኩል ተቀምጧል፡ ብሎ ስለነገረኝ። በጉባኤው መካከል ፈለግኩህ። አንተን እና አባትህ ወንድም ሚላኖ ከኒውዮርክ፡ እንኳን ደህና መጣችሁ ሰንላችሁ ደስታ ይሰማናል። ጌታ ቢፈቅድ፡ በዚህ ጊዜ ወደ ሚሽን ሰወጣ፡ በኒው ዮርክ፡ እና በዙርያ ባሉ ቦታዎች፡ ሌላ የጸደይ-ወቅት እንደሚሆንልኝ፡ ተስፋ አደርጋለሁ።

5 እንዲሁም ሁላችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ። በመምጣታችሁ—እንዴት ደስ ይላል።

6 ትላንት ማታ ድንቅ ጊዜ አሳልፈናል፡ ቢያንስ ለእኔ ድንቅ ነበር። ተባርኬበታለሁ… [ጉባኤውም “አሜን፡” አለ።—እርታዒ።] “ኢሳያስም በቤተ መቅደሱ።” እናንተም እንግዲህ…

7 ዛሬ ማለዳ፡ ከቻልን፡ መናገር፡ ወይም ማስተማር፡ የምንፈልገው ርዕሳችን፡ “ህያው ማደርያውን መገንባት፡ የሕያው የእግዚአብሄር ህንጻ—ህያው ማደርያው ቤት የሆነው፡ ፍጹም ሰው መገንባት፡ ህያው እግዚአብሄር የሚያድርበት፡ ህያው ህንጻ መገንባት።” የሚል ይሆናል…

8 ጥሩ ጥሩ ዝማሬዎች እንዳለፉኝ አውቄዋለሁ። መድረስ አልቻልኩም። ምናልባት ማታ ላይ፡ ለመድረስ እሞክራለሁ። ከቴነሲ ሰለ መጣው ወንድም፡ ካልተሳሳትኩ—ስለ ወንድም እንግረን፡ ባለቤቴ ነግራኛለች። ትላንት ማታ፡

እዚህ ነበር። ዛሬ ጠዋት አላየሁትም፡ ጉባኤው ውስጥ ይኖራል ብዬ እሰባለሁ። ከተቻለኝ፡ ዛሬ ማታ፡ **ከላይ ከክብሩ፡** ወይም **እንዴት ድንቅ ነህ**፡ የሚሉ ዝማሬዎችን ሲዘምር ማየት እፈልጋለሁ። ብሰማው ደስ ይለኛል። ወንድም አንግረን ሲዘምር ማየት ሰንቶች ትፈልጋላችሁ? [ጉባኤውም "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ኦህ፡ መልካም ዝማሬዎችን—እወዳለሁ። ባሪቶን የሚባል መሳርያ መያዙንም ሚዳ ነግራኛለች። ወንድማችንን ባክስተርን ያስታውሰኛል፡ ሁላችንም እንደምናውቀው፡ እሱም፡ ዘማሪ ነው። እና **ከላይ ከክብሩ፡** ወይም **እንዴት ድንቅ ነህ**። ወንድም አንግረንን፡ እዛጋ፡ አየሁት መሰለኝ... ዛሬ ማታ፡ መቆየት ይመችሃል፡ ወንድም አንግረን፡ ፍቃድህ ከሆነ? ለማታው አገልግሎት ትቆያለህ፣ ወይስ ለመቆየት ትሞክራለህ? እሺ፡ እ—እ... እሺ፡ ችግር የለውም... ልንገርህ፡ እንዲህ እናድርግ፡ ምናልባት... ሌሎችን መጉዳት ወይም ማሳዘን አልፈልግም። ምናልባት ግን፡ ከቻልክ፡ **ሰባት ማሕተሞች**፡ በምንሰብክበት ጊዜ ላይ፡ መምጣት ትችላለህ። እያችሁ፡ **ከላይ ከክብሩ፡** እና፡ **እንዴት ድንቅ ነህ፡** ሁለቱንም መዝሙሮች፡ ቀድቼ ማስቀመጥ፡ እፈልጋለሁ።

9 ኦህ፡ ጌታን ማገልገል ደስ አይልም ወይ? ክርስቲያን ባልሆን ኖሮ ምን እንደማደርግ አላውቅም!... ?... በቃ ክርስትያን መሆን ደስ ይላል። ወደላይ-እና-ወደታች እየዘለልህ፡ በሙሉ ድምጽ ተጠቅመህ፡ ጩህ ጩህ ይለኛል። ክርስትያን መሆን፡ በክርስቶስ መጽናትን! እስቲ አስቡት፤

10 የዚህ ወንድም ስም ሁሌ አሳሰቼ እንደምጠራው አውቃለሁ። ኤስ፡ ቲ፡ ወይም ቲ፡ኤስ፡፣ ወይም ዓይነት ነገር ነው። ሳምነር ይባላል፡ ወንድም ሳምነር ነው። እሱን... እና የተወደደች ሚስቱን ላመሰግናቸው እወዳለሁ። **የሰባቱ አብያተ ክርስትያን ዘመናት** መጽሐፍ፡ ጽፋ ለመጨረስ፡ ሰድሰት ወራት፡ ያህል የፈጀባት ይመስለኛል። አሁን በሙላት ተጽፎ፡ ለአርትዖት ተዘጋጅቶ፡ ተሰጥቶናል፡ **የሰባቱ አብያተ ክርስትያን ዘመናት** መጽሀፍ፡ በቅርብ ይታተማል። እህት ሳምነር፣ ባለሸበት፣ ለሰራሽው ሰራ በርግጥ እንከፍልሻለን። እጅግ፡ እጅግ አድካሚ ሰራ ነው። አዎን፡ **በጣም** ትልቅ ነው። እንኳንስ ከቴፕ እያዳመጡ መጻፍ፡ ድግግሞቹን ለቅሞ ማውጣት፡ እና እንደ መጽሐፍ ማዘጋጀት አይደለም፡ ለማምበብ እንኳን ሰድሰት ወር ይፈጅብኛል። ስለዚህ በደንብ አዘጋጅተን ወደ ማተሚያ ቤት እንልከዋለን፡ ምክንያቱ ቶሎ ተዘጋጅቶ ሰዎች ሁላችሁ በእጃችሁ ላይ መድረስ ያለበት፡ እናንተም ማጥናት ያለባችሁ መጽሐፍ ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ እዚህ እንደገባሁ፡ ቢሊ መጣና፡ መጽሐፉ—አሁን—ወደ ማተሚያ ለመግባት—ዝግጅት ማጠናቀቁን አሳይቶኛል። ስለዚህ እህታችን፡ ይሄን ሁሉ በነጻ እንድትሰሪልን አንጠብቅም። ሰለ ድካምሽ ከቤተ ክርስትያን ይከፈልሻል። ወይም—እንዲህ እናደርጋለን... መጽሐፉ ሲደርሰን ዋጋውን እንለጥፍበታለን፡ ወይም የሆነ ነገር እናደርጋለን፡ ወይም፡ በተሸጠ ቁጥር ትንሽ እንድታገኚ ዋጋ እንጽፍበታለን። የቦርድ አባላትን አነጋግሪያቸው፡ የባለ አደራ ቦርድ አባላት፡ ወይም ሌሎችን፡ እነሱ ያስተናግዱሻል። ጌታ ይባርክሽ በእውነት።

11 የዕድሜ ባለጸጎች ወንድም እና እህት ኪድ፡ እዚህ ጋር ቁጭ ብለዋል፡ መቶ ዓመት ለመግባት ጥቂት ብቻ ይቀራል። ቀደም ሲል አግኝቻት ነበር፡ "ወንድም ቢሊ፡ ዛሬ ምናልባት ለመጨረሻ ጊዜ አንተን የማይባት፡ ቀን ትሆናለች፡" አለችኝ። "በጣም አርጅቻለሁ፡" አለች።

12 “ኧረ፡ አይሁን! እንዲህ ስትሉኝ መስማት አልፈልግም። እናንተ’ኮ እናቴ እና አባቴ ናችሁ፡” አልኳቸው። ወንድም እና እህት ኪድን እነወዳቸዋለን። እኛም፡ ሰው ሁሉ፡ ይወዳቸዋል። እንደው የሆነ ነገር...

13 በዚህ እድሜ የደረሱ አረጋውያን፡ ወደ ቤተክርስትያን እንዲህ እየተራመዱ ሲገቡ ሳያቸው የሆነ ነገር ይሰማኛል። አስቡት እስቲ፡ እኔ ከመወለዴ በፊት ጀምረው ወንጌልን ይሰብኩ ነበር። እኔ አሁን ሽምግያለሁ። አዎን፡ አስቡት እስቲ፡ ከመወለዴ በፊት ይሰብኩ ነበር። እኔ አሁን፡ ሽምግያለሁ ብዬ አስባለሁ። እጅ ለመስጠት ተዘጋጅቼአለሁ እያልኩ ማሰብ እጀምራለሁ። ወንድማችን ኪድ እና እህት ኪድ፡ ሲገቡ ሳያቸው ግን፡ “ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን! ሀሌ ሉያ!” “በፍጹም፡ ተሰፋ አልቆርጥም።” አዎን፡ ወዳጄ ሆይ። የሚሆኑትን፡ ሰታዩ፡ እንዴት እንደሚያበረቷችሁ!

14 እንደገና ስታስቡት፡ በእኔ እድሜ በላይ፡ እስከ አሁን ድረስ ወንጌል ስርጭት ይወጣሉ። ጠዋት መጥተው መጽሀፍ ወሰደው መሸጥ ከቻልን ብለው፡ መጻሕፍት ጠየቁን። በመቶ ዓመታቸው ገደማ፡ ወጥተው ነፍሳትን እንማርካለን ብለው በማሰብ፡ መንገድ ላይ የሚያጫዉቷቸው፡ ካሴቶችን ይጠይቃሉ። አሁን እናንተ ሆይ ትላንትና እንደተነጋገርነው “ሁለት ክንፋችሁ” የት ገባ? አዎን። ትላንትና ይሄን—በተናገረ ጊዜ፡ “ክንፎቹ የት አሉ? ” ብዬ አሳብ ገብቶብኛል። እህት ኪድ እድሜሽ ስንት ነው? [እህት ኪድ፡ “ሰማንያ-አንድ ነኝ አለች።”—አርታዒ።] ሰማንያ-አንድ። ወንድም ቶም፡ ዕድሜህ ስንት ነው? [ወንድም ኪድ አለ፡ “ሰማንያ-ሁለት።”] ሰማንያ-አንድ እና ሰማንያ-ሁለት አመታቸው፡ አሁንም ድረስ ክንፋቸውን እየተጠቀሙ፡ በተግባር፡ አሁንም እየበረሩ ነው።

15 እህት ኪድ የምታውቀው አንድ ነገር በኦሃዮ ተከሰቶ ነበር፣ እና ሰልክ ደወለችልኝ። ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ደውላልኝ፡ አንዲት ህጻን ልጅ፡ ይመስለኛል አራስ ሴት ልጅ፡ ተወለደችና፡ የህጻኗ አንጀት ከውጭ ሆኖ ተወለደች። [እህት ኪድ፡ “ፊኛዋ፡” ነው አለች።—አርታዒ።] የህጻኗ ፊኛ፡ ከአካሏ ውጭ ሆኖ ተወለደች። እና ዶክተሩ ምን ማድረግ እንዳለበት ሰላላወቀ፡ ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ፈራ። እና ጸለይንላት። [“ወንድም ብራንሃም፡ ‘መኖር አትችልም’ ብለው፡ ቀዶ ጥገና አድርገው፡ መልሰዋታል። ፊኛውን ወደ ውስጥ አስገብተውላታል።”] መኖር አትችልም ብለው በማሰብ፡ በቀዶ ጥገና፡ ፊኛውን ወደ ቦታው መልሰውታል። እስከ አሁን ድረስ በህይወት አለች። [“ቱቦው ዝግ ነው።”] ምግቡን—ከሬክተም... የሚያስተላልፈው ቱቦ፡ ዝግ ሆኗል አሉ። እና እህት ኪድ በድጋሚ ደወለችልኝ። እንደገና ጸለይንላት፣ አሁን ቱቦው ተከፍቶ ጤነኛ ሆናለች። ዶክተሯ፡ እዚህ ናት፡ ምሰክር ለመሆን፡ እዚህ ተገኝታለች። አያችሁ? ጌታ ኢየሱስ ታላቁ ፈጣሪ መሆኑ፡ ምሰክር ሆናለች! ሰይጣን ምን ለማድረግ እንደሞከረ አያችሁ? የህጻኗን ህይወት ለመቅጨት ፈለገ። ከዛ በኋላ፡ እናቷ፡ ወደ ጌታ መጣች። [“ቤቴ ውስጥ፡ ህይወቷን ለጌታ ሰጠች።”] ወደ ጌታ ተመለሰች። በህጻን ልጇ ከሆነው ታላቅ ተአምር በኋላ፡ እህት ኪድ ጌታን አሰቀበለቻት።

16 ትናንት፡ ካሊፎርኒያ የሚኖር አንድ ምስኪን አገልጋይ ወድማችን፡ ደውሎልኝ፡ ድሮ ካሊፎርኒያ መጀመርያ ጊዜ ሰሄድ፡ የማውቀው ሰው ነው። ትንሹ የልጁ ልጅ—አራት ወይም... ሶስት የልብ ቫልቮቹ ዝግ ሆነው ተወለደ። እና የህጻንኗን ምሰክርነት ነገርኩት። እንዲህ አልኩት፦ “ሌላ መፍጠር የቻለው

ይህ አምላክ፡ በርግጥ የልጅ ልጅህ ይፈውሳል።" ብቻ ልጅህን አይዞህ በርታ በለው።

17 እና ልጁ መጀመሪያ ካሊፎርኒያ ሳለሁ በጉባኤው ውስጥ ነበር፡ የዛሬ አሥራ ስድስት፡ አሥራ ሰምንት ዓመት ገደማ፡ ይሆናል። ያኔ በካሊፎርኒያ ነበርኩ። እና ልጁ-… ጉባኤው በጣም ተጽኖ ፈጥሮበታል… ህጻኑ ተወለደና፡ የተወለደው ልጅ፡ ሲታይ ችግር ነበረበት፡ ሰማያዊ ሆነባቸው፡ እና ኦክሲጅን እና ሌላ ነገር፡ ለመስጠት ሞከሩ። እናም የሚተርፍ አይመስልም ነበር፡ እና ዶክተሮች ምርመራ ሲያደርጉለት፡ አንደኛዋን ቫልቭ ብቻ፡ ትረጫለች እንጂ—የልቡ ሶስት ቫልቮች፡ ዝግ እንደሆኑ ደረሱበት። ፈጽመው የተዘጉ ሆነው ተገኙ። አባቱንም ጠርቶ፡ "አባዬ፡ ወዲያውኑ ወንድም ብራንሃምን፡ ይደውልለት አለው። ይሄን ሁሉ ንገረው… 'ክርስቶስን ለምነው። ይፈውሰዋል በለው አለው።'" ይኸው ነው። ኦህ፡ ማይ! እያችሁ፡ ትላንት ማታ እንደተነጋገርነው፡ ያዩት ነገር፡ ተጽዕኖ ፈጠረባቸው። ትክክለኛ ነገር በትክክለኛ ጊዜ።

18 ብንቀጥል፡ መቋጫ አይኖረውም፡ ወደ ትምህርታችንም አንገባም፡ አይደለም'ዴ? ሞላሰሰ በቀዝቃዛ ማለዳ እንደሚወፍር፡ እጅግ ወፍራምን እና፡ እርስ በራሱ የተያያዘ ነው። እንዲህ አይነቱ ሕብረት ማድረጋችን ደስተኞች ነን። አዎን፡ ደስ ይለናል።

19 ስለዚህ አሁን የኛን ነገር እናቁምና፡ በቀጥታ፡ ወደ ትምህርቱ እንለፍ። ከመቀጠላችን በፊት… በብላክ ቦርዱ ላይ ይታያችሁ አይታያችሁ፡ እርግጠኛ አይደለሁም። ምናልባት ግን **እንዲህ** ከፍ ካደረግኩላችሁ፡ ከአፍታ በኋላ፡ ማለት፡ ግልጽ ይሆንልናል፡ አሁንም፡ አንዳንዶቻችሁ፡ ከ… [ወንድም ኤጋር "ዶክተር" አለ ብራንሃም፡ "ቦታ ትፈልጋለህ?—እርታዒ።] ምን አልከኝ? ["ለዚያም ቦታ ትፈልጋለህ ወይ?"] አይ፡ አሁን እንኳን፡ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡ ዶክተርዬ። ምናልባት በኋላ። [ወለሉ ላይ፡ ባለ ቦታ ማስቀመጥ እችላለሁ።"] በቃ፡ በኋላ—ትንሽ ቦታ ሳገኝ… ቦታ ተገኘ? እሺ በቃ። ሁላችንም አትኩሮታችን ወደሱ እናድርግ። ከኋላ ያላችሁ ይታያል? ይታያችኋል? ከታያችሁ፡ ብላክ ቦርዱ ውስጥ ያለውን ጽሑፍ፡ ማንበብ ከቻላችሁ፡ እጆችሁን ከፍ አድርጉ። አይታይም። እሺ በቃ። ቦታውን አስተካክሉ። አሁን፡ እነሱ እስኪያዘጋጁ ድረስ…

20 ዛሬ ጠዋት ለመጀመር አረፈድኩ፡ ወይስ፡ አይ፡ አይ፡ አስራ አምስት ደቂቃ ቀደም ብያለሁ። ስለዚህ፡ አሁን፡ መቸኮል ስለማንፈልግ፡ ጊዜያችንን እንጠቀማለን። ሰትቸኩሉ፡ ያን ጊዜ የምትናገሩትን ነገር ታበላሻላችሁ። እና፡ እንደነገርኳችሁ፡ በቀደምለት፡ የተቀዳውን እየሰማሁ፡ በራሴ አፈርኩ፤ ያፈርኩት በተናገርኩት ነገር ሳይሆን፡ በፍጥነት በመናገሬ፡ እና የድምጽ መውጣት መውረድ። መጠበቅ እንዳለብኝ ይሰማኛል። እና…

21 ባለፈው ቀን እዚሁ ሉዊስቪል መሀል፡ አንድ ትልቅ መካነ አራዊት— ሲገነቡ አይቻለሁ። በአካባቢው የሚገኘው፡ አቶ ብራውን፡ ይመስለኛል፡ ለመካነ እንስሳቱ አንድ ሚልየን ዶላር ሰጥቷል። እንግዲህ፡ ገንዘቡ የኔ ቢሆን፡ እንስሳቱን ነጻ ለማስወጣት እሰጣቸው ነበር። እኔ—ምንም ዓይነት ነገር በመዝጋት አላምንም። ሁሌጊዜ… መካነ እንስሳት ሄጄ ምስኪን ድቦችን፣ እና አንበሶችን፣ እና ሌሎች እንስሶች ሁሉ፡ የዕድሜ ልክ እስራት፡ ተፈርዶባቸው፡ ወደ ፊትና

ወደ ኋላ ሲንቀሳቀሱ እያለሁ። መጥፎ ስሜት እንዲሰማችሁ ያደርጋል። የሚያሳዝነው፡ ከነሱ ይልቅ በሚበልጡ ብልህ ሰዎች መያዛቸው ነው። አያችሁ? ይይዟቸውና እስር ውስጥ ይከቷቸዋል።

22 እንደማስበው፡ የዲያብሎስ ስራም እንዲህ ነው። በእግዚአብሔር ታላላቅ ቦታዎች እና ሜዳዎች ሁሉ፡ እና—የተለያዩ ሰፍራዎችን፡ በነጻነት መዞር የሚገባቸው ውድ ሰዎችን፡ በማይረባ የሐይማኖት ተቋም፡ ወይም በአዋልድ፡ ወይም በሌላ ነገር ውስጥ፡ እሰሮ ያሰቀምጣቸዋል። እና እንዴት ያለ አሰቃቂ ነገር ነው።

23 እኔ መካነ አራዊት አልወድም። እኔ ራሴ ከእንስሳቶቹ እንደ አንዱ የሆንኩ ይመስለኛል፡ እሰባችሁታል፡ የሆነ ነገር ለማድረግ ፈልጋችሁ—ሙሉ በሙሉ ተዘግቶባችሁ፡ ለመውጣት ስትጣጣሩ አስቡት።

24 አሁን፡ ወደ ቃሉ ከመቅረባችን በፊት፡ አንገታችንን ዝቅ በማድረግ፡ በጸሎት ወደ ቃሉ ደራሲ እንቅረብ።

25 ቸር የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ጠዋትም በውድ ልጅህ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ ተሰብስበናል። እግዚአብሔር፡ በሥጋ ሆኖ፡ ስለ ኃጢአታችን ሰርየት፡ ወደ ምድር የመጣ፡ የሞተልን፡ ጻዲቁ፡ ገና ዓመፀኞች ሳለን፡ በእርሱ ጽድቅ፡ ፍጹማን እንሆን ዘንድ፡ ስለ እኛ ሞተ። ጌታ ሆይ፡ የማይገባን መሆናችንን እየተናዘዝን እንቀርባለን። እኛ ምንም ጥሩ ነገር የለንም። እኛም በየትኛውም ጥግ ብንቆምም ሁላችንም እስር ቤት ውስጥ ነን። በአንድ ትልቅ እስር ቤት ውስጥ እንገኛለን። አንዱ ሌላውን መርዳት አይችልም። ጌታ ግን፡ በማያልቀው ምህረቱ፡ እኛን ነጻ ለማውጣት፡ ከላይ ወርዶ፡ የእስር ቤቱን በሮች ከፈተ። ከአሁን በኋላ፡ ነጻ ነን እንጂ፡ በዓለም መካነ እንስሳት ውስጥ አይደለንም። ወጥተናል። እስረኞች አይደለንም።

26 አቤት፡ ለሱ ያለን ፍቅርና ምስጋና እንዴት ድንቅ ነው! የተሰፋ ቃሉ ታላላቅ መሰኮች አብዝተን ሄደንባቸዋል፡ በፊታችንም ሲገለጡ አይተናል! ታላቁ የዘላለም አምላክ፡ ለቀደሙት ነብያት እንዳደረገው ሁሉ፡ ለእኛም እራሱን እውን እያደረገ፡ በፊታችን ሲገልጥ በገዛ አይኖቻችን አይተነዋል። ይህ ህይወት፡ በማይጠፋው የዘላለም ህይወት፡ በትንሣኤ ከተዋጠ በኋላ፡ አንድ ቀን ዳግመኛ እንደምንመለስ አውቀን፡ የጸና ተሰፋ ይዘን እናርፋለን። ከእርሱ ጋር እንኳዛለን እንጂ። ሰውነታችን አያረጅም። መቼም አንሞትም። በጭራሽ አንራብም። አንዳችም አያሳጣንም። “ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፡ ወደ ተዘጋጀላችሁ፡ ወደ ጌታ ደስታ ግቡ” ሲል መስማት እንፈልጋለን። ኃጢአት ከመግባቱ በፊት፡ ለአዳምና ለሔዋን፡ ያደረገው ዝግጅት፡ ህመም ወይም ችግር በጭራሽ እንዳይነካቸው ነበር። አሁን ደግሞ እኛ እንደምንመጣ አስቀድሞ ሰላወቀ፡ ለእኛ አዘጋጅቶልናል። ኃጢአት ትልቅ የጥል ግድግዳ አደረገ፡ አሁን ግን፡ ኃጢአት በኢየሱስ ደም ተወግዷል። አሁን፡ በዘላለማዊው፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፡ ስለ ተሰፋይቱ ምድር የታጨን ነን።

27 አባት ሆይ፡ ቃልህን ስንማር፡ ባርከን። ወደ ምድሪቱ ለመግባት፡ ምን አይነት ሰዎች መሆን እንዳለብን ማወቅ እንፈልጋለንና። ታላቁን መምህራችን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ዛሬ በዚህ ክፍለ ጊዜ ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ፡ ወርዶም

በገዛ ቃሉ፡ እራሱን ይገልጥልን ዘንድ እርዳን። ስለ ክብሩ በገዛ ስሙ እንለምንሃለንና። አሜን።

28 አሁን፡ ከሁሉ በፊት፡ አብረን ሁለተኛ ጴጥሮስ፡ ምዕራፍ 1 እንከፍታለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ ሁለተኛ ጴጥሮስን፡ 1ኛውን ምዕራፍ ማንበብ እፈልጋለሁ። ብዕር እና ወረቀት ለያዛችሁ ለእናንተ...

29 ዛሬ ማለዳ እንደተነገረኝ—አንዳንድ ጊዜ ጭንቅላቴን ዞር ማድረጌ፡ ቴፑን ያደበዝዛል፡ ተብያለሁ። በርግጥ አውቄ አይደለም ያደረግሁት። ምናልባት፡ አንድ ቀን፡ ከጣርያው በታች የሚንጠለጠለውን—ዌብ ማይክን፡ ማዘጋጀት ከቻልን፡ ከጣርያው በታች ካንጠለጠልን፡ በዙርያ ሁሉ፡ የትም ሆናችሁ ብትናገሩ፡ ቆንጆ ይሆናል፡ ፈጽሞ ትክክል ያደርገዋል።

30 አሁንም፡ እኔ እየተናገርኩ፡ ወይም፡ ከጉባኤው በኋላም ይሁን፡ ስንጠረዡን፡ በሰዕል መያዝ ትችላላችሁ። እኔም እዚሁ ላይ ጽፌዋለሁ። ምናልባት ለሌላ ጊዜ እንዲጠቅማችሁ፡ ማጣበቂያ ነገር ወስጄ፡ ፊት ለፊት እሰቅለዋለሁ። ዛሬ ከሰዓት በደንብ እንድንረዳው፡ ቀደም ብላችሁ ኑ።

31 አሁን **ሰባቱ የቤተክርስትያን ዘመናት** ጨርሰናል። ወደ **ሰባቱ ማሕተሞች** እየተቃረብን እንገኛለን። ይህ መልዕክትም፡ በጌታ ኢየሱስ ደም የሚዋጁትን ሰዎች የሚያስተሳስር፡ ትምህርታዊ መልዕክት ሲሆን፡ የሚፈጸምበት የቤተ ክርስትያን ዘመን፡ በማሕተሞቹ መጨረሻ በምትመጣው ዘለአለማዊት የቤተክርስትያን ዘመን ላይ ነው። ከዚህ በኋላ ስንቀጥል፡ የምንማራቸው፡ ሰባቱ መለከቶች፣ ሰባቱ መቅሰፍቶች፣ ወዮዎች፣ ወዘተ ይሆናሉ። ሰዎች የሚቀመጡበት ስፊ አዳራሽ እስክናገኝ ድረስ እየጠበቅን ነው።

32 እና አሁን፡ ይሄኛው የምጠብቀውን ነገር ድምዳሜ አድርጌ እሰቤዋለሁ። ይሄኛው ስንጠረዥ እሰላለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር። በቀደምለት ግን ከኬንታኪ ከሆኑት የተወደዱ አብሮ አደግ፡ ጓደኞቼ፡ ጋር ነበርኩ። ምናልባት ወቅቱ ከማለቁ በፊት፡ አንድ ወይም ሁለት ቀን ሽኮኮን አድናለሁ ብዬ በማሰብ ነው የሄድኩት። እና ከጓደኛዬ ከቻርሊ ጋር፡ እና ከወንድሙ ከሮድኒ ጋር፡ ጫካ ውስጥ፡ አብረን ቆየን። አንድም ሽኮኮ አላየሁም። በጫካዎቹ መካከል ከርቀት እየተኰሰኩ እስፈርቻቸዋለሁ መሰለኝ። ለእናንተ ወንዶቼ፡ እና—ለነ እህት ኔሊ እና ማርጂ፡ የሆነ ነገር ተቀብያለሁ፡ እሁድ ሲደርስ እነግራችኋለሁ ያልኳችሁ ነገር ይህ ነው። እንድናገረው ወደ እኔ የመጣው መልዕክት፡ ይህ ነው። ሌላው ሁሉ በዚህ ላይ የሚተሳሰር ይሆናል! እና፡ አቤት፡ በጣም ወደድኩት። በጫካዎቹ መካከል፡ ጩኽ—ጩኽ—የሚል እውነተኛ መንፈስ ነበር።

33 ስለዚህ አሁን፡ ከአንደኛ ጴጥሮስ፡ ማለት... ከሁለተኛው ጴጥሮስ፡ 1ኛ ምዕራፍ፡ ከፍለን፡ ጥቂት እናነባለን።

**የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፡ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ፤**

34 አጀማመሩ በጣም ደስ ይላል፡ ምክንያቱ የዛሬ ማለዳ ሙሉ ርዕሴ በእምነት ዙርያ የሚዳሰስ ነውና። አያችሁ? በደንብ አድምጡኝ። ደግሜ ላንብበው።

**የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፡ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ... ካገኘነው** ጋር **የተካከለ የክብር እምነትን...** ላገኙ—**ላገኙ፤**

35 የሚለውን፡ አባባሉን፡ አስተውሉት፦ "እኔ ይህን እምነት ተቀብያለሁና፡ መልዕክቴም እንደኔ ይህን የክብር እምነት ለተቀበሉት ሰዎች ይድረስልኝ።" መልዕክቴ... ለዓለማውያን አይደለም። መልዕክቴ ለቤተ ክርስትያን፡ እና፡ በክርስቶስ ላሉት ነው ይለናል።

**በእግዚአብሔርና** (በ) **ኢየሱስ** ክርስቶስ **በጌታችን እውቀት ጸጋ እና ሰላም ይብዛላችሁ።**

**የመለኮቱ ኃይል** በገዛ **ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ... የመለኮቱ ኃይል ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል...** የሚሆነውን **ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፡ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ** የጠራንን **በማወቅ፤**

**ከመለኮት ባሕርይ**... **ተካፋዮች በተሰፋ** ቃል **እንድትሆኑ፤ በእነዚያ** (የተሰፋ ቃላት) **ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተሰፋን ሰጠን፡...**

36 አሁን በደንብ ጠልቀን እንግባበት። የዛሬ ጠዋት ክፍል ጊዜ፡ ስብከት አይደለም። "ስለ መለኰትዊ ባህርይ" ትምህርት ነው። በደንብ እንዲገባችሁ፡ 4ኛ ቁጥር ደግሜ ላንብብላችሁ። "በእነዚያ የተሰጠን... "

**ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድትሆኑ፤ በእነዚያ** (የተሰፋ ቃላት) ስለ **ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጠን፡ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድንሆን ሰጠ።**

37 አያችሁ፡ "በዓለም ካለው፡" አሁን አምልጠናል። መልዕክቱ ለቤተክርስትያን ነው። ዛሬ ጠዋት እዚህ ያለነውም፡ መንገዱ ምን እንደሆነ፡ የእግዚአብሔር ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማወቅ ነው። እግዚአብሄርን እየወደደ፡ ክርስቶስን መምሰል የማይፈልግ ሰው—ማንም የለምና። ሁሉም እዚህ ተዘርግቷል። ክርስትያን ሁሉ! እኔ ራሴ ከቀደምቶቹ አንዱ ነኝና። ወንድም ኪድ እና እህት ኪድን እዩአቸው፡ ምናልባት በእድሜ ከፍ ያሉ እነሱ ናቸው። "የልባችሁ መሻት ምንድነው? " ብዬ ብጠይቃቸው ግን፤ መልሳቸው "ወደ ጌታ አብዝቶ መቅረብ፡" ሳይሆን አይቀርም። ክርስቶስን ስታውቁት፡ ሁልጊዜ ወደ እርሱ እንድትሳቡ የሚያደርግ፡ የተለየ ፍቅር አለው።

38 ስለ አገላለጽ ይቅርታ አድርጉልኝ። በቅርብ ጊዜ፡ ባለቤቴን፡ "ዛሬም እንደ ድሮሽ ታፈቅሪኛለሽ ወይ? " መቼም አሁን... ሁለታችንም፡ አርጅተናል፡ ብዬ ጠየቅኳት፤

"አዎን በደንብ አፈቅርሃለሁ፡" አለችኝ።

39 እኔም፡ "ታውቂያለሽ፡ አንቺን ወሰጄ ወደ ውስጤ አስገብቼሽ የእውነት አንድ እስክንሆን ድረስ፡ በትክክል፡ አንድ፡ ሆነን እስክንታይ ድረስ፡ እጅግ አፈቅርሻለሁ" አልኳት።

40 ይሄን በመቶ ሚልየን አባዙትና፡ በክርስቶስ ፍቅር የወደቀ አንድ አማኝ ከፍቅሩ ብዛት የተነሳ፡ ምን ያህል አብዝቶ፡ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሚፈልግ፡ ትገነዘባላችሁ። አሁን ደግሞ በእነዚህ የተሰፋ ቃላት ምክንያት፡ የክርስቶስን መለኮታዊ ባህርይ ተካፋዮች፡ መሆን እንዴት እንደምንችል ያስተምረናል። በዚህ፡ ሟች አካል፡ እንዴት መካፈል እንችላለን።

41 እኔ ይሄን የማምንበት ምክንያት... እዚህ ጋር አንድ ነገር ልናገር። ባለፉት ቅርብ ቀናት፡ በተሳሳተ መንገድ የተረዳኝ ሰው ነበር። ስለ እምነቴ በሚመለከት ከአገልጋዮች ማሕበር፡ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ልከውልኝ... “ከትዳር አጋራችን ጋር የነፍስ-ቁርኝት አለን። የነፍስ-ቁርኝት የሌለን ከሆንን ትዳራችንን ፈተን፡ በነፍስ-ከሚቆራኙን ሌሎች ጋር መጋባት አለብን ትላለህ ይላል።” ኦህ፡ ማይ!

42 እኔ እንዲህ አይነቱ ነገር እቃወማለሁ እንጂ። “እንደዚህ ባለ መናፍቃዊነት አልታማም፡” አልኳቸው። እኔ—በዚህ አላምንም። በጭራሽ አላምንም። ጌታ የትዳር አጋር እንደሚሰጠን አምናለሁ። ያ እውነት ነው። አንዳችን የሌላችን አካል ነን። ትክክል ነው። አንድ ሰው ከማግባቱ በፊት፡ እነዚህን ነገሮች ማሰብ እና ማጥናት አለበት።

43 በቀደምለት አንድ ወጣት ልጅ፡ እንዲህ አለኝ፦ “ወንድም ብራንሃም፡ **እንዲህ-እና-እንዲህ** የምትባል ሴት፡ ባገባት፡ ምን ይመስልሃል? ”

“ምን ያህል ታስባታለህ? ” ብዬ ጠየቅኩት፤

“ኧረ፡ ወይኔ፡ በጣም አፈቅራታለሁ፡” አለኝ።

እኔም፦ “በል፡ ከሷ ውጭ መኖር የማትችል ከሆንክ፡ ቶሎ ብታገባት ይሻልሃል አልኩት። ያለሷ መኖር ከቻልክ ግን ባይሆን ይሻልሃል። ስለዚህ፡ ሞትኩላት የምትል ከሆነ ግን፡ ቶሎ ሄደህ—ብታገባት ይሻላል፡” አልኩት። ወደሱ እንዲደርስ የፈለግኩት፡ መልዕክት፡ መልዕክቱ ምንድነው፡ በጣም የምትወዳት ከሆነ!

44 አሁን፡ አሁን፡ ከማግባታችሁ በፊት፡ ሁሉም ነገር ደህና እና ያማረ ነው። ከተጋባችሁ በኋላ ግን፡ የህይወት ድካም እና ፈተናዎች ይመጣሉ። ያኔ ነው በፍቅር አንድ እንድትሆኑ እርስ በርሳችሁ መረዳት አለባችሁ። በእሷ ቅር ስትሰኝ፡ ወይም እሷ በአንተ ቅር ስትሰኝ፡ እርስ በእርስ መረዳዳታችሁ ይቀጥል።

45 በክርስቶስም እንደዛ ነው። አያችሁ? አንድ ነገር ከእርሱ ለምነን፡ ባይሰጠንምም እንኳን፡ ምንም የማንነቃነቅ እስክንሆን ድረስ፡ ከእሱ ጋር በፍቅር መሆን አለብን። አያችሁ? ለምን እንደሆነ? ገብቷችኋል? ይሄን መፈጸም የምትችሉበት፡ ለምን እንዳልሰጣችሁ የምትረዱበት ብቸኛው መንገድ፣ የመለኮታዊ ባህሪው ተካፋዮች እንድትሆኑ ብቻ ነው። “የመለኮታዊ ባህሪው ተካፋይ።”

46 ተከታተሉኝ፦ “ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ።” አምልጣችኋል! ለማን እንደሚል ገባችሁ? ለቤተ ክርስትያን፡ከነዚህ ሁሉ በላይ ከፍ ላደረጋቸው፡ በክርስቶስ ላሉት ሁሉ ነው። እራሱን ከፍ ከፍ ላደረገ ሳይሆን፡ ክርስቶስ ላከበረው ሰው።

47 ዛሬ ጠዋት እዚህ ለተገኛችሁ ጥቁር ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ ይሄን መናገሬ ማንንም ለመጉዳት አይደለም። በዚህ ቤተክርስትያን ተናግሬ እንደሆን

አላውቅም፡ ነገር ግን፡ ከተወሰነ ጊዜ በፊት አንድ ጉባኤ ውስጥ ነበርኩ። ብዙ ቦታዎች ተናግሬዋለሁ። እና አንድ ጥቁር እህታችን ተነሰታ “ምስክርነት አለኝ፡ መመሰከር እችላለው?” ብላ ጠየቀች።

“አዎን፡ እህቴ፡ ቀጥይ ተባለች።”

48 “ምስክርነቴ ለጌታ ክብር እንዲሆን ፈልጌ ነው፡” አለች። እንዲህ አለች፡- “ታውቃላችሁ፡ እኔ—መሆን እንደሚገባኝ አልሆንኩም፡” አለች፡ “እኔ—መሆን እንደሚገባኝ አልሆንኩም፡ ነገር ግን፡” አለች፡- “አንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ፡ ድሮ እንደነበርኩት ግን አይደለሁም።” አያችሁ? ከሆነ ነገር ወጥታለች። ከፍ ተደርጋለች።

49 ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገራችንን የምናውቀው በዚህ መንገድ ነው። ተጠርበን የወጣንበትን ጉድጓድ መለስ ብለን እነየው። አያችሁ? መሆን የምንፈልገውን አይደለንም፡ እኛ መሆን የሚገባን እንኳን አይደለንም፤ እንደ ቀድሞው አለመሆናችን ግን፡ ይህ አንድ ነገር ደስ ይለናል። እውነት ነው። መንገዱ ላይ ነን።

50 “በዓለም ካለው ጥፋት አምልጠናል።” በዓለም ካለው ጥፋት፡ እና ከክፉ ምኞት አምልጣችሁ፡ ከፍ ብላችሁ ወጥታችኋል። አሁን ጴጥሮስ እየተናገረ ያለው ሰው—እንዲህ አይነቱን ሰው ነው፡ ከእንዲህ አይነት ነገሮች፡ አያችሁ፡ ከዓለማዊ ጥፋት ያመለጠን ሰው።

> **ስለዚህም** ምክንያት፡ **ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ፡** በእምነታችሁ **በጎነትን ጨምሩ፡ በበጎነትም እውቀትን፤**
>
> **በእውቀትም ራስን መግዛት፡... ራስንም በመግዛት መጽናትን፡... በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፤**
>
> **እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፡ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።**

51 ምን ማድረግ እንዳለብን፣ እንዴት ማድረግ እንዳለብን የምናውቅበት ዝርዝር አስቀምጦልናል። አሁንም፡ አስቀድሜ እንዳልኩት፡ ሁላችንም ወደ እግዚአብሄር ለመቅረብ እየተጋን ነው። ዛሬ ጠዋት ይህን መልእክት፡ ለቤተ ክርስቲያን የመረጥኩበት ምክንያት፡ ጉዞ ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን ስላወቅኩ ነው። ትላንትና ማታ፡- “ከከተማው ውጭ፡ የመጣችሁ ስንቶች አላችሁ?” ብዬ ሰጠይቅ፤ ከህዝቡ ዘጠና-ሰምንት በመቶ፡ ከከተማ-ውጭ-የመጡ ናቸው። “ከመቶ ማይል ርቀት የመጣችሁስ?” ስላቸው፡ ከሰማንያ በመቶ፡ በላይ፡ ያለፈ ይመስለኛል። “ከአምስት መቶ ማይልስ ርቀት የመጣችሁስ?” እዚህ ካለው ጠቅላላ ህዝብ አንድ—ሶስተኛው የሚያህል ከአንድ፡ ከአምስት መቶ ማይልስ ርቀት የመጣ ነው። እና የሚኀዙትን ሰዎች፡ አስቧቸው። አያችሁ፡ እነዚህ ሰዎች ለመታየት ብለው አልመጡም። ዓለም ሊያየው የሚችል አይነት የሚታይ ውጫዊ ውበት... የላቸውም። ሁሉም ተራና፣ ድሆች፣ የተለመደ ልብስ የለበሱ ሰዎች ናቸው። መላእክታዊ-ለማስመሰል-በመለከት የሚዘምር አስመሳይ ኳየር፣ ወይም የምንታይበት ምርጥ ባለ ህብረ ቀለም መስኮቶች የሉንም። አግዳሚ ወንበር ላይ በመቀመጥ እና በግድግዳ ጥግ በመቆም በጣም ከባድ ጊዜ አሳልፋቿል። እነሱ ይሄን ፈልገው አልመጡም። የሚመጡት በውስጣቸው የተፈጥሮ ዓይን የማያየው ውበት

የሚያይ ነገር ስላላቸው ነው። በክርስቶስን ውበት የሚሳበው መንፈሳዊ ዓይን ነው። ለዚህ ነው የሚመጡት።

52 ስለዚህ፡ ወደ አገልግሎት ከመጀመራችን በፊት፡ ለብዙ ቀናት ያለማቋረጥ ጸልያለሁ። እርሳስ እና ወረቀት ኪሴ ውስጥ... ይዤ፡ ሚስቴን "ዛሬ ሽኮኮን ለማደን እሄዳለሁ፡" አልኳት። ሉክ እና እርሳስ ኪሴ ውስጥ ያዝኩኝ። ማየት የምችልበት በቂ ብርሃን ሲነካኝ፡ ዛፍ ስር ቁጭ ብዬ፡ እጆቼን ወደ ሰማይ አነስቼ፡ እንዲህ እጸልያለሁ፦ "ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ምን ላድርግ? ለልጆችህስ ምን ትሰጠኛለህ? "

53 ከዛ በኋላ የሆነ ነገር ተቃጥሎ እንደረገፈ ሲሰማኝ፡ መገኘቱ እየቀረበኝ ይመጣል። የሆነ ነገር እንዲህ ይወርዳል፡ ትዕዛዝ መሳይ ነገር፡ እንደ ድምጽ የመሰለ ነገር መስማት እጀምራለሁ። "ሁለት ጊዜ ሁለት አራት።" ይቀርባል፦ "ሁለት ጊዜ ሁለት አራት። ሁለት ጊዜ ሁለት አራት። ሁለት ጊዜ ሁለት ይሆናል አራት።" እንዲህ እያለ፡ ይቀጥላል፡ ይቀጥላል፡ ይቀጥላል። መገኘቱ እየመጣ ነው።

54 ያኔ እራሳችሁን ስጡ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከራሳችሁ ትለያላችሁ። "**እንዲህ-እና-እንዲህ** አይነት ቦታ ሂድና፣ **እንዲህ-እና-እንደዚህ** አይነት ነገር ይሆናል፡" ራእይ ይመጣል። እያችሁ? ከዓለም ርቃችሁ፡ ወጥታችሁ፡ በምድረ በዳ፡ ወደ ራሳችሁ በመመለስ፡ አሳባችሁን ጥላችሁ፡ ወደ እግዚአብሄር ትመለሳላችሁ።

55 እና "አንድ፣ አንድ... " እያለ መምጣት ይጀምራል፤ እንዳልኩት፡ ማንኛውም ቁጥር ወይም የሆነ ነገር፡ ቀስ በቀስ ጀምሮ፡ በዝግታ ይገባና። እየፈጠነ፡ እየፈጠነ ይመጣል። እናንተ ምንም አትበሉ፡ ቁጭ ብላችሁ እጆችሁን ከፍ አድርጉ፡ እጆችሁን ወደ ሰማይ አንሱ። በመጀመርያ የሚታወቃችሁ፡ ሁለመናችሁ መወሰዱ ነው። ከዛ በኋላ ሊመጡ ያሉትን ነገሮች እያሳያችሁ፡ እንድታውቁት የሚፈልጋችሁ ነገሮች ያሳያችኋል።

56 አንዳንድ ጊዜ የተወሰነ ድረስ፡ እስከ ተወሰነ ርቀት ድረስ ይመጣል፡ ከዛ ያቆማል። ወደ ራእይ አይቀጥልም። ቅዱስ ቃላት መጉረፍ ይጀምራሉ። እንዳልረሳቸው፡ ብዕሬን አነስቼ፡ እጽፋቸዋለሁ፡ መጻፍ እጀምራለሁ።

57 ወደ ቤት መጥቼ በደንብ አየዋለሁ፡ አጠናዋለሁ። አንዳንዱ ባየውም ትርጉም አይሰጠኝም። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፡ እንደገና፡ ይመጣል! ይነካችኋል፡ ከዚያም ይሄዳል። አነሰ ያለች **እንዲህ** አይነት ማስታወሻ ይዤ፡ የነገረኝን ሁሉ፡ የቻልኩትን ያህል ጠንክሬ፡ መሳል እጀምራለሁ። "ጌታ ሆይ፡ ወደ ቤተ ክርስትያን እሄዳለሁ። አሁን... 'ኑ ተሰብሰቡ።' የሆነ ነገር ይዤላችሁ መጥቻለሁ እላቸዋለሁ፡" ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ፡ አመጣጡ ይሄ ነው። እውነቱ ይህ ነው። አስቀድሜ፡ ከእሱ፡ እስካልተቀበልኩ ድረስ፡ ፈጽሜ አልሰብክም።

58 እንግዲህ አሁን፡ እኔ አሁን ሳያቸው የምታዩኝ፡ እነዚህን ሰንጠረዦች። ይሄኛው መጀመርያ፡ የጀመርኩት ክፍል፡ አንድ ቀን፡ ወይም ሁለት ቀን በፊት ድረስ፡ ጫካው ውስጥ አልተቀበልኩትም ነበር።

59 አሁን እነዚህ—እነዚህ ሰዎች... እዚህ ጋር፡ ጴጥሮስ የነገረን ነገር፡ መለኮታዊ ባህሪው ተካፋይ መሆን እንዴት እንደሚገባን ነው። አሁን፡ ሁላችንም ወደ እግዚአብሄር ቁመና ማደግ የምንፈልግ ሰዎች ነን።

60 አሁን፡ ሰባቱ ማሕተሞችን ከጨረስን በኋላ፡ ሰባተኛው ማሕተም በሚሰማበት፡ ወይም በሚፈታበት... ጊዜ፤ እርግጥ ነው፡ ማኅተም ማለት፡ ሰባት ማኅተም መፍታት ማለት፡ አገልግሎትን መፍታት እንደሆነ እናውቃለን። በሰንጠረዡ ላይ በትክክል የምናየው ነው። ተዘግቶ የነበረውን መልዕክት፡ ማስተላለፍ ነው።

61 ባለፈው እሁድ ምሽት፡ “ቁልፉ፡” የሚል ስብከት ሰብኬአለሁ። ቁልፉ እምነት ነው። ቁልፉን የያዘው እምነት፡ ቁልፉም ቅዱስ ቃል ነው። በሩም ክርስቶስ ነው። አያችሁ? ስለዚህ እምነት የቅዱስ ቃላት መንኰራኩሮች ይይዝ እና፡ የጌታን ክብር እና መልካምነት ለህዝቡ ይከፍታል። አያችሁ? ስለዚህ እምነት፡ ክርስቶስ፡ ለህዝቡ የሚታወቅበት፡ እና የሚገለጥበት፡ መክፈቻ ቁልፍ ያዥ ነው።

62 ዛሬም፡ ያንኑ ቁልፍ ወስደን በመጠቀም፡ በእግዚአብሔር ቁመና፡ ህያው አምላክ የሚያድርበት መልካም ክርስቲያን የመሆኛ፡ ህያው ማደርያው ለመሆን፡ እና መንገድ ለመክፈት እንሞክራለን።

63 አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ራሱን በሦስት መንገዶች ገልጧል። በመጀመርያ ጊዜ፡ አባት ተብሎ በተጠራበት መጠርያ፡ እራሱን በእሳቱ አምድ ገለጠ። ከዛ ቀጥሎ፡ እግዚአብሄር እራሱ፡ ባዘጋጀው አካል፡ በዚሁ አካል፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እራሱን ገለጠ። በሦስተኛ ደረጃ፡ በዚያ አካል መሞት ምክንያት፡ መኖርያ የምትሆነውን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ ቀደሰ። እግዚአብሄር ከእኛ በላይ፣ እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ፣ እና ያንኑ እግዚአብሔር፡ በእኛ ውስጥ ማለት ነው።

64 አባት፣ ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ የተባለበት ምክንያት ይህ ነው። ስለዚህ ሦስት አማልክት ሳይሆን፡ በሦስት መገለጫዎች የተገለጠ አንድ አምላክ ነው። ያኔ በኒቂያ ጉባኤ ይሄን ቢያስቡት ኖሮ፡ ሁላችንም እንበላሽም ነበር፤ አይደለም'ዴ? አዎን። ሦስት አማልክት አይደሉም። ኢየሱስ ስለ አብ የሚናገረው ነገር፡ እሱ እና አብ አንድ እንደሆኑ ህዝቡ መረዳት አልቻለም። ነገሩ ሁሉ፡ እንዲህ ነው። እርግጥ፡ አሁን ነው የተገለጠው። በትክክል። አያችሁ? ሦስት መገለጫዎች እንጂ፡ ሦስት አማልክት አይደሉም! ሦስት-...

65 ምንድነው? ጌታ በፍጥረቱ ላይ የበላይነቱን እያሳየ ነው። ጌታ መመለክ ይወዳል። **አምላክ** የሚል ቃልም “የሚመለክ ነገር” ማለት ነው ስለዚህ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ህዝቦች ላይ፡ እነሱን የፈጠረበት ዓላማ የሚገኝባቸው እንዲሆኑ ለማድረግ ህዝቡን እያበረታ ነው። የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች እንድትሆኑ በቀር ለሌላ አልፈጠራችሁም። ይሄን ከሳታችሁ፡ የእግዚአብሄር ወንድ እና ሴት ልጅ መሆን ካልገባችሁ፡ መሰመር ስታችኋል።

66 እና “መሣት፡” ወይም **ሐ-ጥያ-ት** ማለት “መሰመር መሣት፡” መሰመር መሣት። ዒላማ ሐምሣ ያርድ ላይ እቁሜ፡ እነጣጥሬ፡ ብተኩስ፡ ጠመንጃዬን ደቅኜ፡ በአራት ወይም በአምስት ኢንች፡ ብስተው፡ ትኩሼ ብስት፡ ችግሩ

ምንድነው? የሆነ ችግር አለ። ጠመንጃዬን መቃኘት አለብኝ። እግዚአብሄር ክርስትያን እንድትሆኑ ጠርቷችኋል... ስለዚህ በእግዚአብሄር ካለው እምነት ከሳትሁ፡ ክርስትናዬን ከሳትሁ። ወደ አንድ አቅጣጫ ከዘመማችሁ፡ ተመለሱና ተቃኑ። እናንተን ሊያቃናችሁ የሚቻለው ብቸኛ ነገር ደግሞ፡ ቃል ነው። በቃል ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ፡ ያቀናችኋል፡ በቀጥታ ወደ ዒላማው ይመልሳችኋል። ትክክል ነው።

67 ስለዚህ አሁን፡ ቃሉን እንማራለን። እስጢፋኖስ፡ በሐዋርያት ሥራ 7 ላይ የተናገረውን፡ እሺ... እሱ ብቻ እናንብብ። (አሁን እየተነጋገርን ያለነው፡ ስለ እግዚአብሔር ማደርያ ነው።) (የሕያው እግዚአብሄር ሕያው ማደርያ፡ ስለመሆን ነው።) አሁን፡ የእስጢፋኖስ ነገር... እስጢፋኖስ፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 7 ላይ ሲናገር፡ ይመስለኛል... በሐዋርያት ሥራ 7፡ ከ44ኛው ቁጥር ጀምሮ፦

> **እንዳየው ምስል አድርጎ ይሠራት** ዘንድ፡ **ሙሴን ተናግሮ እንዳዘዘው፡ የምስክር ድንኳን፡ ከአባቶቻችን ዘንድ በምድረ በዳ ነበረች፤**
>
> **አባቶቻችንም** ደግሞ በተራ **ተቀብለው፡** አባቶቻችን... **እግዚአብሔር በፊታቸው ያወጣቸውን የአሕዛብን** አገር **በያዙት ጊዜ፡ ከኢያሱ** ጋር **አገቡአት** እስከ **ዳዊት ዘመንም** ድረስ **ኖረች፤**
>
> **እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቶ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያን ያገኝ ዘንድ ለመነ።**
>
> **ነገር ግን ሰሎሞን ቤት ሠራለት።**
>
> **ነገር ግን ነቢዩ እንዳለው፡ ልዑል የሰው እጅ በሠራችው አይኖርም፡**
>
> **ሰማይ ዙፋኔ ነው፡ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ ለእኔ ምን ዓይነት ቤት** ትሠራላችሁ? **ይላል ጌታ፡ ወይስ የማርፍበት ስፍራ ምንድር ነው?**

68 ስለዚህ አሁን፡ "ማደርያ፡" ስንል... የምናርፍበት ስፍራ፡ ፍሬሽ የምንሆንበት፡ እንቅልፍ ተኝተን፡ ወዘተ፡ እፎይ የምንልበት፡ ወዘተ፡ ማለታችን ነው። እና፡ ዕብራውያን 10፡ ቁጥር 5 ላይ፡ ጳውሎስ እንዲህ ይገልጸዋል።

> **ስለዚህ ወደ ዓለም፡ ሲገባ እንዲህ ይለዋል፡ መሥዋዕትንና**... (ክርስቶስ ማለት ነው።)... **መስዋዕትንና መባን አልወደድህም፡ ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤**

69 አሁንስ ማደርያው ምንድነው? ስጋ ነው፡ እግዚአብሄር በስጋ ውስጥ አድሯል።

70 እግዚአብሄር፡ ከላይ ከክብሩ፡ ወደ ተራራው በወረደ ጊዜ፡ በሬም ቢሆን— ላም የተራራውን ጫፍ የሚነካ ሁሉ፡ ሊገደል ነበር። እግዚአብሄር ቅዱስ ነውና።

71 ትላንት ማታ እንዳልነው፡ እነዚያን መልዕእቶች ፊታቸውን ሲሸፍኑ። ቅዱስ ፊት ያላቸው ቅዱሳን ሱራፌሎች፡ ሐጥያት ምን ማለት እንደሆነ የማያውቁ፡ በእግዚአብሔር ፊት ግን፡ ፊታቸውን ይሸፍናሉ፡ እራሳቸውን በማዋረድ፡ እግራቸው ይሸፍናሉ።

72 ስለዚህ፡ ቅዱስ እግዚአብሄር ሐጥያትን አይታገሰምና፡ እግዚአብሄር የወረደበትን ተራራ መንካት የቻለ አልነበረም።

73 በኋላ ግን እግዚአብሄር እራሱ፡ ፍጥረቱ በሚሆነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በልጁ አምሳል፡ በእኛ ላይ አደረ። የእግዚአብሔር ህዋስ፡ ከደሙ ወጥቶ፡ ህይወት ይሆነን ዘንድ፡ ልጁ የገዛ ህይወቱን ሰጠን።

74 በዚያም በደሙ በኩል ታጥበናል። ስለዚህ አሁን ደማችን፡ በጾታዊ ምኞት የተገኘው፡ ህይወታችን፡ ወደ ዓለም አምጥቶናል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ግን አጠበን፡ መንፈስ ቅዱስ በመላክም፡ ባህርያችንን ቀየረው፤ በዚህም መለኮታዊ የእግዚአብሄር ባህርይ ተካፋይ በመሆን፡ የእግዚአብሄር ማደርያ አደረገን። ኢየሱስም፦ “እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፡ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።” አያችሁ?

75 እግዚአብሄር በቤተ ክርስትያኑ ውስጥ እንደሚኖር እወቁ። አሁን በዚህ ወቅት የክርስቶስ አገልግሎት ተቀብላ የምትሰራው፡ ቤተ ክርስትያን ናት። “በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገው እርሱ ደግሞ ያደርጋል። ገና ጥቂት ጊዜ አለ፡ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር ስለምሆን፡ በእናንተም ውስጥ ስለምሆን፡ ታውቁኛላችሁ።” አያችሁ? ስራውን የቀጠለው፡ በዚህ መልኩ ነው።

76 አሁን የተናገረን፡ እግዚአብሄር፡ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ፡ ነው። እስጢፋኖስ ስሎሞን ስለ ስራው መቅደስ ተናገረ፡ “ልዑል ግን የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም። ‘ሰማይ ዙፋኔ ነው፡ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት። ለእኔ ምን ዓይነት ቤት ትሠራላችሁ? ’ ‘ስጋን ግን አዘጋጀህልኝ።’” አሜን። ይሄውላችሁ።

77 “ስጋን ግን አዘጋጀህልኝ።” እግዚአብሄር በሰው ቁመና ውስጥ አድሮ፡ በዚያ አካል ውስጥ እራሱን ይተርካል። ፍጹም አምልኮ! የእግዚአብሄር ማደርያ ሆነን፡ እግዚአብሄር በእኛ ውስጥ አድሮ፡ ራሱን ሲገልጥ ነው። ኦህ፡ እዚህ በሙቀት እስክንታፈን ድረስ፡ በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ መቆየት እንችላለን። እግዚአብሄር፡ ከጥንት ጀምሮ፡ እራሱን፡ ሰው ውስጥ እንዳንጸባረቀ፡ አስተውሉ።

78 በሙሴ ውስጥ የነበረው እግዚአብሄር ነው። ተመልከቱት፡ መሪ ሆኖ ተወለደ፤ ክርስቶስ። ሙሴ በተውለደ ጊዜ የህጻናት ስደት ነበር፡ እሱንም ለመያዝ ፈለጉት፤ በክርስቶስም እንዲሁ ነበር። ሙሴ በዚያን ጊዜ——ተወለደ፤ ክርስቶስም እንዲሁ ነው። ሙሴ ሕግ-ሰጪ ነበር፤ ክርስቶስም እንዲሁ ነው። ሙሴ በተራራው ላይ፡ አርባ ቀናት ቆይቶ፡ ትዕዛዛቱን ተቀብሎ፡ ወረደ። ክርስቶስም ለአርባ ቀናት፡ በምድረ በዳ ቆየ፡ ተመልሶም መጣ፡ እንዲህ እያለ፡ “ለቀደሙት ‘አታመንዝር’ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን፡ እላችኋለሁ፡ ወደ ሴት ያየ ሁሉ፡ የተመኛትም፡ ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል።” አያችሁ? ሌሎች፡ እግዚአብሄር እራሱን፡ የተረከባቸው ብዙ ነገሮች አሉ።

79 ዮሴፍን እዩት፡ በብዙ ወንድሞቹ——መካከል መንፈሳዊ ልጅ ሆኖ ተወለደ። ሁሉም ጥሩ ሰዎች ነበሩ፡ ሁሉም አባቶች ናቸው። ነገር ግን፡ ዮሴፍ ሲታይ፡ የተለየ ሰው ነበር። ራእይ ያያል፣ ህልም ይተረጒማል፣ በዚህም ምክንያት በወንድሞቹ መካከል ተጠላ። ይሰራው ዘንድ እግዚአብሄር በምድር ላይ እንዲመጣ ባደረገው ስራ ምክንያት፡ ወንድሞቹ ጠሉት። አያችሁ? ነገሩ ሁሉ ወደ መስቀሉን ይጠቁማል። አሁንም፡ ተከታተሉ፡ በገዛ ወንድሞቹ፡ ወደ ሰላሳ

ብር በሚጠጋ ገንዘብ ተሸጠ። በገዛ ወንድሞቹ፡ ይሞት ዘንድ፡ ወደ ጉድጓድ ተወረወረ። ከጉድጓድ ወጥቶ፡ በፈርኦን ቀኝ ይቀመጥ ዘንድ ተወሰደ። በዚያን ዘመን ዓለምን ተቆጣጥሮ በነበረው ፈርኦን ፊት፡ በዮሴፍ በኩል ካልሆነ በቀር፡ ወደ ፈርኦን ሊገባ የሚችል፡ አንድም አልነበረም። አሁንም በክርስቶስ በቀር፡ ወደ እግዚአብሄር መግባት የሚችል ሰው የለም። ዮሴፍ ሲንቀሳቀስም፡ ከመነሳቱ በፊት፡ የሚነፋ መለከት ነበር፡ አጋፋሪዎችም በፊቱ ወጥተው፡ "ዮሴፍ እያለፈ ነው! ጉልበት ሁሉ ይንበርከክ!" እያሉ ይጮኻሉ፤ የትም ብትሆን፡ ወይም ምንም አይነት ስራ ብትይዝ፡ ስራህም ምንም አስፈላጊ ቢሆንም፤ ዮሴፍ እስኪደርስ ድረስ በጉልበትህ ትንበረከካለህ።

80 ዛሬ ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ ቀን፡ መለከት ይነፋል፡ ያኔ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡ ምላሰም ሁሉ ይመሰክራል። የኛ ዮሴፍ የሚሆን፡ ክርስቶስ፡ ከክብር ተነስቶ ሲወርድ፡ ያኔ ሰራህ ትርጉም አይኖረውም። ጉልበት ሁሉ ተንበርክኮ፡ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ይመሰክራል። ይህ እውነት ነው።

81 ኧረ፡ ዳዊት ላይም ማየት እንችላለን! ዳዊትም፡ በገዛ ወገኖቹ፡ በገዛ ልጁ፡ ከዙፋኑ ተጥሎ፡ የተናቀ ንጉስ፡ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ፡ ወደ ላይ ወጥቶ፡ ደብረዘይት ተራራ ላይ ሆኖ፡ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም መለሰና አለቀሰላት፤ ባገለገላቸው እና የእግዚአብሄርን መንገድ ባስተማራቸው፡ በገዛ ወገኖቹ፡ ተንቆ ተራራውን መውጣት በጀመረ ጊዜ፡ የገዛ ወገኖቹ ድንጋይ ይወረውሩበት ነበር፣ ይተፉበት እና ይሳለቁበት ነበር። ኦህ፡ ከሰምንት መቶ አመታት በኋላ፡ የእግዚአብሄር ልጅም እንዲሁ፡ በገዛ ወገኖቹ፡ እንደተናቀ ንጉስ ሆኖ፡ በተራራው ራስ ላይ፡ እንደተናቀ ንጉስ ቁጭ ብሎ፡ ኢየሩሳሌምን አለቀሰላት።

82 ይሄ ምንድነው? እግዚአብሄር በነብያት አልፎ እራሱን ማንጸባረቁ፡ ክርስቶስን ማንጸባረቁ ነው።

83 በኋላ ግን የእግዚአብሄር ፍጽምና የሆነው መጣ። እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ ሆነ።

84 ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፡ ከቀራንዮው በኋላ፡ እራሱን በቤተ ክርስትያኑ ውስጥ እየተረከ ይገኛል። ስለዚህ፡ እንደምታዩት፡ አሁን ሁላችንም ወደ ድንኳኑ፡ ወደ ሕያው የእግዚአብሄር ማደርያ ለመግባት እንታገላለን። በዚሁም ጥቂቶች…

85 እንደምናስተውለው፡ እንዲህ ብሎናል፦ "ከሁሉ በፊት እምነት፣ ትጋት፣ እውቀት፣ ጽናት፣ ትዕግስት፣ መልካምነት ወይም እግዚአብሄርን መምሰል፣ የወንድማማች መዋደድ አለን።" እሺ። ከወንድማማች መዋደድ በኋላ፡ ፍቅርን ጨምሩ። በደንብ እንድትረዱት፡ ሙሉውን፡ በድጋሚ፡ ላንብበው። አሁን ከቁጥር 5 እንጀምራለን።

**ስለዚህም** ምክንያት፡ **ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ፡ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፡ በበጎነትም እውቀትን፡**

**በእውቀትም ራስን መግዛት፡ ራስንም በመግዛት መጽናትን፡ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፡**

**እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፡ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን** ጨምሩ።

... **እነዚህ ነገሮች፡ ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና** ፍሬ **ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና።**

86 አሁን ጴጥሮስ፡ እንዴት ወደዚያ መድረስ እንደምንችል፡ ዝርዝሩን አስቀምጦልናል።

87 አንድ ነገር ልንገራችሁ፡ ክርስትያን ሳይሆኑ፡ ትጋት፣ እውቀት፣ ጥበብ፣ ትዕግስት፣ ወዘተ ሁሉ፡ በከፊል ያላቸው ሰዎች አሉ። የምናደርገው ነገር... የስንበት ትምህርት እየተማማርን ነው። ይህም እውነት ነው። ክርስትያኖች ሳይሆኑ፡ ከዚህ ነገር ግን በከፊል ያላቸው ሰዎች አሉ። ይህ ማለት ግን... አገኙት ማለት አይደለም። የፒኮክን ላባ በላይዋ ስካክታ፡ ፒኮክን ለመምሰል እንደምትጣጣር እንደ ጥቁር ወፍ ናቸው። እራሱን ብቻ ያዋርዳል። ጥቁር ወፍ ቢሆን ይሻለው ነበር። እያችሁ? ክርስትያን ሳይሆን እነዚህም ለመሆን የሚሞካክር ሰው፡ መንገድ እንደሳተ ነገር ብቻ ነው።

88 አፕልን ለመፈብረክ የሚጣጣር የሾላ ዛፍ ነው። እያችሁ፡ ዛፍ ስለሆነ ብቻ፡ አይሆንለትም። የአፕልን ፍሬ ሊፈበርክ አይችልም።

89 የበግ ጠጉርን ለመፈብረክ እንደሚሞክር በቅሎ ነው፡ በቅሎ ሆኖ ሳለ፡ የበግ ጠጉር፡ ወይም በግ ለመሆን የሚጥር በቅሎ ነው። እያችሁ፡ የበግ ጠጉር መፈብረክ አይችልም። አይሆንለትም። የበግ ጠጉር የበግ ስጦታ እንጂ፡ የበቅሎ አይደለም። በግን ለመምሰል ይታገላል እንጂ፡ በቅሎ መሆኑ የማይቀር ነው። እያችሁ? እና፡ "ይኸው፡ እንደ በግ እግጣለሁ። እንደ በግ **እንዲህ** አደርጋለሁ፡" ሊል ይችላል። ምንም ብታደርጉ፡ የበግ ጠጉር ለማብቀል በግ መሆን ይጠበቅባችኋል።

90 እስኪ ለትንሽ ደቂቃ እዚህ ጋር ላቁም። በግ የበግን ጠጉር አይፈበርክም። በግ ስለሆነ የበግ ጠጉር ይኖረዋል እንጂ። ብዙ ሰዎች "ይኸው፡ ጥሩ ለመሆን እተጋለሁ። **ይሄን** ለመሆን እተጋለሁ፡" ማለት ይሞክራሉ። ፈጽማችሁ ለመፈብረክ አትሞክሩ። በፍጹም፡ አይሳካላችሁም። በግን፡ የበግ ጠጉር እንድትፈበርክ የሚጠይቅ እና የሚጠብቅ የለም። ዝም ብላ የበግ ጠጉርን ታበቅላለች፡ ይህን የምታደርገው ግን በግ ስለሆነች ብቻ ነው።

91 እናንተም ክርስትያን ስትሆኑ፡ የመንፈስ ፍሬ ታፈራላችሁ። እንጂ—አትፈበርኩትም። ለማስመሰል አትሞክሩም። በሙከራ... ያልሆናችሁትን ነገር እንደሆናችሁ አትሁኑ። እናንተ መሆን የሚገባችሁ ብቻ ትሆናላችሁ፡ ሌላው ነገር በራሱ የሚመጣ ነው። አንዳንድ ሰዎች፡ "ይኸው፡ ከዛሬ ጀምሮ ነግሬአችኋለሁ። እኔ... የቤተ ክርስትያን ሰው ነኝ። ከአሁን በኋላ—መዋሸት አቆማለሁ" ሲሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? አሁንም፡ ያልሆነ ነገር ለመፈብረክ እየሞከራችሁ ነው። አይሆንላችሁም፡ ሙከራ አያስፈልጋችሁም፡ ይሄም—በቅሎ የበግን ጠጉር—ለማብቀል ከመሞከር አይተናነስም። አይሆንለትም።

92 ወይም፡ ጥንብ አንሳ ከእርግብ ጋር አብሮ ለመብላት መሞከር፣ ጥንብ አንሳ—ጥንብ አንሳ እርግብ ለመሆን መሞከር። አባኮዳ ጥቂት ላባዎች ሰካክቶ፡- "እያችሁኝ፡ እኔ'ኮ እርግብ ነኝ፡" ሲል፡ እስኪ አስቡት፡ "እያችሁ፡ እንዲህ እመስላለሁ... " ቢል፡ እያችሁ? ቅርጹ ሁሉ ይወላገዳል። ይህ

ማለት—እንዲሁ ሳይሆን እንዲህ ነኝ ብሎ የሚናገር ሰው እንደማለት ነው። እያችሁ፡ አይሆንላችሁም።

93 እንዲህ ማለት አትችሉም፡- “አሁን እዩኝ፡ በጎነት ይኑራችሁ ተብያለሁ፡ በጎ እሆናለሁ። እግዚአብሄርን በመምሰል ኑር ተብያለሁ፡ እንዲሁ እሆናለሁ ማለት አትችሉም።” ለምን፡ ላባዎችን ለመሰካት እየጣራችሁ ብቻ ነው። ማድረጉ ቀላል ቢሆንም፡ የሌላ ወፍ ላባ በሌላ ወፍ ላይ ማጥለቅ አይቻልም። ገባችሁ? አይሰራም። በጣም ግብዝ ወፍ እንደሆነች ብቻ ያሳያል። ገባችሁ? ያረጀ አባኮዳ፡ ሁለት የእርግብ ላባዎች ሰክቶ፡ “እዩኝ፡ እያችሁኝ፡ እርግብ ነኝ” ሲል እስኪ አሰቡት? እያችሁ? ለምን፡ አባኮዳ እንደሆነ ሁላችንም ሰለምናውቀው። አይደል´ዴ? አይደል? በቃ። አባኮዳ መሆኑ አውቀናል።

94 ይህው፡ አሁን ያለው ነገር፡ ክርስትናን—ለመፈብረክ መሞከር ነው። አይሠራም። ከሁሉ በፊት መሆን ያለባችሁ፡ ዳግም መወለድ ነው። መቀየር አለባችሁ። እያችሁ? ስትቀየሩ፡ አዲስ ፍጥረት ትሆናላችሁ። አሁን እየገባችሁ ነው፡ አይደል። እያችሁ? እናንተ ሰለላባዎቹ መጨነቅ አይገባችሁም፡ ዳግም—ስትወለዱ፡ በራሱ ያድጋል። አዎን፡ ያድጋል።

95 ሁሌም እንደምላችሁ። አሳማን—ይዛችሁ፡ በደንብ አጥባችሁ ታክሴለር፡ ወይም፡ ቶክሲዶ ሱፍ፡ አልብሳችሁ፡ ብትለቁት፡ ሮጦ ጭቃ ውስጥ ዘሎ ይዋልላል። ምክንያቱ፡ አሳማ ነው። ምንም አይጠቅመውም። ባህርይው ነው። ጭቃ ውስጥ መንደባለል፡ ባህርይው ነው። ከሁሉ በፊት ባህርይው መቀየር አለባችሁ፡ ሌላው (በራሱ) ሰራውን ይሰራል።

96 አሁን፡ ተከታተሉኝ። ዳግም መወለድ አለባችሁ፡ ማለት፡ መቀየር አለባችሁ። ለውጥ መኖር አለበት።

97 እናንተም፡- “ይሄውልህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ይህችን ሴት እኔ አውቃታለሁ፡ ልንገርህ፡ በጣም መልካም ሰው ናት። ክፉ ነገር አድርጋ አታውቅም። ወይም፡ **እከሌ-እና-እከሌ** የተባለው ሰው፡ መልካም ሰው ነው። ምንም እርጎ እያውቅም። ታውቃለህ ማንንም ጎድቶ እያውቅም።” ይሄ ምንም አይነት ዋስትና አይሆንም። ጥሩ ጎረበት ሊሆን ይችላል፡ ዳግም እስኪወለድ ድረስ ግን ክርስትያን አይደለም።

98 ኢየሱስ “ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡” አለ፡ ዮሃንስ 3 ላይ፡ “የእግዚአብሄር መንግሰት ማየት አይችልም፡” ብሏል። አሁን፡ **ማየት፡** ማለት፡ “መረዳት” ማለት ነው።

99 የሆነ ነገር አይታችሁ፡ “እኔ አልታየኝም፡” ትላላችሁ። አልገባኝም ማለታችሁ ነው።

100 ፍጥረታዊ ሰው ሰዎች ለምን እንደሚጮኹ አይረዳውም። ፍጥረታዊ ሰው ሰዎች እንዴት ቋንቋቸው ተቀይሮ በልሳን እንደሚናገሩ አይረዳውም። ፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሄር ክብር በሰው አይን ላይ ወርዶ፡ ራዕይ እንደሚገለጥ እና ለሰዎች ማድረግ የሚገባቸው መናገር እንደሚቻል፡ ልክ ጌታ፡ ትላንት ማታ ለእኛ ያደረገው አይነት ነው፡ ሊሆኑ ያላቸው ነገሮች፡ የሚፈጸሙ ነገሮች እንደሚናገር እያውቀውም። እያችሁ? እያችሁ? በፍጥረታዊው አእምሮ—ሊመረምር ይጥራል። “እንዴ፡ ምን እያለ ነው? ወይም፡ ምን አይነት ሰልት ተጠቅሞ ነው? ምን አይነት ማታለያ ነው? ” እንድ ሰው በልሳን ተናግሮ፡ ሌላው

ሲተረጉም... ወይም ሰዎች ያደረጉትን ነገር፡ ወይም ማድረግ የማይገባቸው ነገር በዝርዝር ሲነግራቸው። አያችሁ? አያችሁ? የሆነ ማታለያ ይመስላቸዋል። “በውስጥቸው የተከለባቸው ነገር አለ።”

101 ያ ሰው ዳግመኛ እስኪወለድ ድረስ ሊረዱት አይችሉም። ዳግመኛ ሲወለድ ግን፡ አዲስ ፍጥረት ስለሆነ፡ በኅብረት መስመር ውስጥ ነው። በጥርጣሬ የተሞላው፡ ባለ ሁለት ልብ ያረጀ ማንነት፡ ሞቷል። አሁን፡ አዲስ ፍጥረት ነው። ስለዚህ፡ እስተውሉ፡ አሁን ላለበት ቁመና፡ የሚጨምርበት ነገር የለውም፡ በራሱ ቅጽበት ይሞላል።

102 ዳግም መወለድ እንዳለባችሁ፡ እወቁ። ዳግም ስትወለዱ ግን፡ ያለ እምነት ዳግም አትወለዱም። ይህ እውነት ነው። ስለዚህ፡ ስንጠረዥ ላይ፡ እንደምትመለከቱት፡ እምነት የሁሉ መሰረት መሆኑን፡ አስቀምጬአለሁ። “ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና። ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ፡ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና። አይታቿል? ማመን አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምትጠራጠር ከሆንክ፡ ስለ ቃሉ እውነትነት የምትጠራጠር ከሆንክ፡ እምነት እስኪኖርህ ድረስ ወደ ኋላህ ብትል ይሻልሃል።

103 ኃጢአት ምንድን ነው? አለማመን ነው። የሰውን ልጅ የሚቆጣጠሩት ሁለት አካላት ብቻ አሉ። እምነት ወይ ጥርጣሬ፡ ከሁለቱ አንዱ ናቸው። ከሁለቱ መካከል ህይወትህን በሚወርሰው በአንደኛው ትሞላለህ። ምን ያህል እምነት አለህ፡ ምን ያህል መዘርጋት ትችላለህ ይወስነዋል።

104 ከሁሉ በፊት ግን፡ እምነት፡ መኖር አለበት። እስቲ መሰረቱ ላይ ትንሽ ጊዜ ልውሰድ። እምነት፡ የግድ የሚታመን ነው። እምነት ማለት... “እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ ነው።” ነገሮች በእምነት ስለሚገለጡ፡ እምነት ካለህ፡ ደርሰህበታል ማለት ነው። “እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፡” ዕብራውያን 11፡ ላይ፡ “ማስረጃ ነው።” ምንድነው? ምንን አይነት ማስረጃ? ቅዱስ ማስረጃ።

105 ስለዚህ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ እግዚአብሄር ፈዋሽ እንደሆነ አምናለሁ፡” ስትሉ። እንደ ፈዋሻችሁ፡ አምናችሁት፡ እርሱን ስትቀበሉት፡ ሳትዋሹ፡ በመገረፉ ቁስል እንደተፈወሳችሁ ስትቀበሉት፡ ሊቋቋማችሁ የሚችል ኃይል አይኖርም። የጸና ነው። ምናልባት **ይሄን** በመጠራጠር **ያንንም** በመጠራጠር፡ ተስፋ ብቻ ሊኖራችሁ ይችላል። እምነት ካላችሁ ግን፡ ማስረጃ ስለሆነ፡ እውቀቱ ይኖራችኋል። ደርሳችሁበታል። ዛሬ...

106 ኦራል ሮበርትስ ማለዳ ላይ ሲሰብክ፡ ያዳመጠ ሰው አለ፡ እስቲ፡ ካላችሁ፡ የኦራል ሮበርትስን ስብከት ያዳመጣችሁ ካላችሁ? አንድ ነገር ሲናገር ሰምቼዋለሁ—የነጻ መውጣት እምነት፡ እንደሚደረግ፡ ነጻ የመውጣት፡ የእምነት ጸሎት እንደሚጸልይ ሰምቼዋለሁ። “እንድትፈወሱ... ራድዮውን በመንካት ተገናኙት፡ ወይም የሆነ ነገር በመንካት ተገናኙት፡” ሲል ነበር። ሰውዬው ይሄን የሚያደርገው፡ ሰዎች የሆነ ነገር መንካታቸውን እንዲሰማቸው ለማድረግ ያክል ነው። “ራድዮውን ንካ ብሎኛልና፡ አሁን ሆነልኝ። ተፈወስኩ፡” የሚያስብላችሁ፡ አንድ ነገር ለመፍጠር ነው። አያችሁ? ይህም፡ ይሁን። ነገር ግን፡ ትክክለኛው እምነት፡ ቁሳቁስ መንካት አይጠይቅም። ወንድም ኦራልን መቃወሜ አይደለም፡

በፍጹም። ታላቅ ስራ የሚሰራ፡ የእግዚአብሄር ሰው ነው፡ ስለ ኦራል ሮበርትስ——አብዝቼ እሰባለሁና። እንደሱ ያሉ ሰዎች በበዙልን እላለሁ።

107 እኔ ለማለት የፈለግኩት፡ እምነት——ሌላ ነገር አያስፈልገውም። አያችሁ? እምነት የእግዚአብሄርን ቃል ማመን ብቻ ነው። እምነት "በመንካት" ነውን? አይደለም። "እምነት ከመስማት ነው፡ መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው።" ይሄ ያጸናዋል። እዚህ ጋር ነው። አያችሁት? እንደሚባለውም፡ እምነት፡ ገደብ የለውም። እምነት አሁን ነው። እምነት እዚህ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው...

108 የበቀደምለቷ፡ ህጻን ልጅ። እነ እህት ኪድ ያነጋገሯት እናት፡ የሆድ እቃዋ ወደ ውጭ ሆኖ፡ ምግብ ማስተላለፊያው ሬክተም፡ ዝግ የሆነ ህጻን የወለደች እናት። አሁን ይህች ሴት፡ እህት ኪድ እና ሌሎች ወንጌልን ሲሰብኩ፡ ሰምታ፡ እኔ ለህጻኗ እንድጸልይላት፡ ከእኛ ጋር ለመገናኘት አመነች። አያችሁ፡ እግዚአብሄር፡ ሰዎችን ሰጥቶናል...

109 አንዳንዶቻችን——እግዚአብሄር እዚህ እንደሚራመድ ያክል፡ ከወንድም ነቪል ጋር እንደማውራት፡ ወይም፡ ከሰው ጋራ እንደመቀራረብ ያክል ከእግዚአብሄር ጋር ልምምድ ያላቸው ሰዎች አሉን። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ አይነት ሰዎችን እንዲጸልዩልን እጠይቃቸዋለን። ማድረግ ያለብንም እንዲህ ነው። እምነት ካለን፡ የትም ቦታ ሆኖ የሚጸልይልን ወንድም ይሁን ሴት፡ ከእግዚአብሄር ጋር ይነጋገራል፡ እምነታችንም ይቆራኛል። ተጣብቋል። ተረጋግጧል።

110 አንዱ። ሮማዊው ኢየሱስን ለመገናኘት ወረደና። እንዲህ አለ፡- "ከጣርያዬ——በታች ትገባ ዘንድ አይገባኝም። ለእኔ——አይገባኝም። እኔ——ለዚህ አልበቃም። እራሴን——ብቁ አላደርግም... ስለራሴ——እንደሚበቃ አልቆጥርም። ግን፡" አለ፡- "ልጄ እጅግ ታሟል። አንተ ቃል ብቻ ተናገር፡ ልጄም፡ ይፈወሳል።"

111 ይሄ ምንድነው? ርቀት ልዩነት አይፈጥርም። ለምን? እግዚአብሄር፡ በሁሉ ቦታ የሚገኝ ስለሆነ። እግዚአብሄር ሁሉን ቻይ ነው። እግዚአብሄር ሁሉን ቻይ፡ በሁሉ የሚገኝ አምላክ ነው። እግዚአብሄር፡ በሁሉ ከሆነ፡ እግዚአብሄር፡ ሁሉም ጋር ይገኛል። አያችሁ? እግዚአብሄር አሁን እዚህ እንዳለ ሁሉ፡ በዚህ ቅጽበት፡ በጀርመን፣ በስዊዘርላን፣ በአፍሪካ ውስጥ ታላቅ አምላክ ነው። ኦህ! ይሄው ነው።

112 ሮማዊው "ከጣርያዬ በታች ትገባ ዘንድ አይገባኝም። ቃል ብቻ ተናገር፡" አለው። ያ ምን ነበር? የአንድ ሮማዊው እምነት ነበር። አመነው።

ኢየሱስም "በሰላም ሂድ፡ ልጅህ በህይወት ይኖራል።" አለው።

113 ከዚያ በኋላ፡ የሁለት-ቀን ጉዞ ተጓዘ። በሚቀጥለው ቀን፡ ቤቱ ሲደርስ፡ ከአገልጋዮቹ አንዱ መንገድ ላይ ተገናኘው። "ልጅህ በህይወት አለ፡" ብለው ነገሩት።

114 ሮማዊው ሰው፡ እጅግ ተገርሞ ጠየቃቸው፡ "በስንት ሰዓት ላይ ህመሙ ለቀቀው? በቀኑ በይትኛው ክፍለ ጊዜ? "

"በአስራ አንደኛው ሰዓት፡ ተሻለው፡" ብለው መለሱለት።

115 ኢየሱስ፡ “ልጅህ በህይወት ይኖራል፡” ብሎ የነገረው ሰዓት እንደሆነ ሮማዊው አወቀ። አሜን።

116 ሁሉን ቻይ፣ በሁሉም ቦታ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ ማለቂያ የሌለው፣ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ፡ ስልክ ደውለው “ጸልይ!” ሲሉኝ፡ ያ ልመና! እና እምነታችሁ እግዚአብሄርን እንዲወርድ ያደርገዋል። ጸሎት እና እግዚአብሄር፡ በአንድነት ወደ ሰፍራው፡ እንዲመጡ የሚያደርጋቸው ነገር ይህ ነው። ጸሎት! እምነትን **ወዲያ** እና **ወዲህ** ያነቃንቀዋል። ወደ አንድነት ያመጣዋል።

117 “ቃል ብቻ ተናገር። ፍላጎቴ ቃል ብቻ ከአፍህ እንዲወጣ ነው፡ ሌላ ሁሉ ትክክል ይሆናል።” አይታችኋል፡ በሰፍራው መገኘት አይጠበቅበትም። “ቃል ብቻ ተናገር።” ለምን? እግዚአብሄር በሁሉ ቦታ ስለሚገኝ። ኃያል-ነው። ከታች በምድር በታች ኃያል እንደሆነ ሁሉ በሰማያትም፡ ወይም በሁለቱም ኃይለኛ ነው። አምላክ ነው። “ቃል ብቻ ተናገር ይህ ብቻ አድርግ፡” አለው።

118 ሌላው፡ እምነት ራሱ፡ የሚያደርገው ነገር ነው። ሌላው እምነት ያደርገዋል። ስለዚህ እምነትን መሰረታችሁ አድርጉት። ክርስትና በአጠቃላይ፡ እናንተንም ጨምሮ፡ የምትሆኑትን ሁሉ፡ በቃሉ ላይ ባላችሁ እምነት የተመሰረተ ነው። እኔ ቃልን የማምንበት ምክንያት ይህ ነው። ተረዳችሁኝ?

119 እምነቴን በሌላ በማንም ላይ ማድረግ አልችልም። በቤተ ክርሰትያን ላድርግ ብል፡ በየትኛይቱ ቤተ ክርሰትያን አደርገዋለሁ፤ ካቶሊክ፣ ሉተራን፣ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ጴንጤቆስጤ? የትኛው ላይ አሳርፈዋለሁ? እንጃ። እነዚህ ሁሉ ግራ የተጋቡ ምናምንቴ፡ መሰመራቸው ጠማማ፡ የሆኑ ወዘተረፈ ናቸው።

120 እምነቴን በቃሉ ላይ ካደረግኩት ግን፡ የጸና ይሆናል። ማንም አይተረጉመውም። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ነውና። መሰረቱ ይህ ነው። እኔም ይሄን አምናለሁ።

121 ጥሩ ዶክተር እዚህ ከተማ ውሰጥ የሚኖር፣ ጓደኛዬ፣ ዶክተር ሳም አዲር ይባላል። ከህጻንነታችን ጓደኛሞች ነን። ሳምን ሁላችሁ ታውቁታላችሁ። እና እንዲህ አለኝ፡ “ቢል፡” አለኝ… ቦታውን የት እንደሚገነባ፡ እና ምን እንደሚመሰል፡ ራእይ አይቼ ከነገርኩት በኋላ። እውነትነቱን ማረጋገጥ ከፈለጋችሁ፡ ሄዳችሁ እሱን መጠየቅ ትችላላችሁ። የት እንደሚሆን፡ ከሁለት ከሶሰት አመታት በፊት ነግሬዋለሁ። “አንድ ሰፈር የሚያክል ቦታ ትቀበላለህ፡” ብዬዋለሁ። ከማገገሚያው ማዕከል በቀር፡ እንደተባለውም በሱ እና በዚያ መካከል ሌላ ነገር የለም። ከመድሃኒት መሸጫው ጋር፡ ሁሉንም ተቀብሏል። ይሄው ነው። ዶክተር አዴር፡ ራእዩ በትክክል አሟልቷል። ሰለቦታው፡ ሲናገር “በኃያ-አምሰት አመታትም አያልቅም። በፍርድ ቤት ተይዟል፡” አለኝ።

122 “ዶክተር፡ በትህትናህ ምክንያት፡ ጌታ ለአንተ ሰጥቶሃል፡” አልኩት።

“እኔ ጥሩ ሰው አይደለሁም፡” አለኝ።

123 እኔም፡- “አዎን ኤሊ ነህ። ከውጭ ከባድ ቅርፊት አለብህ፡ ጓደኞችህ የምትመለከትበት አለት አለብህ፡ ውሰጥህ ግን ትክክለኛ ሰው ነህ። ከቅርፊትህ ውሰጥ ውጣ።” “እግዚአብሄር አሳልፎ ሰጥቶሃል፡” አልኩት።

124 "ቢሊ፡ ከዚህ በፊት ተጠራጥሬህ አላውቅም፡ ይሄን ግን እጠራጠራለሁ፡" አለኝ።

"ወደ ቢሮህ ሂድ፡" አልኩት። እርሱም ወድያው ሄደ።

125 በነጋታው፡ ደውሎ፡ "እስክሞት ድረስ በርዶኛል፡" አለኝ።

126 ሐምሌ ነበርና፡ "ምነው ምን ገጠመህ?" አልኩት። "ምን ሆንክ ዶክተር?" አልኩት፤

127 እርሱም፡- "ቦታውን ገዛሁት አለኝ። ትላንት ማታ ቦስተን ላይ ስብሰባ አድርገዋል፡ ዛሬ ጠዋት እኔ ገዛሁት።"

"ነግሬኃለሁ፡" አልኩት።

128 ባለፈው ቀን ጠመንጃው ፊቴ ላይ በፈነዳ ጊዜ፡ ሄጄ ነበርና፡ እየተጫወትን ነበርን። "ይመስለኛል፡ ወደዚህ ለመጣ ሰው ሁሉ፡ ነገሩን ተናግሬአለሁ፡" አለኝ። ምን ማለት ነው? ይህ ማለት፡ እግዚአብሄር አንድ ነገር ሲናገር፡ መፈጸሙ አይቀርም።

129 ባለፈው ምሽት አንዳንድ ጓደኞቼ መጥተው። ስለ ባለ አርባ-ሁለት-ኢንች ካሪቡ እና፡ ስለ ሲልቨር-ቲፕ ግሪዝሊ ድብ የተነገረውን ራእይ ሰምተው ነበርና መጡ። ስንቶች ሰዎች ወደ ቤታችን እንደመጡ አላውቅም፡ ብዙዎች ማየት ይፈልጋሉ። "እና መለኪያው ገመድ እንካ። ቀንዱን ለካው፡" አልኩት። ከመፈጸሙ በፊት ሰምቶት ነበርና። አያችሁ? ለምን? እግዚአብሄር ከተናገረ፡ መፈጸሙ አይቀርም። መሰረት አለው፡ ምክንያቱም እሱ ነው።

130 እንግዲህ፡ የመዳን እቅድ **እንደሚከተለው** ነው። ከዚያ በኋላ ራእዩ በትክክል ሲፈጸም፡ ይሆናል በተባለበት መንገድ ሲፈጸም፡ ቤተክርስትያኒቱ እውነት እንደሆነም ታውቃለችና፤ ቃሉስ? አያችሁ? ቃሉ'ማ ከራእዩ ይልቅ እንኳን የተረጋገጠ ነው። ራእዩ ከቃሉ ጋር ካልተስማማ፡ ራእዩ የተሳሳተ ነው። ከሁሉ በፊት ግን፡ ቃሉ፡ ነው፡ ቃሉ እግዚአብሄር ነውና። ገብቷችኋል? ስለዚህም በሁሉ ቦታ ይገኛል። እዚህ ሆኖ የተናገረው ራእይ፡ ካናዳ ውስጥ ተፈጸመ። አሜን። እርሱ፡ በሁሉ ቦታ ይገኛል። በጣም ጥሩ።

131 በመጀመሪያ ዳግመኛ መወለድ አለብህ። ከዚያም ዳግመኛ ስትወለድ፡ እምነት ይኖርሃል፡ ቃሉን ታምናለህ። ዳግመኛ እስክትወለድ ድረስ ግን፡ ትከራከራለህ። ሐይማኖተኛ ከሆናችሁ፡ እኔ የምሰራው ሁሉ—ትክክል ነው የሚል የተወሰነ—የሰው—እውቀት ያላችሁ ከሆናችሁ፡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ መስማማት ፈጽሞ አትችሉም። ፈጽመህ አትችለውም። እንደገና መወለድ አለብህ። ዳግመኛ መወለድ ደግሞ፡ እምነትን፡ ይፈጥራል። እሺ። ከዚያ በኋላ፡ **እንደዚህ** እምነት፡ ኤፍ-ኤ-አይ-ቲ-ኤች፡ እምነት ሲኖራችሁ፡ ያኔ ወደ እድገትን ጎዳና ትገባላችሁ።

132 ብዙ ሰዎች፡ ወደ መሰውያው ቀርበው፡ ይጸልያሉ፡ "ጌታ ሆይ፡ ይቅር በለኝ፡" ይላሉ። በዚህም ምክንያት ታላቅ የሆነ የቅድስና፡ እና ሌሎች ነገሮች ልምምድ ይጀምርባቸዋል። ስለዚህ ወደ መሰውያው ቀርባችሁ፡ የምትጮኹበት፡ ታላቅ ጊዜ ታገኙና። መጥታችሁ፡ "ጌታ ይመስገን፡ አሁን አገኘሁት፡" ትላላችሁ። አይደለም፡ ማደግ የምትጀምሩበት መልካም ስፍራ

ውስጥ መግባት ጀምራችኋል ነው። ገና ምንም አልሰራችሁም። አያችሁ? ያደረጋችሁት ብቸኛው ነገር መሰረትን መሰርታችኋል ነው።

133 ቤት ልትገነቡ ነው፡ ስለዚህም መሰረት መሰርታችሁ፡ "ወዳጄ፡ አገኘኋት፡" ትላላችሁ። አያችሁ? ቤታችሁን የምትገነቡበት መሰረት ብቻ መሰርታችኋል። ቀጥላችሁ ቤት ማነጽ ይጠበቅባችኋል።

134 የዛሬ ማለዳው ቁምነገር የሚጀምረው፡ በዚህ ነው፡ አሁን እንነጋገርበታለን። በጣም ጥሩ። ቤት ሰናሰብ፡ ቀዳሚው ነገር መሰረት ነው። የክርስትና መሰረቱ ምንድነው? በእግዚአብሄር ቃል ያለን እምነት ነው። መሰረታችሁ ይህ ነው። ከዛ ጀምራችሁ ታድጋላችሁ። ከዛ በኋላ መሰረቱ ላይ መጨመር፡ ትጀምራላችሁ።

135 ቤት፡ ሲገነባ፡ ከሁሉ በፊት ኮለናችሁ እና ሌላው አስፈላጊ ነገር ሁሉ ታቆማላችሁ። ወንድም ዉድ እና እዚህ ያሉ የእንጨት ስራ ባለሞያዎች እና ኮንትራክተሮች ቤት እንዴት እንደሚታነጽ ሊነግሩን ይችላሉ። አያችሁ? እኔ ግን እግዚአብሄር የሚያድርበት መንፈሳዊ ቤታችሁ፡ እንዴት እንደምትሰሩ እነግራችኋለሁ። በውስጣችሁ ማደር ይፈልጋል። እናንተ እሱን እንድትመስሉ ይፈልጋል። ሰብእናውን፡ እንዲንጸባረቅ፡ ወይም እንዲንጸባረቅባችሁ ይፈልጋል።

136 ታውቃላችሁ፡ በድሮ ዘመን ወርቅ ሲሰሩ፡ ወርቅን ለማቃጠል ምድጃ ከማዘጋጀታቸው በፊት፡ ወርቁን እየደበደቡ፡ ዝቃጩን፡ ብረቱን እና መዳብን፡ እና እቃዎችን ለማስቀረት ይደበድቡታል፡ እያገላበጡ፡ መቀጥቀጥ ይቀጥላሉ፡ በደንብ ይመቱታል። ህንዶች እስከ አሁን ድረስ፡ ወርቅ ይቀጠቅጣሉ፡ ይቀጠቅጡታል። ዝቃጩን፡ ብረቱን እና መዳቡን፡ እና አላስፈላጊው ነገር ሁሉ መውጣቱን እንዴት እንደሚያውቁ ታውቃላችሁን? ቀጥቃጩ፡ ምስሉን በመስታወት እንደሚያይ ሰው፡ ምስሉን በወርቁ ላይ ሲንጸባረቅ ማየቱ። ያኔ ቀጥቃጩን ለማንጸባረቅ ንጹህ እና ግልጽ ነው።

137 እግዚአብሄርም እንዲሁ ያደርጋል። ከምድር ያገኘውን ወርቅ ይዞ ይሄድና፡ ደጋግሞ እያገላበጠ፡ እያገላበጠ፡ እያገላበጠ የገዛ ምስሉ እስኪንጸባረቅ ድረስ ምስሉን (እስኪያይ ድረስ) በመንፈስ ቅዱስ ይቀጠቅጠዋል። [ወንድም ብራንሃም አብዝቶ ደጋግሞ በእጆቹ አጨበጨበ—እርታዒ።]

138 የእግዚአብሄር ልጅ በውስጣችን እስኪታይ ድረስ፡ ልናደርገው የሚገባን ይህ ነው። ከዛ በኋላ ስራውን መሰራት እንችላለን። እርሱም እንዳለ፦ "በእኔ የሚያምን... " ዮሃንስ 14:7 ላይ፣ "በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገው ስራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ብሏል።" የክርስቶስን ስራ ማንጸባረቅ እየጀመራችሁት ነው።

139 ብዙዎቻችን ግን የክርስቶስ ምስል በውስጣችን መታየት ከመጀመሩ በፊት የክርስቶስን ስራ ለመስራት እንሞክራለን። ችግሩም እዚህ ጋር ነው። እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ አይተናቸዋል። ታውቁታላችሁ። እኔም አውቃለሁ። በመንገዳችን እንደነዚህ ያሉ እንቅፋቶች፡ ይገጥሙናል። የክርስትያን አገልጋዮች ኮቴ በመንገዳችን ላይ ተቀርፎ፡ እና ተልጦ፡ ወዳድቆ ይገጥመናል፡ ይህም በትክክለኛው አካሄድ ስለማይሄዱ ነው።

140 ለዛም ነው ዛሬ ጠዋት እዚህ የመጣሁት፣ ይህችን ትንሽ ቤተክርስትያን፡ እና እራሴን፡ እንዴት የህያው አምላክ ማደሪያ መሆን እንደምንችል ለማስተማር ነው። ሰንቶች መሆን ትፈልጋላችሁ? የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያ!

141 አሁን የምናደርገው ነገር ይኸውና። የመጀመሪያው ነገር ምንድን ነው? እምነት ይኑርህ ዳግም ተወለድ። ይህም መሰረት መጣል ነው።

142 ከዛ፡ መሰረት ከጣልን በኋላ፡ መሰረታችሁ ላይ ሁለተኛው እርከን ጨመሩ። “በእምነት ላይ ጨምሩ፡” አለ ጴጥሮስ። በእምነታችሁ... ከሁሉ በፊት እምነት ነው፡ በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ጨምሩ። ቀጣይ እርከን ይህ ነው። አንደኛው፡ መሰረት ወይም እምነት፡ መጣል ነው። ከዛ፡ በእምነት ላይ፡ በጎነት ይጨመራል።

143 እያችሁ፡ ብዙዎቻችን የምንዘረረው እዚሁ ላይ ነው፡ አዎን፡ በትክክል። አዎን። “በእምነታችሁ ጨምሩ።” ይህ ማለት፡ እንደ ሴት ወይም እንደ ወንድ፡ የድንግልና ህይወት መኖር ማለት አይደለም፡ ወዘተ መኖር አይደለም። ያ ከዚህ ጋር ምንም አይገናኝም።

144 መጽሐፍ ቅዱስ፡ በሉቃስ መጽሐፍ ውስጥ፡ “በጎነት ከእርሱ ወጣ፡” የሚል ተጽፎ እናነባለን። ልክ ነው? እንደሱ የምንሆን ከሆነ፡ እንግዲህ፡ በጎነት ሊኖረን ይገባል። እሱን ለመሆን፡ ደግነት ሊኖረን ይገባል። መጀመርያ፡ ከታላላቅ መዝሙሮች አንዱ፡ ከዝማሬዎች ሁሉ—የወደድኩት፡ **እንደ ኢየሱስ መሆን**፡ የሚል ዝማሬ ነው። አዎን፣ እንደ ኢየሱስ የምሆን ከሆነ፣ በጎነት ሊኖረኝ ይገባል፣ ከእኔ አልፎ ለህዝቡ የሚሆን በጎነት ሊኖረኝ ይገባል። ምክንያቱ፡ “በጎነት ከእርሱ ወጥቶ ወደ ህዝቡ ገብቷልና።” በጎነት! ከእናንተ ውስጥ መውጣት ከመጀምሩ በፊት፡ በውስጣችሁ ሊኖር ይገባል። ከሌላችሁ ግን፡ አይወጣም። የሚወጣበት ምንም ነገር ከሌለ የለም።

145 አንድ ሰው በጎነትን ከውስጣችን ለማግኘት ፈልጎ፡ መዝገባችን ግን “ያሎት ቀሪ ሂሳብ አነስተኛ ነው” ቢልስ? እያችሁ? የለም፡ የለም፡ ምንም አይገኝብንም፡ መዝገባችን ባዶ ነው። አንድ ሰው እንደ ክርስትያን ቆጥሮአችሁ፡ በሚቀጥለው ቀን ከሐጥያት ጋር ስታብሩ ብያያችሁ፡ ያን ያህል በጎነት ሊቀዳባችሁ አይችልም። እያችሁ? አዎን።

146 በጎነት ሊኖረን ያስፈልጋል። በጎነት እስኪኖረን... እውነተኛ በጎነት ስናገኝ፡ በእምነታችን ላይ መጨመር እንችላለን። ሁለተኛው የመሠረቱ ግድግዳ ነው። በመጀመሪያ፡ እምነት ይኑራችሁ። እምነት ብቻውን ግን ምንም አያደርግም። ጴጥሮስም... እንዲህ ብሏል፡ “በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ጨምሩ።” በእምነት ላይ ለመጨመር፡ በጎነትን ልታገኙ ያስፈልጋል።

147 አሁን፣ ምናልባት፡ በጎነት ሊኖርህ ያልቻለበት፡ ምክንያት፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ዘመኑ ያለፈበት ነው፣ ወይም ምንም አያስፈልግህም ብለው ስለሚያስተምሩ ነው። “ምንም አይጠቅማቸውም። ዝም ብለህ የቤተክርስትያን አባል ከሆንክ ይበቃል። አዎን፡ ዘመኑ አልፎበታል።”

148 በጎነት፣ በጎነት የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ማንም ያውቃል፣ እያችሁ፣ ሊኖረን ይገባል። የታመመችውን ሴት ለመፈወስ፡ በጎነት ከእርሱ ዘንድ ከሄደ፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ተመሳሳይ በጎነት እንዲኖር ይጠብቃል፣ ምክንያቱም እርሱ ምሳሌአችን ነው። ለሰዎች የሚሰጥ በጎነት ከነበረው፡ ለሰዎች የምንሰጠው በጎነት እንዲኖረን ይጠብቅብናል። በጎነት ምንድን ነው? በጎነት ጉልበት፡ እና ኃይል ነው።

149 አንዳንዶቹ በእግዚአብሔር ኃይል እንኳን አያምኑም። ሲናገሩም፡- “ያ—ያ—ያ’ኮ ዘመኑ ያለፈበት ነው። ማድረግ ያለባችሁ ነገር ቢኖር ስማችሁን

በመጽሐፉ ላይ ማስመዝገብ፡ ከዛ በውሃ ተረጩ፡ ወይም ታጠቡ፡ ወይም ተጠመቁ፡ ወዘተ። ይሄን ብቻ አድርጉ።"

150 ጴጥሮስ ሲናገር ግን፦ "በጎነትን ጨምሩ" ብሏል። አሁን እዩት፡ ጴጥሮስ፡ የእግዚአብሔርን ቤት ስለመገንባት እየተናገረ ነው፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በአንድ ቦታ ላይ ለማቆም። ከበጎነት በኋላም፡ መጨመር አለባችሁ... ከእምነት በኋላ፡ በላዩ ላይ በጎነትን መጨመር። ትክክል ነው። ለአለም ሁሉ በጎነት ይኑራችሁ።

151 የዛሬ ሃያ አመት ገደማ አንድ ሰብከት ሰበክኩኝ፣ ይመስለኛል፣ በሬቨረንድ. አቶ. ሊሊ። ፓስተር፡ ሊሊ። ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ከተናገረበት ክፍል ወሰጄ፦ "ሊሊዎችን፡ ተመልከቱ አይዘሩም አያጭዱም። እውነት እላችኋለሁ፡ ሰለሞን በክብሩ ሁሉ እንደነዚህ ያህል አላጌጠም።"

152 ሊሊን ተመልከቱት። ከታች ከጭቃ ውስጥ ወጥቶ ያድጋል። ዘወትር በየደቂቃው ከምድር ይመጣል። አያችሁ? በጠጣው በጎነት ምን እና ምንን ያደርጋል? ውበቱን ያሳያል። ለሚያደንቁት ሁሉ መስህብ ይፈጥራል። ንብ መጥቶ ድርሻውን እንዲቀሰም፡ ለማር ራሱን ይከፍታል። እንድታካፍሉ፡ ተሰጥቷችኋልና። አታማርሩ። ንብ መጥቶ፡ ማር የለም፡ ያለዎት ቀሪ ሂሳብ አነስተኛ ነው ቢባልስ? ንቡ እራሱን እያከከ "ምን አይነት ሊሊ ነው? " ማለቱ አይቀርም፡

153 አንድ ሰው አብሮ መጥቶ፡ መዳንን ለማግኘት ቢሞክር፡ የተአምራት ዘመን አልፏል ብሎ ወደሚያምን ቤተ ክርስቲያን ቢሄድስ?

154 ጃክ ኮ በአንድ ወቅት እንደተናገረው። ወደ ሬስቶራንት ገብቶ፡ ባለ ብዙ የምግብ ዝርዝር ሜኑ አንስቶ፡ ቲ-ቦን ስቴኮችን እና ሌላ ሌላውን ዝርዝር አነብቦ። "ቲ-ቦን አምጡልኝ፡" ይላቸዋል።

"ይሄ፡ -ትላንትና ነበር። ዛሬ የለም ይሉታል።"

155 ከዚህ ሁሉ ሜኑውን ጥሎላቸው መውጣት ይሻላል፡ አይደል፡ አዎን፡ በመሰረቱ፡ ሌላ የሚበላ አይኖራቸውም። ስለዚህ የሚበላ ነገር ወዳለበት ሬስቶራንት መሄድ ይሻላል።

156 መንፈሳዊው ሰውም እያደገ፣ የሚበላው ነገር ያስፈልገዋል። ያ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉን ሁሉ እምናለሁ።

> እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ቅዱሳን የሚመገቡበት የተዘረጋ ገበታ አለው፡
> የተመረጠ ህዝቡን ይጋብዛል፡ "መጥታችሁ ብሉ ይላል።"
> መናውን ይመግበናል፡ የሚያስፈልገን ይሰጠናል፡
> ኦህ፣ ሁል ጊዜ ከኢየሱስ ጋር መመገብ ይጣፍጣል!

157 አዎን፡ ወዳጄ። በትክክል። በሱ ዘንድ ሁሉ ይገኛል። በክርስቶስ እውቀት፡ በፍጹም ሰው ህንጻ በተገነባች፡ በህያው የእግዚአብሄር ቤተክርስትያን ውስጥም አለ፡ ቤተ ክርስትያንም አላት። በጎነት ሊኖርህ፡ ያስፈልጋል።

158 እንግዲያው ልንገራችሁ፡ ከሁሉ በፊት ማወቅ ያለባችሁ፡ ሽቶ ማሽተት የሚወድ ሰው አለ። ሽቶ ስለተቀባ። ራስ ወዳድ አይሆንም። ማዓዛውን

ከማካፈሉ በፊት ግን፡ መቀባት አለበት። ማር ከመሰጠቱ በፊት፡ መያዝ አለበት። ውበት ከማሳየቱ በፊት፡ ውበት መኖር አለበት።

159 በጎነት ከመስጠታችሁ በፊት፡ በራሳችሁ በጎነት ሊኖር ይገባል። ስለዚህ፡ በእምነታችሁ ላይ፡ በጎነትን ጨምሩበት። አሜን። ገብቷችኋል? ብዙ ማለት እንችላለን፡ ጊዜ ግን ያጥርብናል። በእምነት ላይ በጎነትን ጨምሩ። ከሁሉ በፊት፡ እምነት፡ ከዛ በጎነት።

160 ከዛ፡ በሶስተኛ ደረጃ፡ እውቀት ጨምሩ። እውቀት ስንል ዓለማዊ እውቀት ማለት አይደለም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞኝነት ነውና፤ ነገር ግን መፍረድ የሚያስችል እውቀት፣ (ምን) መፍረድ? ስህተትን ከእውነት። ታዲያ፡ በበጎነታችሁ እና በእምነታችሁ የክርስትያናዊ እውቀት ከያዛችሁ፡ እንዴት ትፈርዳላችሁ? ቃሉ ትክክል ነው ወይስ ስሕተት ነው ትፈርዳላችሁ። አለማመናችሁ ሁሉ እና፡ አዋልዶቻችሁ ሁሉ፡ ሰራን ብላችሁ የምትመኩባቸው ነገሮቻችሁ ሁሉ ወደ ጎን ካደረጋችሁ፡ ያኔ እግዚአብሄር እንደማይዋሽ ታውቃላችሁ። “የሰው ቃል ሁሉ ውሸት፡ የእኔ እውነት ይሁን።” አያችሁ? እውቀትን ማግኘት ጀመራችሁ። ፍጹም እውቀት ይህ ነውና። እሱን ለማወቅ፡ ከኮሌጅ አራት ዲግሪ፡ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር ሊኖርህ አይገባም፡ እነዚህ ሁሉ በጎነቶች፡ ወደ እውነተኛው እና ወደ ሕያው የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ቁመና፡ እንድትደርሱ እና፡ በእምነታችሁ መሰረት ላይ እንዲገነቡ በእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው። አዎን፡ ወዳጄ።

161 የቃሉ እውቀት ይጨመር፡ ምክንያቱ፡ እውቀትን ጨምሩ። እንዲህ ማመን አለባችሁ። ማለት፡ ዛሬ… የተአምራት ዘመን እንዳላለፈ፡ ማመን እና መቀበል አለባችሁ። አደርገዋለሁ ያለውን ነገር፡ ጌታ መፈጸም እንደሚችል እውቀት ሊኖረን ይገባል ።

162 አብራሃም ይሄን አመነ። የመቶ ዓመት በሆነ ጊዜም፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ባለማመን አልተደናገረም። ያ ቃል ምን ያህል ቀልድ ይመስል እንደነበር ተመልከቱ። የመቶ ዓመት ሰው፡ ዘጠና ዓመት ከሆናት ሴት፡ በቤቱ ውስጥ፡ ሕፃን እንዲወለድ ይጠብቅ ነበር። አይገርምም? ከወጣትነት ዘመኗ ጀምሮ—ወይም፡ ከአሰራዎቹ ዓመቷ ጀምሮ፡ አብሯት ኖሯል፡ ሐምሳ አመት ገደማ ታገሰ። እነሆ አሁን፡ የህይወት ማመንጫው ሞቷል። የሳራ ማህጸንም ሙት ነው። ተስፋን በተመለከተ ሁሉ፡ ተስፋ ሁሉ አልቋል። በዚህ ሁሉ፡ ግን፡ ተስፋን በመቃወም፡ በተስፋ አመነ፡ የገባውን የተስፋ ቃል ሁሉ የሚፈጽም አምላክ መሆኑን የእግዚአብሄር እውቀት ነበረውና።

163 ስለዚህ፡ እንዲህ መሆኑን ስታውቁ፡ እንግዲያውስ በእምነታችሁ ላይ ጨምሩት። እውነተኛውን በጎነት ስታገኙ፡ በእምነታችሁ ላይ ጨምሩት። በጎዳናዎች ላይ ስትጓዙ፡ እንደ ክርስትያን ኑሮ ኑሩ፡ እንደ ክርስትያን ስራ ስሩ፡ ክርስትያኖች ሁኑ፡ ይህም ሁሉ እምነታችሁ ላይ ጨምሩት። እውቀት ስታገኙ…

164 እንዲህ እያላችሁ፡ “ይህ ቃል፡ ትክክል ይሁን አይሁን **ገና** አላወቅኩትም። ለምሳሌ የሐዋርያት ስራ 2፡38፣ ከሐዋርያት ስራ 28፡19 ጋር፡ እንዴት እንደሚያያዝ አላውቅም።” ይሁን። ገና ሳትረዱት፡ ምንም ነገር አት—አትጨማምሩ። ገባችሁ? ታድያ ምን ማድረግ ይገባችኋል? ስለ እግዚአብሄር ልታውቁት የሚገባችሁ በቂ እውቀት፡ ማለት፡ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርስ

እንደማይጋጭ፡ ገና ስላልተረዳችሁት። ዝም በሉ። ሌላ ቃላት አትናገሩ። ዝም በሉ። እሺ?

165 ነገር ግን ቅዱስ ቃል እንደማይጋጭ መረዳት ከጀመረችሁ፡ በእግዚአብሔር መገለጥም፡ የእግዚአብሔር ቃል በምስጢር እንደተጻፈ፡ማየት ከቻላችሁ፡ እና፡ መናገር ከቻላችሁ፡ የእግዚአብሄር እውቀት ብቻ ቃሉን እንደሚገልጥ ተረድታችሁ፤ እያንዳንዲ የእግዚአብሔር ቃል "በአሜን፡" ስርዓተ ነጥብ መዝጋት ስትጀምሩ፡ ያኔ በእምነታችሁ ላይ ጨምሩት።

166 ኦህ፡ ያኔ ያማረ ቁመና ያለው ሰው ትሆናላችሁ። አያችሁ? እያደጋችሁ ነው፡ አያችሁ። በምን? በእምነት፣ ከበጎነት ጋር፣ እውቀትን ጨምሮ። ይህ ሰው እንዴት እንደሚታነጽ አይታችኋል? ማምለጥ የሚቻልበት መንገድ እንደሌለ—ማየት ትችላላችሁ። ይህ በክርስቶስ ፍጹም ቁመና ውስጥ የመሆን መንገድ ነው። አዎን፡ ወዳጄ።

167 ስትፈርዱ፡ በቅን ፍረዱ። የእግዚአብሄር ቃል ለማመን፡ ስህተት ወይም እውነት እናንተ ፍረዱ። ስህተት ወይም እውነት፡ አዋልድን ወይስ እግዚአብሄርን የትኛው ማገልገል እንዳለብኝ ፍረዱ። ስህተት ወይም እውነት፡ ዳግም መወለድ ወይስ የቤተክርስትያን አባል መሆን፡ እናንተ ፍረዱ። ሰባኪው፦ "የተአምራት ዘመን አልፏል" ብሎ ሲናገር፡ ቅን ፍርድ ፍረዱ። መጽሐፍ ቅዱስ፦ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ እና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ድረስ ያው ነው፡" ይላል። እናንተ የትኛውን ታምናላችሁ?

168 "እግዚአብሄርን አምናለሁ፡" ስትሉ። ከልብ፡ ስለ ማለት ብቻ፡ "አዎን፡ እኔ—እኔ አምኛለሁ" አትሉም። ግን፡ የሆነ ነገር፡ እምነት ከውስጣችሁ ፈንቅሎ ያናግራችኋል። ይሄው ነው። እምነታችሁ፦ "ያው እንደሆነ አምናለሁ። አሜን። ያው እንደሆነ እመሰክርለታለሁ። ከእኔ ማንም አይወስድብኝም። እውነት እንደሆነ አውቀዋለሁ።" አሜን። ከዛ ይህ ሁሉ በእምነታችሁ ላይ ጨምሩት። መሰረቱ ላይ ደርቡት። ማደግ መጀመራችሁ ነው፡ ወደ መንግስቱ ማደግ ትጀምራላችሁ። አንድ ደረጃ ትወጣላችሁ። እሺ።

169 ሌላው፡ ብዙ ሰዎች፡ ወይም ሰባኪው፡ እንዲህ ይላችኋል፦ "ስማ... አንተ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምታነባቸው ነገሮች፡ ለሌላ ዘመን የተጻፉ ናቸው። ለምን እንደሆነ፡ እነግርሃለሁ። ዛሬ፡ እነኚህ ነገሮች አያስፈልጉንም። አያስፈልጉም። ገባህ? መሆን የለበትም። መለኮታዊ ፈውስ፣ ወዘተ መለማመድ አያስፈልገንም። ቤተ ክርስትያናችንን—ስርዓት ለማስያዝ፡ ቤተ ክርስትያን ውስጥ፡ ልሳን መናገር አያስፈልግም። እኛም **ይሄን** አንጠቀምም።"

170 ወደዚያ እመጣበታለሁ። ስለዚህ ጉዳይ ያዘጋጀሁት ቅዱስ ቃል አለ፡ እሺ፡ አሁን፡ መጠቀም አለብን ወይስ የለብንም እናያለን።

171 ሰውዬው የሚለው ግን፦ "እኔ እንጃ። ዛሬ ይሄን ማድረግ የለብንም። ማድረግ እንዳለብን የሚመስለኝ ብቸኛው ነገር፡ በህዝቡ ፊት በአግባብ መናገር መማር አለብን። ሳይካትሪስት ዘንድ ሄደን፡ እራሳችንን በትክክል ማቅረብ መቻላችን አለመቻላችንን፡ አእምሯችን እንፈትሸው፡ ምናልባት ይሄን ለመስራት በቂ አይኪው፡ አለን—የለንም ወዘተረፈ እናያለን። እንደማስበው... ትልቁ ጉባኤ የኛ ነው። ድርጅታችንን አቋቁመናል።"

172 ድርጅት እየገነባን አይደለንም። ዛሬ ማለዳ እዚህ የተገኘሁት ድርጅትን ለማቋቋም አይደለም። ድርጅት አቋቁም ብሎ ክርስቶስ ልኮኝ አያውቅም። ክርስቶስ በገዛ ቃሉ የመንፈስ ኃይል ማከማቻ እና ማደሪያው የሚሆኑት ግለሰቦችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቁመና፡ እንድገነባለት ልኮኛል። አያችሁ፡ በገዛ ቃሉ፡ ግለሰቦችን ወደዚያ ቁመና ያሳድጋል። ድርጅትን ከፍ ወዳለው የሐይማኖት ተቋም ማሳደግ ሳይሆን፡ ግለሰቦችን ወደ እግዚአብሄር ሴት እና ወንድ ልጆች ማነጽ ነው። ሐሳቡ ይህ ነው። ገባችሁ? በእምነታችሁ ላይ፡ በጎነትን ጨምሩ፡ በበጎነትም፡ እውቀትን ጨምሩ። ጥሩ፡ ወደ አንድ ሰፍራ እያደጋችሁ ነው።

173 "አይ፡ እኛ ዛሬ ይሄን አንቀበልም..." ማለት ሲጀምሩ፤ እናንተ ግን መቀበል አለባችሁ። የግድ ነው።

174 ቅዱስ ቃል ይዋሽ ዘንድ አይችልም። "በግል የሚተረጎም አይደለምል፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። በተጻፈበት መንገድ እመኑት። እሺ? እነኚህ ነገሮች ሊኖሯችሁ ይገባል። እነዚህን ነገሮች የምታገኙባቸው መንገድ፡ ከሰማይ-የመጣ እውቀት በማግኘት ብቻ ነው። ከሰማይ-የመጣ እውቀትም ቃሉን ይገልጠዋል። አያችሁ?

175 አስመሳይ-አማኝ ሳትሆኑ፡ አማኞች መሆን አለባችሁ። "ደርሼበታለሁ፡" ማለት ከፈለጋችሁ፡ እነዚህ ነገሮች እምነት-መሳዮች አይደሉም፡ አያችሁ። የፒኮክ ላባ በራሳችሁ ላይ ለመሰካት የምትሞክሩ ጥቁር ወፎች አትሁኑ፡ እሺ፡ ወድያው ይወዳድቃሉ። የተሰኩ ናቸው። በተፈጥሮ የተተከሉ አይደሉም።

176 ዳዊት በመዝሙር 1 ላይ፡ "በውኃ ዳር እንደ ተተከለች ዛፍ ይሆናል፡" ብሎ የተናገረውን አስታወሰኩ። በመተከል እና፡ በመዋቀር ወይም ተጣብቆ በመቀመጥ መካከል፡ ልዩነት እንዳለ እወቁ። ተተክሎ የቆየ፡ ወደ ታች እየተወዛወዘ አጥብቆ የያዘ፡ እንደ ኦክ ዛፍ ይቆማል። ያረጀ ግማድ እንጨት አጠገቡ ተሰክቷል፡ እጣ ፈንታው ምን እንደሆነ አይታወቅም። ስር የለውም። መሰረት አልባ ነው። አያችሁ?

177 ከሰነ መለኮት ወይም ከሌላ ትምህርት የወጣ ሰው እንዲሁ ነው። እንዲህ አትሁኑ... "እኔ'ኮ አገልግሎት ላይ በዶክተር **እከሌ-እና-እከሌ** ነው የተሾምሁት ብትሉም።" ምንም ትርጉም የለውም።

178 አያችሁ፡ አያችሁ፡ በእምነታችሁ፡ ክርስቶስ ወደዚያ ወለዳችሁ። ገብቷችኋል? ወደዚያ ዳግም በመወለድ ታደሳችሁ። ከተወለዳችሁ በኋላ፡ እንድትጨምሯቸው የሚጠብቃችሁ ነገሮች እነዚህ ናቸው። እነዚህን እየጨመራችሁ ቀጥሉ። አሁን አንድ በአንድ እያየናቸው ነው።

179 አሁን በዚህ እውቀት ላይ፡ ማንሳት የሚገባን፡ ሌላ አምላካዊ እውቀት አለ። አያችሁ? "በዚህ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሙን አጥቷልን?" ብዙ ሰዎች፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ ለማለት ፈልጎ አይደለም፡ ይሏችኋል። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንኩ፡ የሚጠብቀኝ እግዚአብሔር ከሆነ፡ ሐጥያት ስሰራ፡ ይገስጸኛል። እናንተ ሴት፡ እና ወንድ ልጆች ሆይ፡ [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] በእናንተ ላይም እንዲሁ ያደርጋል። ስታጠፉ፡ ይገስጻችኋል። እግዚአብሄር እናንተን ይሄን ያህል የሚያስብ ከሆነ፡ ከጠበቃችሁ እና ካረማችሁ፡ የገዛ ማንነቱ የሆነውን፡ እና የእናንተ ምሳሌ ያደረገውን ቃሉ፡ ምንኛ ይጠነቀቅለት ይሆን!

**በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።**

**ቃልም... ስጋ ሆነ፡ በእኛ አደረ፡...**

180 ቃሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ በቃሉ ይገለጣል፡ በማለት ያስተምራል። ሕጎችን ስትተላለፉ የሚጠብቃችሁ ከሆነ፡ በዚህም ምክንያት እናንተን ከኰነነ፡ እናንተን በሚኰንነው በገዛ ሕጉ ላይ እንዲያው እንዴት አብልጦ አይጠነቀቅም! አሜን።

181 ዘወር በል፡ አንተ ደግሞ፡ ይሄን አትንገረኝ!

182 በእውነተኛው፡ በመንፈስ ቅዱስ እውቀት አምናለሁ። የመንፈስ ቅዱስ እውቀትም ሁል ጊዜ ቃሉን "በኣሜን" ይዘጋዋል። በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እርስ በርስ የሚጋጭ የሚመስል ነገር ሲገጥማችሁ፡ እንዲሁ በጸሎት ሆናችሁ፡ ተረጋግታችሁ አጥኑት። ከዛ በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ ስራውን ሲሰራ ማየት ትጀምራላችሁ። ጥቂት ቆይቶ ያያይዝላችኋል፡ ያኔ ትረዱታላችሁ። አያችሁ? እውቀት ይሄ ነው።

183 አንዳንዶች "መጽሀፍ ቅዱስ፡ እርሱ፡ ትላንትናና፡ ዛሬ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው ይላል፡" ይላሉ።

184 ቤተ ክርስትያን ደግሞ "በመጠኑም ቢሆን፡ ያው ነው፡" ትላለች። ኸህ-ህ! ኸህ-ህ! ያኔ ነው፡ ክፍተቱት የምታሰፉት። አያችሁ? አዎን፡ ያኔ ነው። አይደለም፡ ወዳጄ። እርሱ ያው ነው። አዎን፡ ነው።

185 "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" በእሱ ዘንድ፡ በፍጹም መለያየት የለም። ተመሳሳይ ነገር እያደረገ፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ይኖራል። "ትንሽ ጊዜ፡" ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደጠቀስኩት፡ "ጥቂት ጊዜ አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ።" እርሱም፡ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም እሆናለሁ፡" ብሏልና። ዳግመኛም፡ እንዲህ አለ፦ "እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ዳግመኛም፡ እንዲህ አለ፦ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ። እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ።" ቅርንጫፍ የሚኖረው በወይኑ ህይወት ብቻ ነው። በወይኑ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር በቅርንጫፍ በኩል ይታያል። ክብር! ስለዚህ "ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለም ያው ነው።" የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት አፈራለሁ። ኣሜን።

186 እውቀት፡ ዓለማዊ ግን አይደለም (ምክንያታዊ ነውና)። ሁሉም ዓለማዊ እውቀት ምክንያት አለው። አያችሁ? እምነት ግን ምክንያት የለውም። እግዚአብሔር **እንዲህ-እንዲህ** ይሆናል ብሎ አንድ ነገር እንደሚፈጸም ሲገልጥላችሁ፣ በዓለም ላይ ያሉ ሳይንቲስቶች ሁሉ፦ "ተቃርኖ አለበት። ሊሆን አይችልም ይሏችኋል።" እናንተ ግን፡ እንዲሁ ታምኑታላችሁ። አዎን፡ ወዳጄ። አይደል? አያመካኝም። መጽሐፍ ሲናገር "ምክንያትን አሰወግደን፡" ይላል። እምነት አያመካኝም። እምነት ምንም ምክንያት የለውም። እምነት ሰፍራውን ያውቃል። እምነት ይሠራል። እምነት ጸንቶ ይኖራል። አይወድቅም። ምንም ነገር አይጥለውም። **ይህ፣ ያ፣ ሌላ** ስለሚናገረው ግድ የለኝም።

ፈጽሞ፡ አይወድቅም። ባለበት ይጸናል፡ ይጠብቃል፡ ይጠብቃል፡ ይጠብቃል፡ ይጠብቃል። ምንም ለውጥ አያደርግም። ባለበት ይጸናል።

187 እግዚአብሔር ይህ ይሆናል ብሎ ኖኅን ነገረው። አመነ። አያችሁ? እግዚአብሔር ይህ ይሆናል ብሎ ሙሴን ነገረው። አመነ። እግዚአብሔር እንዲህ እና እንዲህ ይሆናል "ሂዱና እስከ ጴንጤቆስጤ ድረስ ጠብቁ" ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ነገራቸው። እነርሱም ታምነው ጠበቁት። አዎን፡ ጠበቁት። ትክክል።

188 አሁን፣ ይህ እውቀት፡ ማለት፡ ዓለማዊ ያይደለ እውቀት፡ ሰማያዊ እውቀት ነው። ሰማያዊ እውቀት፣ እግዚአብሔር የእውቀት ሁሉ ምንጭ ሲሆን፡ እና እግዚአብሔር ቃል ሲሆን፣ እንግዲህ፣ ሰማያዊ እውቀት ካላችሁ፣ ቃሉን ታምናላችሁ፣ ማንኛውንም ነገር በቃሉ ምክንያት ታሰባላችሁ።

189 ቤተ ክርስትያኒቱ የገባችበት፡ ወይም እኔ ገብቼበት የነበረ የግብር ጉዳይ ነበር። ከሰዎቹ አንዱ፡ በክስ መዝገብ ቀን፡ እንዲህ ብሎ ነግሮኝ ነበር። እንዲህ አለኝ... "ምንም አይነት ክፍተት ማግኘት አልቻሉም፡" አለኝ። ከዛ በኋላ ምን ጀመሩ...

190 እኔም፡ "ታድያ፡ ምንም ችግር ካልተገኘብኝ፡ ለምን አትተውኝም? " አልኩት፤ አያችሁ? አያችሁ? ወደርሱ ቀረብ ብዬ፡ ጥቂት ቅዱስ ቃላት ነገርኩት።

191 በጣም ግዙፍ ሰው ነው ሲጋራ እጁ ላይ ይዟል፡ እና እንዲህ አለ፡ "አቶ. ብራንሃም፡ እኔም የመጽሀፍ ቅዱስ ተማሪ ነኝ፡" አለኝ።

"ይህን በመስማቴ ደስ ብሎኛል።" አልኩት።

192 እርሱም፡- "አንተ ገንዘብ እያስከፈልክ የምትልካቸው መሃረቦች፡ ምን አይነት አጉል ልማዶች ናቸው ማወቅ እፈልጋለሁ፡ መሃረብ ላይ ጸልየህ የምትልከው ይህ አጉል ልማድ፡ 'የተቀባ ልብስ፡' ብላችሁ፡ ትጠሩታላችሁ። በዚያ ላይ "ገንዘብ ታስከፍላለህ፡" አለኝ።

እኔም "በጭራሽ፡ አላስከፍልም። ክፍያ የለውም፡" አልኩት።

በድጋሚም "እሺ፡ ይህ አጉል ልማድ፡" ብሎ ተናገረኝ።

193 እኔም፡ "እንዴት አጉል ልማድ ብለህ፡ጠራኸው። ቀደም ብለህ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ነኝ ብለህ ነግረኸኝ አለነበረምን።"

እርሱም "አዎን ነኝ፡" አለ።

194 "የሐዋርያት ሥራ 19፡11 ንገረኝ፡" አልኩት። እውቀት! እሱ ራሱ ወጥመድ ውስጥ ገባ፡ ርዕሰ ጉዳዩን ለመለወጥ ሞከረ። "ከዚያም ዮሐንስ 5፡14ን ጥቀሰልኝ፡" አልኩት። አልተቻለም። "ከዚያም ያዕቆብ 5፡14፡" አልኩት። አልቻለም። እንዲህ አልኩት፡- "ዮሐንስ 3፡16 ታውቃለህ? " አያችሁ? እውቀት፣ ብልጠት፣ ዓለማዊነት! መቼም...

195 እርሱም፡ "አቶ. ብራንሃም፡ አንተ'ኮ፡ ኬዙን በመጽሐፍ ቅዱስ ለመፍታት ትሞክራለህ። እኛ ደግሞ በምድሪቱ ሕግ ነው።"

196 እኔም፡ "የምድሪቱn ሕግ፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል መሰረት ያደረገ አይደለምን? ስለዚህ ፍትሕ ነው።" አሜን! በትክክል።

197 ዓለማዊ ያይደለ፡ ዕውቀት። የቃሉ መንፈሳዊ እውቀት፡ እግዚአብሄር ያለውን ማወቅ፡ እግዚአብሄር ያዘዘውን ማድረግ፡ ትክክለኛው ይህ ነው። ስለዚህ ይህ ካለህ፡ ቃል የሚናገረው ነገር ሁሉ እውነት እንደሆነ እና፡ እርሱ ያው እንደሆነ ካመንክ፡ ሁሉንም "በአሜን" ሰርዓተ ነጥብ ትዘጋለህ። ይህም መልካም ነው። ይህም እምነትህ ላይ ጨምረው። ይህም መልካም ነው። አዎን።

198 አንድ ሰው ቀርቦ፡ እንዲህ በማለት፦ "መጽሀፍ ቅዱስ ኃይል የለውም። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብሎ ነገር የለም" ለማለት ቢሞክር። ኧህ-ህ። ይሄን አትጨምር። አይሰራም። ይወድቃል። በድንጋይ ላይ ሽክላ እንደ ማቆም ነው፡ አይቆምም። ይንከባለላል።

199 ከዚያም ሰዎች መጥተው፦ "መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ሊታመን አይችልም። አሁን ተጠንቀቅ። ያንን እምነህ አትሂድ። ጥቅም ሊሆን አይችልም-... " ለብዙ ዘመን ሲባል የነበረው ሰምታችኋል። "መጽሐፍ ቅዱስን ማመን አይችሉም፡" ይሉ ነበር። አዎን፡ ይህ በአእምሮህ ውስጥ—ከገባ፡ ምንም ስለማይጠቅም፡ ይሄን ለመጨመር—አይሞክር። መላው ሕንፃው እዚያው ይወድቃል።

200 በመንፈስ ቅዱስ መለሰን አለባት። አጣብቆ በሚይዛት ማሕተም፡ መጣበቅ አለባት ማለቴ ነው። በሚያትማት ተመሳሳይ ነገር... መንገዱን ታውቁታላችሁ...

201 ባረጀ-እራፊ ከተዘጋ ካላማዳሪ ይልቅ ቀልጦ የተዘጋውን ሁሌ ዕድሜ ይኖረዋል። አሮጌው እራፊ ብትንሸ ሙቀት ጎማው ላይ ይጣበቃል፡ መጀመሪያ ነገር፡ ጎማውን ትንሽ ይሙቅ፡ ከዚያ ትንሽ በፍጥነት ከሮጣችሁበት፡ ቀልጦ ይወድቃል። አዎን፡ አይቆይም። አያችሁ?

202 ዛሬም የብዙ ሰዎች ህይወት ይህ ነው። እውቀታቸውን በዓለም ዕውቀት ላይ፡ በትንሽ አሮጌ ምድራዊ ሙጫ ለማጣበቅ ይሞክራሉ፡ እና፡ ፈተናዎች ሲመጡ "አይ፣ ምናልባት ተሳስቻለሁ ይላሉ።" ወድያው አየሩ ይወጣል፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ይበላሻል። አያችሁ? ጩኸታችሁ ሁሉ ወደላይ-እና-ወደታች መዝለላችሁ ምንም አይጠቅምም። ህዝቡ እንደገና በተመሳሳይ ኩሬ ውስጥ ያያችኋል። አያችሁ? ትክክል።

203 ነገር ግን በበቂ የመንፈስ ቅዱስ ሙቀት፡ አንተን እና ካላማዳሪውን አንድ እስኪያደርጋችሁ ድረስ ከቆያችሁ። በቃ። አንተ እና ካላማዳሪው አንድ ትሆናላችሁ። አንተ እና እያንዳንዷ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አንድ እስክትሆኑ ድረስ እዛው ስትቆይ፣ ያኔ በእምነትህ ላይ ይሄን ጨምረው። ካልቆየህ ግን፡ ፈጽመህ አትጨምረው።

"ቃሉ አይታመንም፡" እያልክ። ይሄን ለመጨመር አትሞክር።

204 "የተሰፋው ቃል፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ነበር፡" እያልክ፤ ዛሬ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚሉት፡ ይህን ለመጨመር አትሞክር። ከመሠረታቸው እያልፉም፡ ሁሉም ይፈርሳሉ። አያችሁ? ልክ እንደ ያዝያ፡ ትላንት ሌሊት የታመነበትን ሰው መሰረቱ ባየው ጊዜ፡ ሁሉም ፈራረሰበት፡ በለምጽ ተመታ፡ ምንም ጥሩ አልነበረም። አሁንም፡ "ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ነው፣ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ።"

205 እነ ወንድም ራይት ከኋላ አካባቢ ናቸው መሰለኝ... እና እነሱ ጋር ወርጄ ነበር። አንድ ቀን ማታ፡ እኔ እየሰበክኩ፡ አንድ አገልጋይ በዚያ ነበረ፡ ባጠቃላይ አራት አምስት ሰባኪዎች ነበሩ። እና ሰባኪው ተነሰቶ፡ “የተወደዳችሁ ሰዎች ሆይ፡ ስሙኝ አንድ ነገር ልንገራችሁ። ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ሰዎች ናችሁ፡” አለ።

206 ይህን ነገር፡ ለአንድ ሰው ተናግሬአለሁ፡ “እዛ ጋር—ቁጭ ያለውን፡ እዩት።” ነግሬዋለሁ።

207 ከኋላ የሚታያችሁ፡ ጁኒየር ጃክሰንም፡ እየተናገረ ነበር። እንዲህ ብሎ... ስለ እግዚአብሔር ጸጋ እየሰበከ ነበር። ኦህ፡ ማይ!

208 ተነሰቶ ለመረዳት እየሞከረ። እየተቀጣጠለ፡ ሲጠባበቅ ነበር። “ልንገራችሁ፡ እዚህ የምታዩት አቶ. ብራንሃም፡ ጸረ ክርሰቶሰ ነው አለ።” ምሽቱን፡ ይሄን በመናገር ጨረሰው።

209 አንዳንድ ሰባኪዎች ሊነሱ ሲሉ... ተውት አልኳቸው፡ “ወንድሞች፡ አሁን፡ ምንም አትበሉት። ትንሽ ታገሱ። እሱ አንድ ነው እኛ ብዙዎች ነን አልኳቸው።” “አሁን ዝም በሉት። በኔ ላይ ነው የተነሳው፡” አልኳቸው። እኔ እራሴ፡ በጣም፡ ፈልጌዋለሁ፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግን አላወቅኩም። አያችሁ?

210 እና፡ ንግግሩን ቀጠለበት፦ “አቶ. ብራንሃም ጸረ ክርሰቶሰ ነው፡” እያለ፡ ሌላ ሌላ ነገር እየተናገረ፡ ቀጠለ... እንዲህ አለ፦ “እዛ ሲናገር ‘የመንፈሰ ቅዱሰ ጥምቀት’ ብሏል አለ።” “መጽሐፍ ቅዱሰ ግን አሰራ ሁለቱ ብቻ መንፈሰ ቅዱሰ መሞላታቸው ያሰተምራል፡” አለ። ሰለ መለኮታዊ ፈውሰ ብንነጋገርም “አሰራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ናቸው መለኮታዊ ፈውሰ የነበራቸው፡” አለ። ሰለዚህ “መጽሐፍ ቅዱሰ ሲናገር እንናገራለን፡ መጽሐፍ ቅዱሰ ዝም ሲል ዝም እንላለን፡” አለ። ተንፈራግጦ እሰኪጨርሰ ድረሰ ለግማሽ ሰዓት ያህል ታገሰኩት።

211 “አንድ ደቂቃ ታገሰኝ፡ ጽፌ የያዝኩት ብዙ ነገር አለኝ፡” አልኩት። “ጥቂቶቹን እንድመልሰ እድል ሰጠኝ፡” አልኩት። በተነሳሁም ጊዜ፡ እንዲህ አልኳቸው፦ “ሰውዬው ሲናገር፡ ቤተክርሰትያኑ ውሰጥ ‘መጽሐፍ ሲናገር እናገራለሁ፡’ ‘ዝም ሲልም ዝም እላለሁ።’ ብሏል እናንተም ምሰክሮች ናችሁ አልኳቸው። ‘አዎን’” አልኳቸው፦ “ሰውዬው፡ ሲናገር ‘መንፈሰ ቅዱሰን የተቀበሉት አሥራ ሁለት ብቻ ነበሩ ብሏል።’ መጽሐፍ ቅዱሴ ግን፡ በመጀመርያ መፍሰሰ ላይ አንድ መቶ ሀያ ሰዎች ነበሩ ይላል።” አሜን! የምታዩትን፡ ሰውዬው የሚሞካከረው ከንቱ እውቀት፡ አሽቀንጥሩት።

212 “ታድያ ጳውሎሰም መንፈሰ ቅዱሰ አላገኘም ብለን እናሰብ ወይ እሱ ተሞልቻለሁ ብሏል፡” አልኳቸው። አያችሁ?

213 እንዲህ አልኳቸው፦ “ፊልጶሰ... ወደ ሰማርያ በወረደ ጊዜ ወንጌልን ሰበካቸው። በጌታ ኢየሱሰ ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ። መንፈሰ ቅዱሰ በእነርሱ ላይ አልወረደም ነበር፡ ይላል። ጴጥሮሰን እና ዮሃንሰን ሰደዱላቸው፡ እጆቻቸው በጫኑባቸው ጊዜ፡ መንፈሰ ቅዱሰ በእነርሱ ላይ ወረደ። ታድያ ይሄ በአሰራ ሁለቱ ብቻ ነውን? ”

214 ጨምሬም፦ “በሐዋርያት ሥራ 10:49፣ ጴጥሮሰ በሰገነት ላይ ሳለ ራእይ አይቶ፡ ወደ ቆርኔሌዎሰ ወረደ’። ጴጥሮሰ እነዚህን ቃላት ገና ሲናገር፣ መንፈሰ

ቅዱስ ቃሉን በሰሙት ላይ ወረደ።” “መጽሀፍ ቅዱስ አሁንም እየተናገረ ነው፡ ቤተክርስትያንህ የት አለች? ” አልኩት። ሊሆን-ይችላል ላይ ናት። አዎን። አያችሁ?

215 እንዲህ አልኩት፡ “ስለ መለኰታዊ ፈውስ፡ አንስተሃል፡ ‘አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ መለኰታዊ ፈውስ ነበራቸው ብለሃል።’ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ወርዶ አጋንንትን አውጥቶ ድውያንን እንደፈወሰ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡ በከተማይቱም ታላቅ ደስታ ሆነ። ፊልጶስ ከአስራ ሁለቱ መካከል አይደለም። ሐዋርያ አልነበረም። ዲያቆን ነበር።” አሜን። አሜን።

216 “ጳውሎስ በላይኛው ክፍል ውስጥ ከነበሩት ከአሥራ ሁለቱ አንዱ አይደለም፡ የመፈወስ ስጦታ ግን ነበረው፡” አልኩት።

217 አልኳቸው፡- “የፈውስ ስጦታዎችን እዩ! በትክክል፡ ከሠላሳ ዓመት በኋላም፡ በክርስቶስ አካል ላይ፡ መለኰታዊ ፈውስ እየሾመ በቆሮንቶስ ነበር።” ኦህ፡ ማይ!

218 ስለዚህ፡ ከአንዳንድ መጻህፍት ውስጥ የተማራችሁት እንደዚህ አይነት እውቀቶች፡ ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ብትጥሉት ይሻላል። ወደዚህ እውቀት ተመለሱ። እግዚአብሔር፡- “ትናንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ድረስ ያው ነው ሲል፡” “አሜን፡” በሉት። አዎን፡ ወዳጄ። አዎን፡ ወዳጆች። ለአሥራ ሁለቱ አይደለም፡ ለሁሉም ነው። እንደዚህ አይነት—እምነት ሲኖራችሁ፣ እምነታችሁም፡ እያንዳንዷን ነገር፡ “በአሜን” ሰርዓተ ነጥብ ሲደመድም፡ “በጣም ጥሩ፡” ይሄ፡ መጨመር አለበት ትላላችሁ።

219 አራተኛው። መፍጠን አለብን፡ እዚህ ቆሞ... ስለነዚህ ነገሮች ማውራት በጣም ይጣፍጣል። አሜን። [አንድ ወንድም፡ “እያጣጣምነው ነው አለ።”—አርታዒ።] አዎን። አመሰግናለሁ። አራተኛው...

220 “ራስን መግዛት” ጨምሩ። ኦህ፡ ማይ! አሁን ራስን መግዛት ላይ ደርሰናል። በመጀመሪያ፡ እምነት ነው፡ ከሁሉ በፊት፡ አስቀድማችሁ፡ እምነት ይኑራችሁ። በመቀጠል፡ ትክክለኛውን በጎነት ከያዛችሁ፡ በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ጨምሩ። አሁንም ትክክለኛው እውቀት ሰታገኙ፡ እውቀትን ጨምሩ። አሁን ደግሞ ራስን መግዛት ጨምሩበት።

221 ራስን መግዛት ማለት፡ “አልኮል መጠጣት ማቆም፡” ማለት፡ አይደለም። አይ፡ አይ። ራስን መግዛት ስንል በዚም መልኩ አይደለም፡ ከአልኮል ነጻ መሆን አይደለም። ይህ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ራስ መግዛት፡ መንፈስ ቅዱሳዊ ራስ መግዛት ነው። ያ’ማ ከስጋ ምኞቶች መካከል አንድ ነው፡ እኛ የምንናገረው ግን መንፈስ ቅዱሳዊ ራስ መግዛት ነው። ይህ ማለት፡ አንደበትን መቆጣጠር ማለት ነው፡ ሐሜት መተው፤ ቁጣህን እንዴት ትቆጣጠረዋለህ፡ ማንም በተናገረህ ቁጥር ባለመበሳጨት። ኦህ፡ ማይ!

222 ወዳጄ፡ ብዙዎቻችን ገና ሳንጀምረው እነወድቃለን፡ አይደል’ዴ? አያችሁ? ከዛ እግዚአብሔር ለምን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንደሌለ፡ ድሮ የነበሩትን ተአምራትን እና ድንቆችን ለምን የሉም ብለን እንቅበዘበዛለን። እንዲያ፡ ነው። አያችሁ?

223 እነዚህን ጨምሩ። ራስ መግዛት ጨምሩ። ኦህ፡ ራስን መግዛት ማለት፡ በቁጣ ሲናገሩህ በደግነት መመለስ ነው። አንድ ሰው መጥቶ “እናንተ አልቃሾች ወንበር-ሰባሪዎች!” ቢላችሁ፤ እጅጌ ሰብሰባችሁ አካኪ ዘራፍ ለማለት አትነሱ። እሺ? አይደለም። በእግዚአብሄር ፍቅር፣ እራሳችሁ ከመግዛት ጋር፣ በትህትና መልሱላቸው። መሆን ትፈልጋልላችሁ? ሲሰድቧችሁ፡ በሰድብ አትመልሱ። እርሱን ምሳሌአችሁ አድርጉት።

224 “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፡ እነዚህን ድንጋዮች ወደ እንጀራ ቀይር።” ባሉት ጊዜ፡ ያሉትን ቀይሮ፡ አምላክ መሆኑ ማስረዳት ይችል ነበር። ራስን መግዛት ግን ነበረው። “ብዔልዜቡል፣” ባሉት ጊዜ፡ “ይቅር ብያችኋለሁ፡” ብሏል። አይደል? ከፊቱም እፍኝ ጢሙን ነቅለው፡ በፊቱ ላይ ተፉበት፡ “ከመስቀል ውረድ!” አሉት፤

225 “አባት ሆይ ይቅር በላቸው። የሚያደርጉትን አያውቁም፡” አለ።

226 በእርሱ የመለኮት ሙላት በሰውነት ተገልጦ ነበርና፡ በነበረው፡ ሰጦታ፡ ሁሉን ያውቃል። ለሰዎች ችግራቸውን በመንገር፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ፡ ተአምራት ሲያደርግ አይተውታል። በጭንቅላቱ ላይ የነተበ ጨርቅ፡ አይኖቹ ሸፍነው፡ ጭንቅላቱን በበትር መቱት፡ “ትንቢት ተናገር ማን እንደመታህ ንገረን። እናምንሃለን፡” አሉ። ራስን መግዛት ነበረው። አያችሁ?

227 እናንተም፡ እንዲህ ካላችሁ፡ በእምነታችሁ ላይ ጨምሩ። ቶሎ ከፈነዳችሁና ከተንኮታኮታችሁ፣ ከነፈራችሁ፣ ጉራ ጉራ ካላችሁ፣ እና ከቀለጣችሁ፣ ኧህ-ህ፡ ገና አላገኛችሁትም... ይህ የሚጨመር ስላልሆነ፡ መጨመር አትችሉም። አያችሁ? አይጣበቅላችሁም። አያችሁ፡ የጎማ ቁራጭ ውሰዳችሁ፡ ቁራጭ ብረት ላይ ማጣበቅ አትችሉም፡ አይሰራም። አይቻልም፡ እንደጎማው፡ ለሰላሳ መሆን አለበት። አይደል? የእናንተ እምነት እና ራስ መግዛትም ለመንፈስ ቅዱስ ያለው ራስ መግዛት ዓይነት ከሆነ፡ አብሮት ሊጣበቅ ይችላል። እናንተም ትጨምሩታላችሁ።

በጎነታችሁ እንደርሱ በጎነት ከሆነ፡ ትጨምሩታላችሁ።

228 እውቀታችሁ እንደ እውቀቱ ሲሆን፡ “አምላክ ሆይ፡ ፈቃድህን ለማድረግ መጥቻለሁ ነው።” አያችሁ? በአባቱ ቃል፣ ሰይጣንን ሁሉ ድል አድርጓል። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሉ ግን አያልፍም። አስተውሉ? እንደዚህ አይነት እውቀት ሲኖራችሁ፡ በእምነታችሁ ላይ ይጣበቃል።

229 የእሱን አይነት፡ ትክክለኛ ራስ መግዛት ሲኖራችሁ፡ ይጣበቃል። ከሌላችሁ፡ በከፊል ሰው-ሰራሽ፡ እና የተዛባ-እምነት፡ ወይም አጉል ራስ መግዛት ከሆነ፡ “ኧረ፡ በጥፊ ብጥለው ደስታዬ ነው፡ ምናልባት ግን——የክስ መዝገብ ከሚከፈትብኝ፡ ቢቀርብኝ ይሻለኛል።” እሱ እየተናገረ ያለው እንደዚህ አይነት ራስ መግዛት አይደለም። ለመጨመር አትሞክሩ። አይሰራም። ነገር ግን ከልባችሁ፡ ከእውነት በመነጨ መልካምነት፡ ሰላማችሁን ስትጠብቁ፡ ሰውን ሁሉ ይቅር ስትሉ፡ ይቅርብኝ ስትሉ፡ ያኔ፡ ይጣበቃል። እንዲህ አይነቱን እምነታችሁ ላይ ጨምሩት። ዊው!

230 ቤተ ክርስትያን ድሃ መሆኗ አያስገርምም። እውነት አይደል? አይገርምም። “መጽሐፍ ቅዱስ፡ ንስሐ ግቡና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ይላል፡” ብዬ ብናገር። ይሄን የማያምን ወግ አጥባቂ የሰላሴ አማኝ መጥቶ፡ “ይሄ የጸረ

ክርስቶስ ነው። የኢየሱስ ሰም ነው። የኦንሊ ጂሰስ ነው፡” ሊል ይችላል። ወዳጄ፡ ተረጋጋ፡ ያኔ ራስ መግዛታችሁ ምን እንደሚመስል እንጃ። ገባችሁ? መጥተህ’ኮ “ወንድም ብራንሃም፡ ና እስቲ ይህ ነገር እንነጋገርበት፡ ይህ ነገር ሲብራራ ልሰማው”? ማለት ትችላላችሁ። አየህ? ናና ስማው። በፊትህ ይቀርብልሃል፡ ከዛ በኋላ መንገድህን ትቀጥላለህ፤ ከአፍታ—በኋላ፡ ወደዛ፡ “እግዚአብሄርን ወደ መምሰል” እናልፋለን እሺ። በየአንዳንዷ ርዕስ ከፍ ዝቅ ካልክ—ብረር ብረር የሚልህ ከሆነ፡ ኧሃ-ህ፡ ገና—አልደረስክበትም። አየህ? እንዲህ ከሆንክ፡ እንዴት መመለስ እንዳለብህ የመጽሐፍ ቅዱሱ ራስ መግዛት የለህም። ይህ ሁሉ ካለህ ግን፡ በእምነትህ ላይ ደርበው።

231 ከዛ በኋላ፡ በአምስተኛ ደረጃ፡ በእምነትህ ላይ፡ ትዕግስትን ጨምርበት። እምነት ካለህ፡ “ትዕግስትን ይሰራል፡” ይላል መጽሀፍ ቅዱስ። አየህ? ትዕግስት **ይሄ** ነው። ቁመናውን ከሚሰሩ ነገሮች፡ ቀጣይ መሳርያ ይህ ነው። ታውቃላችሁ፡ እግዚአብሄር በህንጻው ውስጥ ትክክለኛ መሳርያዎች አሉት።

232 ወንድም፡ እህቶች ሆይ፡ ምን ያህል ድሆች እንደሆንን አይታችኋል? እዩት? ያለነው የት ነው፡ ለምን? አዎን፡ ወገኔ። አያችሁ? እምነት ሰላለን፡ አሁን ዕልልታና፡ ጩኸት እና ሌላ ሌላ ነገሮች አሉን። **እዚህ** ወደተዘረዘሩት ስንመጣ ግን፡ በዚሁ ቁመና እግዚአብሄር ሊገነባን አይችልም። አያችሁ? አይችልም። ሌላ ነገሮች ሁሉ አዝለናልና። ወደዚያ አካል ሊያደርስን አይችልም። ሰንወድቅ፡ በዚያው እንወሰዳለን። አያችሁ? በዚህ ቤተ ክርስትያኑን መገንባት አይችልም።

233 ትዕግስታችን ለማን ነው? ምን አይነት መታገስ? ከሁሉ በፊት፡ ከእግዚአብሄር ጋር ትዕግስት ይኑረን። እምነት ትዕግሥትን ይሠራልና፡ እውነተኛና ትክክለኛ፡ እምነት ካላችሁ፡ እውነተኛና ትክክለኛ ትዕግስት ይኖራችኋል። እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ሲናገር ታምነዋለህ። ይኼው ነው። ትዕግስት አለህ።

234 “ኧረ፡ ማታ ፈውሰኝ ብዬ ለመንኩት፡ ዛሬ ጠዋትም እንደታመምኩ አለሁ፡” ትላለህ። ኦህ፡ ማይ! ምን አይነት ትዕግስት ነው?

235 እግዚአብሔር ለአብርሃም ተናገረ፣ ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ አንድ ምልክት እንኳ አልነበረም። እሱ ግን አሁንም ያምን ነበር። እግዚአብሔርን ታግሷል። ኧህ-ህ።

236 ሁል ጊዜ በፊታችሁ አድርጉት። እርሱ ቀድሞ ይሻገርላችሁ። አትቅደሙት፡ ከፊት ሁን በሉት። “ተናግሯልና፡ እንዳለው ይፈጸማልና።” አያችሁ? ከፊት ይሁንላችሁ። ልክ ነው።

237 ኖህ ታግሷል። አዎን። ኖህ እውነተኛ፡ የእግዚአብሄር ትዕግስት ነበረው። እግዚአብሔር፡ “ይህንን ዓለም በውኃ አጠፋለሁ፡” አለ፡ ኖኅም ለመቶ ሀያ ዓመት ያህል ይህንን ሰበከ። ምንም ሳይኖር። ብዙ ታገሰ። ጠል እንኳን ከሰማይ ሳይወርድ። መቶ ሀያ አመታት ሁሉ፡ እንደ ወትሮው አቧራ ነው፡ እርሱ ግን ታገሰ።

ስለዚህ፡ እግዚአብሄር ትዕግስታችሁን ይፈትነዋል። አዎን። እግዚአብሄር ይፈትናቸዋል።

238 ኖህን ካዘዘው በኋላ፡ እንዲህ አለው፡ “ኖህ፡ አሁን ቀጥልና ወደ መርከብ ግባ። አንተ ግባና—ሌሎቹ እንሰሶች፡ እንዲገቡ እነዳቸዋለሁ። አሁን፡ እንድትገባ

እፈልጋለሁ፡ ወደ ሰገነት ውጣና፡ ከዛ፡ በላይኛው መስኮቶች፡ ወደ ውጭ ማየት ትችላለህ። ሰዎችን ሁሉ እንዲህ ትላቸዋለህ፦ 'ለአንድ መቶ ሀያ አመታት የሰበኩት ሰብከት፡ ነገ፡ ይፈጸማል' ትላቸዋለህ። በጣም ጥሩ፡ አሁን ውጣና ንገራቸው።"

239 የመጀመሪያው ምልክት ምን ነበር? ኖህ ወደ መርከብ ገባ። ዝናብም አልነበረም። ኖህ ተዘጋጀ፡ አልፎ አልፎ፡ የሚሆነውን ለማየት፡ የዝናብ ካፖርት፡ እና ሌላ ሌላ ለብሷል። ተዘጋጅቷል። ቀጣይ ቀን ግን…

240 የልጆቹ-ሚስቶችን-ጨምሮ፡ መላ ቤተሰቡን፡ እንዲህ ሳይላቸው አይቀርም፦ "ኦህ፡ ማይ! ነገ አይታችሁት የማትውቁ ነገር ታያላችሁ። ምክንያቱ፡ ሰማያት ሁሉ፡ ይጠቁራሉ። መብረቅ እና ነጎድጓድ ይሆናል። ታላቁ የእግዚአብሄር ሰይፍ በሰማያት እንደ ዚፕ ያልፋል። ለመቶ ሀያ አመታት ሲሳለቁብን የኖሩትን ሐጥያተኞችን ሁሉ፡ ይኰንናቸዋል። ጠብቁት እና ታያላችሁ።" አያችሁ?

241 ታውቃላችሁ፡ አንዳንድ የመንገድ-ዳር አማኞች፡ በዙሪያው ያንዣብባሉ፡ ታውቋቸዋላችሁ፡ በጭራሽ አይገቡም። አሁንም—ከእናንተው ጋር፡ አሉ። ስለዚህ—መጥተው እንዲህ አሉ፡ "እስቲ፡ አዛውንቱ ትክክል ሊሆን ስለሚችል፣ ለጥቂት ቀናት እንጠብቃለን፣ ወይም፡ ጠዋት ላይ ለጥቂት ሰዓታት አይተን እንጠብቀዋለን።"

242 በሚቀጥለው ቀን፣ ከጥቁር ደመና ይልቅ፣ ጸሀይ እንደወትሮዋ ትወጣለች። ኖህም አየና። "ሄይ፡ ዛሬ ደመና አልወጣም፡" አለ።

243 ያ ሰውዬ መጣና እንዲህ አለ፡ "ኧይ፣ አንተም ከነሱ አንዱ እንደሆንክ አውቃለሁ። ሰማ፣ ዝም ብለህ ትንከራተታለህ።"

244 "ደህና፣ ሀ-ሀ። ይቅርታ አድርግልኝ፣ ጌታው። እንደምታውቀው፡ ምናልባት እኔ—እይ—እኔ፡ በቃ፡ ታውቃለህ፡ ደስተኛ ነኝ። ብቻ ጠብቅ፣ እሺ። ሀ-ሀ-ሀ።"

245 ኖህ፡ ግን፡ ትዕግስት ስለነበረው። "ዛሬ ካልመጣ፡ ነገ ይመጣል፡" አለ። ለምን? ጌታ ስለተናገረ።

"ኖህ ሆይ፡ መቼ ነው የነገረህ? "

246 "ከመቶ ሃያ ዓመታት በፊት። እስከዚህ ድረስ ተጉዣለሁ፡ አሁንም እጠብቃለሁ።" አያችሁ ወይ? በኋላ ግን…

247 ጌታ፡ ቤተ ክርስትያንን፡ እስከዚህ ዘመን ድረስ እንደጠበቃት አውቀናል፡ መምጣቷ ግን የማይቀር ነው። አይዟችሁ። ቃል ገብቶልናል።

248 እስክትነሳ ድረስ ይሄን ያህል ጊዜ ጠብቋታል። አታስቡ። ትንሳኤ ይሆናል። እግዚአብሔር ቃል ገብቷልና። በትዕግስት ብቻ ጠብቁ። አንተ ብታንቀላፋም፡ አያቅተውም… ከመከሰቱ በፊት እንቅልፍ ወስዶህ ቢሆንም፡ በዚያ ጊዜ ግን ትነቃለህ። አየህ፡ ቃል ገብቷል። እንቅልፍ፡ ታውቃላችሁ፡ ሞትን፡ እንቅልፍ፡ ነው። ሞትን፡ በክርስቶስ ሆኖ ማረፍ፡ ወይም ማንቀላፋት እንለዋለን። አያችሁ? ሕይወት እና ሞት አይቀላቀሉምና። በክርስቶስ ተሁኖ መሞት የለም። ወዳጆቻችን ሊቀሰቅሱን በማይችሉበት እንቅልፍ እንወሰዳለን። ሊጠራን የሚችለው እሱ ብቻ ነው። ኢዮብም "ይጠራኛል፡ እመልሰለታለሁ፡" ብሏል። ኢዮብ ለአራት ሺህ ዓመታት ተኝቷል። ቢሆንም አታስቡ። አንድ ቀን—ይነሳልና። አሁንም እየጠበቀ ነውና። አታስቡ።

249 ኖህ ጠበቀ። አራተኛው ቀንም አለፈ። ዝናብ የለም። መምጣቱ አይቀርምና። ምንም አይደለም።

250 ወ/ሮ ኖህ ወደ አካባቢው መጥታ እንዲህ ስትል እሰማለሁ፦ “ጋሼ፡ እርግጠኛ ነህ-... ? ”

“ዝም በይ እንዳትጨርሺው።”

251 እምነት ስለነበረው፡ ትዕግሰት ነበረው። አዎን፡ ጌታዬ። በጎነት ነበረው። እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ አውቋል። ራሰን መግዛት ነበረው። “እንጃ፡ ሰለ ምን እንደሆነ አላውቅም። ተወዳጅነቴን ሁሉ ግን አጥቻለሁ፡” ብሎ፡ ቶሎ አይበሳጭም። “ሰዎች ከእንግዲህ ለእኔ ግድ የላቸውምና። ሄጄ እንደገና እጀምራለሁ፣ እንደገና በአዲሰ መልኩ ልጀምር፡” በጭራሽ፡ አይልም። በጭራሽ፡ አይልም። ጌታ ቃል ገብቶለታ። ጌታ ቃሉን ይፈጽማል። ጌታ ተናግሯልና፡ ጌታ ያለውን ያደርጋል። ትዕግሰተኛ ነው።

252 እያችሁ፡ ልጁም መጥቶ፡ የሸበተውን ረጅም ጸጉሩ በእጁ እያሻሸ፦ “ታውቃለህ፡ ዳዲዬ... ” ሲል ይታየኛል። እያችሁ፡ እርሱ ራሱ እድሜ ጠግቧል፡ ቁጭ ብሎ። እንዲህ አለው፦ “ከጥንት አባቶች አንዱ እንደሆንክ ይገባኛል። ዳዲዬ፡ እኔ—እወድሃለሁ። ግን ትንሽ ተሳሰተህ ሊሆን እንደሚችል አትጠረጥርም? ”

“ኧይ፡ በፍጹም፡ አልተሳሳትኩም።”

“ለምን? ”

“ጌታ ተናግሯላ!”

253 “ደህና፣ አባቴ፣ እዚህ ከገባን ገና ሰድሰት ቀናችን ነው። በዚህ በትልቁ፡ በደረቀው፡ መርከብ ውሰጥ ተቀምጠናል። ደግሞም፡ ከውሰጥ እና ከውጭ ተዘግቷል። እኛም ይሄን ሁሉ አመታት ሰንገነባው ቆይተናል። አንተም ጸጉርህ እሰኪመልጥ፡ እና እሰኪሸብት ድረሰ ሰብከሃል። አሁን ደግሞ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ይሆናል እያልክ፡ እዚህ ነህ። ሰዎቹም እየሳቁ፣ እና የበሰበሰ ቲማቲሞችን እና ሌላ ነገሮችን እየወረወሩ ናቸው። እያደርግ ያለኸውን ነገር መርምር። ለምን፡ አንተም እንደምታውቀው... ”

“ልጄ ሆይ፡ ታገሰ።”

“እርግጠኛ ነህ? ”

“ይዘንባል!”

የልጁ-ሚሰት-ምራቱም፡ “አባት ሆይ፡ እንደምታውቀው... ”

“ይዘንባል!”

254 “ግን እነዚህን ሁሉ ዓመታት ጠብቀናል። እየተዘጋጀን ነበር። ከአንድ ሳምንት በፊትም፡ ዝናብ እንደሚዘንብ ነግረኸናል። እኛም ውሰጥ ገብተናል፡ በሮች ሁሉ ተዘግተዋል፡ ወዲያ እና ወዲህ እየተራመድን ነው፡ ፀሐይ እንደሆነች እንደ ድሮዋ ታቃጠላለች።”

“መዝነቡ ግን አይቀርም!”

“እንዴት ታውቃለህ? ”

“ጌታ ተናግሯል!”

255 በዚህ መልኩ ከደረሳችሁበት ጨምሩት። አለዚያ ግን ተውት፡ ለመጨመር—እንዳትሞክሩ። አይጠቅማችሁም። ፈውስ ላይ አይጠቅማችሁም። በሌላም ነገር አይጠቅምም። እሺ? ከሚጣበቀው ቁስ ጋር ተመሳስሎ መጣበቅ አለበት። ልክ ነው። ልትጨምሩት ይገባል። በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መታገስ ነው። አዎን፡ ታገሱ። ኖህ አመነ። በእግዚአብሔርም ፊት፡ መቶ ሃያ ዓመት ታግሦአል።

256 ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ታግሷል። አዎን፡ ታግሷል። “ሙሴ፡ የሕዝቤን ጩኸት ሰምቻለሁ። መከራቸውን አይቻለሁ። ነጻ ላወጣቸው እወርዳለሁና። አንተን እልክሃለሁ።”

257 እና በእርሱ እና በእግዚአብሔር መካከል ትንሽ ንግግር ነበር፡ እግዚአብሔርም ክብሩን አሳየው። እርሱም “እነሆ እሄዳለሁ፡” አለ። የእግዚአብሔርን ክብር ፈጽሞ ባየ ጊዜ፡ በቃ፡ እምነት አገኘ።

“ሙሴ ሆይ በእጅህ ያለው ምንድን ነው? ” አለው፤

“በትር ናት፡” አለ።

እርሱም “ወደ መሬት ጣላት፡” አለው።

በትሩም እባብ ሆነች። “ኡህ፡ ማይ!” አለና፡ ጉዞውን ቀጠለ…

258 “ወደ እባብ መቀየር ከቻልኩ፡ እንደገና መመለስ እችላለሁና። ሙሴ ሆይ፡ በትርህን አንሳ፡” አለው።

259 አህ! አሜን! እግዚአብሔር ፍጥረታዊ ሕይወትን ከሰጠኝ፡ መንፈሳዊ ሕይወትን ሊሰጠኝ ይችላል! እግዚአብሔር የመጀመሪያ ልደትን ከሰጠኝ፡ ዳግም ልደቱን ሊሰጠኝ ይችላል! አሜን! እግዚአብሔር **ይህንን** ከፈወሰ፣ በመለኮታዊ ፈውስ፣ በመጨረሻው ቀን ለክብሩ ያስነሳዋል። ልክ ነው።

260 “ይህን በትር ወርውሬ ወደ እባብ ልለውጠው ችያለሁ። ወደ በትር ልመልሰው እችላለሁ። በጅራቱ በኩል አንሳው።”

261 ሙሴም ወርዶ አነሳው። ወድያውም፡ በትር ሆነች። አያችሁ? እውቀት መጨመር ጀመረ።

“አሁንም፡ ሙሴ ሆይ፡ እጅህ ምን ሆነች? ”

“ምንም።”

“ብብትህ ውስጥ አርጋት።”

262 “እሺ፡ አሁንስ… ” እንደ ለምጽ ነጣች። “ጌታ ሆይ፡ እጄን እያት!”

“ሙሴ ሆይ፡ ብብትህ ውስጥ መልሳት።”

263 እሱም **እንዲሁ** እዚያው አስገባት፡ እንደ ቀድሞ ሆነች… **እንዲህ** እያለ፡ አንድ በአንድ፡ መጨመሩን ጀመረ። አዎን፡ ጀመረ።

264 ወደዚያም ወረደ። ወደዚያ በሄደ ጊዜም… የመጀመሪያው ፍጥጫ ሆነ። ወደዚያ ወጣና፡ “ፈርዖን ሆይ፡ ይህን እንድታውቅ እፈልጋለሁ፡ ‘ሕዝቤን ልቀቅ።’ ይልሃል ጌታ እግዚአብሄር አለው። እግዚአብሔርን ወክዬ መጥቻለሁ። እኔን መታዘዝ አለብህ።”

265 ፈርዖንም፦ “ታዘዘኝ? ማን እንደሆንኩ ገብቶሃል? ፈርዖን'ኮ ነኝ። እኔ ለአንተ ለባሪያ፡ ልታዘዝን?”

266 አዎን፡ “ትታዘዘኛለህ፡ ወይም ትጠፋለህ። የፈለከውን አንዱን ምረጥ።” ለምን? የሚናገረውን ያውቃል። ተልዕኮ ነበረው። ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሮ። ወደዚያ ወርዷልና። እምነት ነበረው። የት እንዳለ ያውቅ ነበር።

“ሂድ ውጣ ከዚህ! እንድታዘዝህ ትፈልጋለህን?”

“አሳይሃለሁ።”

“ምልክት አሳየኝ።”

በትሩን ወደ ታች ወረወረ፡ እባብም ሆነች።

267 “ኧረ፡” አለና፡ “ይህ'ማ ተራ የአስማተኞች ዘዴ ነው! ወደዚህ ቅረብ። እያንኔስ፡ አንተም፡ እያንበሬስ፡ ወደዚህ ኑ፡ በትሮቻችሁን ጣሉ።” እነርሱም ወደ ታች ወረወሯቸው፤ እባብም ሆኑ።

268 ንጉሱም፦ “አሁን አንተ የማትረባ፡ ወደ እኔ፡ ወደ ግብጻዊ ሰው፡ ያውም ወደ ግብፅ ፈርዖን፡ እኮ ነው የመጣኸው። የመጣኸውም የማይረባ ቀልድ፡ እና ተራ አስማት ይዘህ ነው፡” አእምሮን-የማንበብ ብቃት፡ ታውቃለህ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቶሃል። ስለ እሱ እያነበብክ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። “አእምሯዊ ቴሌፓቲ ወይም የሆነ ነገር፣ እየህ፣ እዎ፣ እነዚህን እና ጥቂት ነገሮችን ይዘህ መጥተሃል።” “ይህም፡ አንተ የምታደርገው ነገር ማድረግ እንችላለን፡” አለው።

269 ሙሴ ምን አለ? “ኦህ፡ አቶ/ ፈርዖን፡ ይቅርታ—እጠይቃለሁ፡ ጌታዬ፡ ከእንግዲህ፡ ባርያህ እሆናለሁ።” በፍጹም፡ ጌታዬ።

270 ጸንቶ ቆየ። አሜን። በደረሰበት ጸና። እግዚአብሔር በልብህ ምንም ጥርጣሬ አይኑር፦ “ዝም ብለህ ጠብቀኝ። የሆነ ነገር አሳይሃለሁ፡” አለው። አድርግ ያለህን በትክክል አድርገህ፡ የተሳሳትክ ሲመስል፡ ጽና፡ ዝም ብለህ ታገሥ።

271 ሙሴም፦ “ሰማኝ፡ መስረቱን በጣልኩት ቀን፡ ትዕግስትም አብሮ ጥያለሁ፡ ስለዚህ ዝም ብዬ እጠብቃለሁ እግዚአብሔር የሚያደርገውም አያለሁ አለ።”

272 እባቦቹ እየተሳቡ፣ እየተነፉ፣ እና እርስ በርሳቸው እየተፎካከሩ ነበር። እንደምታውቁት በመጀመሪያ፡ የሙሴ እባብ ሄዶ፡ “ዋጥ፡ ዋጥ፡ ዋጥ፡” ሁሉንም ዋጣቸው። ታግሷል።

> እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ፡ኃይላቸውን
>   ያድሳሉ፡
> እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ።

ልክ ነው? አይደል? አዎን።

> ይሮጣሉ አይደክሙም፡ ይሄዳሉ አይታክቱም።

አስተውል፣ ጌታን ብቻ ጠብቅ። ትዕግስት ይኑርህ። ገባህ? አዎን፡ ይኑርህ።

273 እስራኤል ሊዋጥ ተቃረበ። ታላቅ ተግዳሮት ተነሳበት፡ ሙሴ ግን ጠበቀ።

274 ከዚያም ወደ በረሃ ገባ። የሶስት- ወይም የአራት-ቀናት ጉዞ ብቻ ነው. ልክ እንደገና እስከተሻገሩበት ቦታ ድረስ፡ ከተሻገረበት ቦታ አርባ ማይል ርቀት ብቻ ነው። ሙሴ ግን፡ በምድረ በዳ፡ አርባ ዓመት፡ ጠበቀ። ታገሰ። ኣሜን። ትክክል። አርባ አመት ጠበቀ። ኦህ! አዎን፡ ወዳጄ።

275 እርሰ በርሳችንም ትዕግስት ሊኖረን ይገባል። እሺ? እንደው… አንዳችን ለሌላው—በጣም ትዕግስት ይጎድለናል። እንደ ሙሴ መሆን ያለብን ይመስለኛል። ሙሴ ህዝቡን እጅግ ታግሷቸዋል። እንዳይሻገሩ ተግዳሮት የሆነባቸውም፡ ይህ ነገር ነው። አያችሁ? አንዳች ነገር ማድረግ ስትፈልጉ…

276 ማለት፡ የዚህ ጉባኤ አባል ሁሉ መልዕክቱን እንዲመስል፡ በማሰብ እኔ **ይህን** መልዕክት በጉባኤው ውስጥ ሰርጾ ለማየት እተጋለሁ። እጅግ ከባድ ነው። ላለፉት ሰላሳ-ሶስት አመታት፡ ለመታገሰ ተግቻለሁ። እናንተም ትዕግስት ይኑራችሁ። እሺ? እስከ አሁን ድረስ፡ ሴቶች ጸጉራቸውን ይቆራርጣሉ። በቃ ታገሰ ትእግስት ይኑርህ። ገብቶሃል? ታጋሽ ሁን። ጠብቅ። ይኑርህ። ከሌለህ ግን፡ **እነዚህን** ነገሮች ለመገንባት አትሞክር። ታጋሽ ሁን።

277 አንድ ጊዜ እንኳን፣ አመፀኞቹ ትዕግስት አልባ ሰዎች እንደዚህ ያለ ነገር ባሳዩት ጊዜ፣ ሙሴ ስህተት እንዲሠራ አድርገውታል። በዚህ ሁሉ፡ ግን፡ ወደ ፍርድ ሚዛን ሲመጣ፡ እግዚአብሔር በተግባራቸው ተቆጥቷል። “ሙሴ ሆይ፡ እራስህን ለይልኝ። ሙሉውን እገድላቸዋለሁ፡ እንደ አዲስ እጀምራለሁ፡” ብሎት ነበር።

278 ሙሴ ግን ክፍተታቸው ላይ እራሱን ጥሎ፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ አይሆንም፡” አለ። ምን? በእርሱ ላይ ያመፁትን ሰዎች ታግሷችኋል።

279 እኛ ይሄን ማድረግ እንችል ይሆን? ሰማኝ፡ አንተ ካልቻልክ፡ **ይሄን** ለመገንባት አትሞክር፡ ፈጽሞ—ለውጥ አይኖረውም። እንደኛው በዚህ መንገድ ነው **ወደዚህ** የተጣበቀው፡ ሌሎቹ ሁሉ መጣበቅ ያለባቸውም በዚሁ መንገድ ነው። ታጋሽ ካልሆንክ፡ የህያው እግዚአብሄር ፍጹም ቁመና ያለው ማደርያ ለመሆን አትበቃም፡ ትዕግስት ከሌላችሁ፡ አንዳችሁ ለሌላው፡ ትዕግስት ይኑር። እሺ።

280 የዕብራውያኑ ልጆች ትዕግሥት ነበራቸው። አዎን፡ ነበራቸው። እግዚአብሔርም ተሰፋ ሰጥቶ፡ “ለማንኛውም ምስል አትስገዱ፡” ብሏቸው ነበር። እነርሱም ትዕግስትም ነበራቸው። “አምላካችን ያድነናል። ባያድነን ግን፡ ላቆከው ምስል፡ አንሰግድም፡” አሉ። በትዕግስት፡ እግዚአብሄር በዘመን ፍጻሜ እንደሚያስነሳቸው፡ አውቀዋል።

281 በመሰረቱ፡ ይህ ህይወት ምንም አይደለም። በዘመን ፍጻሜ እግዚአብሄር ያስነሳዋልና። አያችሁ? ለምስል ሰገድ የሚል ሲመጣ ግን፡ አናደርገውም። የቄሳር የሆነውን፡ ለቄሳር እንሰጠዋለን፡ በእግዚአብሔር ጣልቃ ለመግባት፡ ቄሳር ሲመጣ ግን፡ እግዚአብሔርን እናሰቀድማለን።

282 “እግዚአብሔርም፡ ‘ለማንኛውም ምስል አትስገዱ ብሎናል።’ እኛም አንሰግድም። አምላካችን ሊያድነን ይችላል። ባያድነኝ ግን፡ እኔ ለምስሉ አልሰግድም።”

“ይሁና፡ ምድጃው ተዘጋጅቶላችኋል፡” አላቸው።

283 "እሺ፡" አላቸው፡- "እንደው፡ ዛሬ፡ ከፍተኛ ዝናብ ቢዘንብ ያጠፋላችሁ ነበር።" ዝናብ ግን የለም አላቸው። አሁንም ታገሱ።

284 በማግስቱ ጠዋት፡ ወደ ቅጥር ግቢው ሲወሰዱ፡ ናቡከደነፆር ተቀምጧል። "እሺ ልጆች፣ እኔን እንደ ንጉስ፡ ልታውቁኝ ዝግጁ ናችሁ? " አላቸው፤

"አለጥርጥር። ንጉሥ ሆይ፡ ሺ ዓመት ንገስ።"

"አሁን ለምስሌ ስገዱ።"

"በፍጹም፡ አንሰግድም።"

285 "እንግዲያውስ፡ ትቃጠላላችሁ። ጥበበኛ ሰዎች ናችሁ። ብልህ ናችሁ። ለእኛ በብዙ ረገድ ረድታችሁናል። ለመንግስታችን በረከት ነበራችሁ። መቼም ይህን ማድረግ እንደማልፈልግ ይገባችኋል? ነገር ግን—አዋጅ አስነግሬለሁ፡ መፈጸም ደግሞ አለበት። ወደዚያ መወርወራችሁ ፍላጎቴ አይደለም ምነው፡ እናንተ ልጆች፡ ምን ነካችሁ? "

286 "ጥሩ ምክር እንደሆነ ይገባናል። ይሁን እንጂ፡ አምላካችን ሊያድነን ይችላል። ባያድነንም ግን... " ታገሰ።

287 መወጣጫውን መውጣት ጀመሩ። አንዱ ሌላውን ተመለከተ። "አይዞህ። አይዞህ ተባባሉ።" ታገሱ። አንድ ደረጃ ወጡ፡ እግዚአብሔር በዚያ አልነበረም። ሁለት ደረጃ፡ በዛም አልነበረም። ሶስት ደረጃዎች፡ አራት ደረጃዎች፡ አምስት ደረጃዎች፡ መሄዳቸውን ቀጠሉ፡ አሁንም አልነበረም። ወዲያውም ወደ እቶን ውስጥ ገቡ። ትዕግስት ነበራቸው። ያኔ በዚያ ውስጥ ተገኘ። አያችሁ? እጃቸውና እግራቸው የታሰሩበትን ማሰርያ፡ለማቃጠል የሚችል በቂ እሳት ነካቸው። የጉድጓዱን ወለል በነኩ ጊዜ ግን፡ እሱ ተገኘላቸው። አያችሁ? ታግሷልና።

288 ዳንኤልም እንዲሁ። ዳንኤል ትዕግስተኛ ነበር። አዎን። ተሰፋ አልቆረጠም ነበር። በፍጹም፡ አልቆረጠም። ምን ያደርግ ነበር? በእግዚአብሔር ፊት መሰፈርቱ ነበርና። እንዲሁ፡ መስኮቶችን ከፍቶ ይጸልያል። ትግስተኛ ነበር። እግዚአብሔር ቃሉን መጠበቅ እንደሚችል አውቆ፡ እግዚአብሔርን ጠበቀ። "አንበሶች እንዲበሉህ አዘናል፡" በማለት፡ በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት።

289 እሱም "ይሁና፡" አለ። ታገሰ። ለምን? "ይሄን ያህል ዘመን፡ አምላኬን፡ ጠብቄአለሁ። ጥቂት ተጨማሪ ሺህ ዓመታት መጠበቅ ካለብኝ፡ በመጨረሻው ቀን እንደገና እነሳለሁ። ስለዚህ፡ ታገሰ፡ ጠበቀ።"

290 ጳውሎስ ትዕግስተኛ ነበር። ታጋሽ ነበር። ጳውሎስ ያደረጋቸውን ነገሮች ተመልከቱ። ስለ ትዕግስት ካላችሁ!

291 የበዓለ ኃምሳው ሰዎችስ? አደራውን እስኪቀበሉ ድረስ፡ "በትዕግስት፡ ጠብቁ፡" "ሐይል እስክትቀበሉ ድረስ ጠብቁ፡" ተባሉ። እስከ መቼ? ምንም ጥያቄ አልነበራቸውም፡ "እስከመቼ ይቆያል? " ያገኙት መልስ "በትዕግስት፡ ጠብቁ፡" የሚል ብቻ ነበር።

292 ወደዚያ ወጡና እንዲህ አሉ። "እሺ እንግዲህ፡ ልጆች፡ ምናልባት ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ ሊመጣ ይችላል ከዛ በኋላ አገልግሎታችንን እንቀበላለን።" አሥራ አምስት ደቂቃ አለፋ፡ ምንም የለም። አንድ ቀን አለፈ፡ የለም፡ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት።

293 አንዳንዶቹ “እናንተ ሰዎች፣ ያገኘነው አይመስላችሁም? ” ያሉ ይመስለኛል።

“በቃ፣ በቃ፣ በቃ፣ ይበቃናል።” እንዴ። አሁን። በቃን።

294 “እናንተ ሰዎች፡ አሁን ብንወጣ ይሻላል።” ዲያብሎስ ሹክ ብሎ፡- “ታውቃላችሁ—አሁን’ኮ—የምትፈልጉትን አግኝታችኋል። አሁን ውጡና፡ አገልግሎታችሁን ፈጽሙ።”

295 “አይ፡ አይ፡ አይደለም። እስከ አሁን ድረስ፡ አልተቀበልንም። ምክንያቱም፡ እሱ ሲናገር ‘በመጨረሻው ቀን የሚሆነው ነገር ይመጣል፤ ዕረፍት ይህች ናት፡ በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ህዝብ እናገራለሁ፡ ያልኩት ይህ ነው፡’ እያችሁ፡ በኢሳይያስ 28:19።” የተባለው፡ “ይህ ነው—ይህ ነው—ሲወርድ እንቀበላለን... ምክንያቱ፡ እርሱ ሲወርድ፡ እናውቀዋለን። ሲመጣ እናውቀዋለን። ‘የአብ ተስፋ፡’” ሲመጣ ይታወቃል። ዘጠኝ ቀናት ጠብቀዋል። አስረኛው ቀን ላይ፡ “አብረን ሳለን።” ጠብቀዋል፡ ትእግስት አላቸው።

296 እግዚአብሔር ቃል ከገባላችሁ በኋላ፡ እናንተም ከመጽሐፍ ቅዱስ አውቃችሁት፡ እንዲህ አይነት ትእግስት ካገኛችሁ፡ “የኔ ነው፡” ብላችሁ ያዙት። ከዛ በኋላ፡ እንዲህ አይነት ትእግስት ስታገኙ፡ በእምነታችሁ ላይ ጨምሩት። ምን ያህል እያደጋችሁ እንደሆነ አይታችኋል? አሁን **ወደላይ** እያደጋችሁ ነው። እሺ። የእጅ ሰዓታችሁም፡ እንዲሁ እየዞረ ነው፡ አይደል’ዴ? እሺ። እሺ። እምነታችሁ ላይ ጨምሩት።

297 ተስፋ የሰጣችሁ እርሱ እንደሆነ፡ እያሰባችሁ፡ ዘወትር እርሱን አስቀድሙት። የተስፋው ቃል፡ ከኔ አልተሰጣችሁም። የተስፋው ቃል፡ ከወንድማችን፡ ከፓስተር ነቪሌ አልተሰጣችሁም። የተሰፋው ቃል የሰጣችሁ፡ አገልጋይ አይደለም። ከካህን ወይም ከጳጳስ አልተሰጣችሁም። ከምድራዊ ሰው ዘንድ አልመጣም። የተሰፋው ቃል የሰጠ እግዚአብሔር ነው፡ እግዚአብሔርም የገባውን ቃል ሁሉ ሊፈጽም ይችላል። እሺ። የተሰፋው ቃል ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደተሰጣችሁ በማወቅ፡ እንዲህ አይነቱ እምነት ከያዛችሁ! “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አሞኛል። ፈውስ እጅግ ያስፈልገኛል፡” ብላችኋል። የእናንተ ነው ተቀበሉ። አዎን፡ ወዳጆቼ፡ ካመናችሁ ስጦታው የእናንተ ነው፡ ስጦታችሁ ነው። “ስለዚህ፡” “አምኛለሁ፡” በሉ። ከዚያ እርሱት። በቃ። ያበቃለታል። እያችሁ?

298 ትዕግስት ካገኛችሁ፡ ትዕግስትን ያዙ። እያችሁ፡ ካልያዛችሁ ግን፡ ከዚህ ህንጻ ፈራርሳችሁ እንደመውረድ ነው። አንዷ ነገር፡ ሌላውን ሁሉ ይዛው ትወድቃለች። ሊኖራችሁ ያስፈልጋል። ትዕግስት ከሌላችሁ፡ በእምነታችሁም ላይ፡ የምትጨምሩት በጎነት ከሌላችሁ፡ የገነባችሁትን ሁሉ ይዞ ስለሚወርድ ሌላ ለመጨመር አትሞክሩ። እምነት ሳይኖራችሁ፡ በጎነት ለመገንባት ብትሞክሩም፡ እምነታችሁን ሁሉ ይሰባብርባችኋል። እያችሁ? እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ “እንዴ፡ ቆይ እስኪ፡ እንዴት ነው ነገሩ። ስጀምርም፡ ተሳስቻለሁ። ምናልባት እግዚአብሄር እግዚአብሄር አይደለም። ምናልባት እግዚአብሄር ላይኖር ይችላል።” ህንጻችሁ፡ ለሁለት ይሰነጠቃል። ገባችሁ?

299 እውነተኛ እምነት ኖሯችሁ፣ እውነተኛ በጎነት ጨምሩበት፣ በላዩም እውነተኛ ዕውቀት፣ እውነተኛ ራስን መግዛት፣ እውነተኛ ትዕግስት ጨምሩ። እሺ? መሰመሩን ይዛችሁ ወደ ላይ ታድጋላችሁ። በጣም ጥሩ።

300 አምስተኛ እግዚአብሔርን መምሰል ጨምሩ። ኦህ፡ ማይ! እግዚአብሔርን መምሰል ይጨመርበታል። እግዚአብሔርን መምሰል ምን ማለት ነው? አራት ወይም አምስት መዝገበ ቃላት ፈትሼ ምን ማለት እንደሆነ ማግኘት አልቻልኩም። በመጨረሻም፣ ወንድም ጄፍሪስ ጋር ወርጄ ነበር፣ መዝገበ ቃላት ውስጥ—አገኘነው። **እግዚአብሔርን መምሰል** ማለት “እንደ እግዚአብሔር መሆን።” ማለት ነው። ኦህ፡ ማይ! እምነትን፣ በጎነትን፣ እውቀትን፣ ራስን መግዛትን፣ ትዕግስትን፣ ከዛ እንደ እግዚአብሔር መሆን። ዋው!

301 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኔ እንደዛ መሆን አልችልም፡” ብላችኋል። ኧረ፡ አዎን፡ ትችላላችሁ።

302 ለጥቂት ደቂቃዎች፡ ጥቂት ቃላት ላንብብላችሁ። ማቴዎስ 5፡48። ይህንን ማቴዎስ 5፡48 ወሰደን፡ ምን እንደሚመሰል ተረድተን፣ እንደ እግዚአብሔር መሆን ካለብህ እንመለከታለን። በመጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ ሲናገር፡ “እናንተ አማልክት ናችሁ።” እንዳለ ታውቃላችሁ። ለምን? በጎነት ሁሉና፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኝ ሁሉ በእናንተ ውስጥ ስላለ። ማቴዎስ 5፡48፣ “የሰማይ አባታችሁ… ” ኢየሱስ ለብፁዓን፡ ሲናገር።

> **የሰማይ አባታችሁ** ፒ-ኢ-አር-ኤፍ-ኢ-ሲ-ቲ፡ (ምን ሁኑ? ) **የሰማይ አባታችሁ**… **ፍጹም እንደሆነ፡ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።**

303 እንግዲህ ሳይጠይቃችሁ፡ እጅግ **ላይ** ትወጣላችሁ። ከሁሉ በፊት እነኚህ ነገሮች መጨመር አለባቸው። እዚህ ላይ ስትደርሱ፡ ያኔ እግዚአብሄርን የሚመሰሉ፣ ፍጹማን፣ ሴቶች እና ወንዶች የእግዚአብሄር ልጆች ሁኑ ይላችኋል። ትክክል ነው። በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ነገር ማለት እችላለሁ!

304 ወደ ኤፌሶን ሰዎች ምዕራፍ 4 እንመለሰና፡ በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ፡ ስለዚህ ነገር፡ እንዴት ማድረግ እንዳለብን፡ እና፡ ምን እንደሚል—እንወቅ። ኤፌሶን ምዕራፍ 4፡ ከ12ኛው ቁጥር ጀምሮ። ኤፌሶን 4፡ ከ12ኛው ቁጥር ጀምሮ። እሺ። ከ11ኛው ቁጥር እንጀምር።

> **እርሱም እንዳንዶቹ፡ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣**…

305 ትናንት የነበረው አስታወሳችሁ? የሌላ ሰው ጥሪ ለመውሰድ አትሞክሩ። ትዝ አላችሁ?

> **ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣** ሌሎቹም፣ **እረኞችና… አስተማሪዎችም፡ እንዲሆኑ ሰጠ፤**

306 “እግዚአብሄርን ፍጹም ለማድረግ”? ይላል እንዴ? [ጉባኤው “አይልም፡” አለ—አርታዒ።] ማን ፍጹማን ለማድረግ ይላል? [“ቅዱሳንን።”] ቅዱሳን እነማን ናቸው? የተቀደሱት ሁሉ። አሜን። **ከዚህ** ከታች የጀመሩ ሁሉ።

> **… ቅዱሳንን ፍጹማን ለማድረግ፡ እና አገልግሎትን ለመሥራት** (የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት)፡ **ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ወደ መሆን** (መታነጽ፡ መገንባት፡ እስክንታነጽ)፡ ድረስ…
>
> **ሁላችን የእግዚአብሔርን** ልጅ **በማመንና፡ በማወቅ… ወደሚገኝ አንድነት፡ ሙሉ ሰውም** ወደ መሆን፡ **ወደ** ማረጋገጫው፡ (ኦህ፡ ማይ) ወደ **ክርስቶስ ሙላት ወደመሆን፡ ፍጹም ወደሚሆን ቁመናው፤**

307 “ፍጽምና፡” እግዚአብሔር መምሰልን ይጠይቃል። ስለዚህ በእምነት እግዚአብሔር መምሰልን መጨመር አለባችሁ። እነሆ፡ **ከዚህ** በበጎነት ትጀምራላችሁ። ከዚያም ወደ እውቀት ታድጋላችሁ። ከዚያም ራስን ወደ መግዛት። ከዛ ወደ ትዕግስት። አሁን እግዚአብሄር መምሰል ላይ ናችሁ። እግዚአብሄርን መምሰል! ኦህ፡ ማይ! ጊዜያችን እያለቀ ነው። እንቀጥል። እግዚአብሄርን መምሰል ምን ማለት እንደሆነ አውቃችኋል። ይሄን መዝሙር ትዘምራላችሁ፡

እንደ ኢየሱስ መሆን፣ እንደ ኢየሱስ መሆን፣
ምድር ላይ እንደ እርሱ መሆን እመኛለሁ፤
በሕይወት ጉዞ ሁሉ ከምድር ወደ ክብር
እንደ እርሱ መሆን ብቻ እሻለሁ።

308 እግዚአብሔርን መምሰል እንዲህ ነው። ፊቱን በመቱት ጊዜ፡ ሁለተኛውም አዞረ። ሲሰድቡት፡ ክፉ አልመለሰላቸውም። በሰድብ አልመለሰም። አያችሁ? አምላካዊነት፣ ሁል ጊዜ አንድን ነገር ይሻል፡ “ሁልጊዜ አብን ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁ።” አይልም? አዎን፡ ይላል። ዘወትር። እግዚአብሔርን መምሰል ይህ ነው። አይደል?

309 ከዚህ ጀምራችሁ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህ**፣ **ወደዚህና**፣ **ወደዚህ** ከደረሳችሁ በኋላ፡ ያኔ ወደ እግዚአብሄር ልጅ ቁመና ወደ ሙላቱ ትደርሳላችሁ። ከሁሉ በፊት ግን **እነዚህን** ሁሉ ጨምራችሁ፡ **ይሄኛው** ሊኖራችሁ ያስፈልጋል፡ እና **ይሄኛው** እስኪኖራችሁ ድረስ ገና አላገኛችሁትም።

310 የፒኮክን ላባዎች የሚሰካውን ጥቁሩን ወፍ አስታውሱት። እንዳትረሱት። እሺ? ዳግም እስክትወለዱ ድረስ ለመጨመር አትጋጋጡ። አያችሁ፡ ለእናንተ፡ አይሰራም፡ እናንተም—እንዲሰራ ማድረግ አትችሉም። **እዚህ** ድረስ፡ ወይም **እዚህ** ድረስ ደርሶ፡ ይፈራርሳል።

311 ነገር ግን **እዚህ** ጋር፡ ዳግም-የተወለዳችሁ እርግቦች ስትሆኑ፡ የምትጨምሩት ነገር አይኖርም። አያችሁ፡ አሁን፡ ወደ ፍጽምና እየወጣችሁ ነው፡ ማለት፡ እራሱ በእናንተ ላይ ይጨምራል። እሺ።

312 ከዚያም፡ ሰድስተኛው፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ጨምሩ ያለን ነገር፡ የወንድማማች መዋደድ... ወንድማዊ ደግነት። ይሄኛው፡ ሰድስተኛ፡ ማለት ሰባተኛው፡ ይሄ፡ በጣም ደስ ይላል። የወንድማማች መዋደድ ጨምሩ ይላል። በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ። ወደዚህ ወንድማዊ መዋድድ ከደረሰን በኋላ፡ በሚነሳው ነገር ላይ፡ እራሳችሁን በቦታው ትተካላችሁ። እንዲህ በማለት...

313 ጴጥሮስ ሲናገር፡ “ወንድሜ ቢበድለኝ።” “ስንቴ ይቅር ልበለው፡” “በቀን ሰባት ጊዜን? ” ብሎ በጠየቀ ጊዜ፤

“ሰባ ጊዜ ሰባት፡” ብሎታል። አይደል?

314 ወንድማዊ መዋደድ። ሰሙኝ፡ አያችሁ፡ አንድ ወንድም፡ መስመር ከሳተ፣ ለመታገስ አትድከሙ። እሺ? አትድከሙ። እሺ? ራሩለት። እና፡ መንገዳችሁን ቀጥሉ።

315 በቅርብ ጊዜ፡ አንድ ሰው እንዲህ አለ፡- “ወደ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ እና ወደ ዋንነስ፡ እና ሌሎች ዘንድ፡ የምትገባ ከሆነ፡ እንዴት አማኝ ነኝ ትላለህ? ”

ሲላችሁ፡ አያችሁ፡ ወንድማዊ መዋደድ ጨምሩ። አያችሁ? አያችሁ? ራስ ከመግዛት ጋር፡ ታገሱት፡ እሺ፡ ተሸከሙት፡ ምናልባት፡ አንድ ቀን፡ የሚያምነው ነገር ለመረዳት፡ እውቀት ሊያገኝ እንደሚችል፡ አሰቡ፡ በልቡ ውስጥ ያለው ነገር፡ በጎነት፡ በእናንተም ዘንድ ያለው፡ ደግሞ ያው ነውና፡ በደግነት፡ በትሕትና አቅኑት፡ አንድ ቀን እግዚአብሄር እንደሚገልጥለት እያሰባችሁ ራሩለት። እሺ?

316 ሰባተኛው ደረጃ፡ የወንድማማች መዋደድ ነው። አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ ሰድስት፣ ሰባት። [ወንድም ብራንሃም በሰሌዳው ላይ ሰባት ጊዜ መታ—አርታዒ።] ሰባተኛውን፡ እዩት። ይህ ሲሆን፡ ነገሩ ላይ፡ እየደረሳችሁ ነው።

317 ከዚህ ሁሉ በኋላ፡ የሚከተለው፡ ቸርነት ጨምሩ፡ እርሱም ፍቅር ነው። ከነዚህ ቀናት አንድ ቀን፡ በቤተ ክርስትያን...

318 አሁን፡ የምናገረው ነገር፡ በቴፕ ለሚሰሙት፡ እና ለሌሎች ሁሉ እማጸናለሁ፡ አሁን የምናገረው ይህ ነገር፡ እንደ ዶክትሪን ለማስተማር አይደልም። ነገር ግን በእግዚአብሄር እርዳታ፡ ላሳያችሁ የምፈልገው፡ እግዚአብሄር፡ በመጀመርያ የጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ፡ ሰማይ ላይ በዞድያክ ላይ ነበር። በቬርጅን ይጀምራል። በሊዮ ይደመድመዋል እርሱም ላየንን ነው። ሰድሰተኛውን እና ሰባተኛውን ማሕተም ወደ መፍታት ሰደርሰ፡ ሌላኛውን ማሕተም፡ ሲከፈት ታዩታላችሁ፡ የዚያ ቦታ የዞዲያክ ምልክት ክሮሰድ ፊሽ፡ የሆነው ካንሠር ይባላል። ይህም ይህ አሁን እኛ እየኖርንበት ያለውን የካንሠር ዘመንን፡ ይገልጣል። ከዚያ ቀጥሎ ማኅተሙ ሲቀደድ የሚታየው፡ አንበሳ የሆነው ሊዮን ነው፡ ይህም የክርሰቶሰን ዳግም ምጽዓት ያሰረዳል። በፊተኛው፡ ሲመጣ፡ ወደ ድንግል መጣ፡ በሁለተኛው፡ ሲመጣ፡ እንደ አንበሳ ሆኖ ሊዮ ሆኖ ነው። ይህን ወደ ምን ያደርሳል...

319 አሁን፣ ዛሬ ጠዋት ጊዜ ይኖረኝ አይኑረኝ አላውቅም። ነገር ግን እዚህ የተዘረዘሩ ነገሮች፡ በትክክል ፒራሚድ ላይ እንድሚገኙ፡ ለእናንተ ለማሳየት የሚቻለኝን አደርጋለሁ፡ በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሄር መጽሀፍ ቅዱሰ ሲጽፍ። በሄኖክ በኩል ፒራሚድ ላይ ነው።

320 በሶሰተኛ ደረጃ፡ የእግዚአብሄር ነገር ሁልጊዜ በሶሰት እንደሚጸና ሁሉ፡ እራሱን ቃል አደረገ።

321 ሰለዚህ፡ አሁን፡ አሰታውሱ፡ ፒራሚዱ ውስጥ... ብዙዎቻችሁ በተለይ ዘማቾች የሆናችሁ ግብጽ እንደነበራችሁ አሰባለሁ። በፒራሚዱ ራሰ ላይ መደምደሚያ የለውም። አልነበረውም። ራሰ ከሆነው—የማዕዘን ድንጋይ በሰተቀር፡ ሌላው ሁሉ አለ፡ እሰከ አሁን...

322 ኪሳችሁ ውሰጥ አንድ ዶላር ኖት ካለ፡ የዶላሩ ኖት ተመልከቱት፡ በቀኝ በኩል፡ ከአሜሪካው ሰንድቅ ጋር፡ ንሰር ተሰሎ ታያላችሁ። "የዩናይትድ ሰቴትሰ ማሕተም፡" የሚል ማሕተም፡ ተጽፎበታል። በሌላኛው ጥግ፡ በውሰጡ የሰው አይን ያለበት፡ ግዙፍ የድንጋይ ኮፍያ ይታያል። በዚህኛው ጥግ "ታላቁ ማሕተም፡" የሚል ተጽፎበታል። እሺ፡ ይህ ታላቅ ህዝብ ከሆነ፡ ለምን ይህ ታላቅ ማህተም የራሱ የሀገር ማህተም አይሆንም? የትም ቢሄዱ፡ እግዚአብሔር እንዲመሰክሩ ያደርጋቸዋል።

323 አንድ ጊዜ ከአንድ ዶክተር ጋር፡ ስለ መለኮታዊ ፈውስ እየተነጋገርን፡ እኔን ከሰል እንደሚንከባለል ጥላሸት ይቀባኝ ጀመር። መንገድ ዳር ቆመን ነበር። እና፡ “አቶ/ ብራንሃም አንተ’ኮ ሰዎችን ግራ ማጋባት ብቻ ነህ።” “በመድኃኒት ካልሆነ በቀር፡ ፈውስ ብሎ ነገር የለም፡” አለኝ።

324 ፊቴን ዞር አርጌ፡ በመኪናው ላይ የተለጠፈው፡ ምሰሶ ላይ የተሰቀለውን የእባብ ስዕል ያለበትን ምልክት አየሁ። “እንዲህማ ከሆነ በመኪናህ የሰቀልከው ምልክት ማንሳት አለብህ፡ የገዛ ማስታወቂያህ፡ እግዚአብሄር ፈዋሽ መሆኑ ይመሰክራልና፡” አልኩት።

325 እውነተኛ ዶክተር ይህን ያምናል። ነገራቸው ፋከራ ነው። አዎን፡ ጓዴ። ምሰሶው ላይ የሚታየው እባብ! ሙሴ እባብን በእንጨት ላይ ሰቀለ። “ደዌህን ሁሉ የምፈውስ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡” አላቸው። ህዝቡም ስለ መለኮታዊ ፈውስ እባቡን ያዩ ነበር። የገዛ ምልክቶቻቸው እየተቃወማቸው፡ ልክ አይደለም ይሉታል። ዋው!

326 እዚህም፡ በአገራችን ውስጥ፡ እንዲህ ነን የሚሉት ነገር ይታያል፡ ይሁን እንጂ ይሳለቁበታል፡ ገንዘባቸው፡ እና ምንዛሬአቸው፡ የዓለም ሁሉ ማሕተም እግዚአብሄር እንደሆነ ይመሰክራል። በአንድ ዶላር ኖት ላይ የሚታየው አይን፡ ይታያችኋል? ታላቁ ማሕተም እሱ ነው።

327 ፒራሚዱ ላይ በፍጹም ተቀምጦ አያውቅም። ለምን እንደሆነም አይገባቸውም። የመአዝን ድንጋይ፡ ራስ የሆነው፡ ክርስቶስ መገፋቱና። አንድ ቀን፡ እንደሚመጣ ያሳያል።

328 አሁን፡ ህንጻው ሲገነባ፡ ከበጎነት… አያችሁ፡ ይህን ቁመና፡ ይህ ግንብ፡ ህንጻው ሲገነባ በመአዝኑ ድንጋይ ይመሰረታል፤ በእምነት፣ በጎነት፣ እውቀት፣ ራስን መግዛት፣ ትዕግሥት፣ እግዚአብሔርን መምሰል፣ የወንድማማች መዋደድ። ይህስ ምን ያደርጋል? እግዚአብሄር ፍቅር ነውና፡ የመአዝን ራስ የሆነውን ፍቅርን፡ እንዲጠብቁ ያደርጋል። እሱም የነዚህን ሁሉ ጥንካሬአቸው ነው፡ ሁሉንም ይቆጣጠራቸዋል። አዎን፡ ወዳጄ። በትክክል።

329 **በዚህች** በኩል፡ **እዚህ** ጋር፡ በመካከል፡ ማለፊን ተመልክቱ፡ እነዚህ ሁሉ ስራዎች ላይ፡ ሞገድ መሳይ ነገሮች ሲመጡ ይታያሉ። ምንድነው? በክርስቶስ በኩል የሚወርድ መንፈስ ቅዱስ፡ ነው። መንፈስ ቅዱስ! መንፈስ ቅዱስ **ከዚህ** ሁሉ በላይ ነው፡ ሁሉንም አንድ ላይ እያስተሳሰረ፡ (ምን) ይገነባል? የማአዘን ድንጋይ መጥቶ የሚቀመጥባት፡ ፍጹም ቤተ ክርስትያን።

330 በሌላ በኩልስ ምን እያደረገ ቆይቷል? በሰባቱ የቤተክርስትያን ዘመናት፡ እና ሰባት የቤተክርስትያን መልእክተኞች ሲገለጥ ቆየ።

331 ጅማሬው **ከዚህ** ነው። ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ የተመሰረተችው የት ነበር? የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሰረተው የት ነበር? ኤፌሶን ላይ፡ የኤፌሶን ቤተክርስትያን ዘመን ኮከብ፡ በሆነው በሐዋርያ ጳውሎስ፡ በኤፌሶን ተመሰረተች።

332 ሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ሰምርኔስ ነው። “በጎነት።” የጳውሎስን ወንጌል አደራ ያስቀጠለ ታላቅ ሰው፡ ኢራኒየስ ነበር።

333 የሚቀጥለው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ የማርቲን ጴርጋሞስ ናት፣ ማርቲን ነገሩን ያስቀጠለ ታላቅ ሰው ነበር። ጳውሎስ፣ ኢራኒየስ፣ ማርቲን።

334 በትያጥሮንም ኮሎምባ መጣ። ታስታውሱታላችሁ? ኮሎምባ፡ **እዚህ** ጋር ተሰሏል። ኮሎምባ ይባላል። ከኮሎምባ በኋላ… የጨለማው ዘመን ገባ።

335 ከዚያም **የሞተች** የተባለው፡ ሳርዴስ መጣች። ሉተር ነበር። ሀሌሉያ! ከሉተር በኋላስ? ከሳርዴስ በኋላ፡ ማን መጣ?

336 ፊልደልፊያ መጣች። "እግዚአብሄርን መምሰል።" ዌስሊ፡ ቅድስና ይዞ መጣ! ሉተርም "ጻድቅ በእምነት ይኖራል፡" ይዞ መጥቶ ነበርና። ቅድስና በዌስሊ መጣ።

337 ከዚህ ሁሉ በኋላ፡ በሎዶቅያ በኩል የወንድማማች መዋደድ ገባ። እኛም የኤልያስን በመጨረሻው ቀን ሁለተኛ መምጣት፣ እና ምድሪቱን የሚሞላ ታላቁን መልእክቱን እናምናለን።

338 ሰባቱ አብያተ ክርስትያናት እነዚህ ናቸው፡ ሰባት ደረጃዎች ናቸው። እግዚአብሔርም፡ ቤተክርስቲያኑን እንደ አንድ ሰው፡ እንደ ግለሰብ ወደ ራሱ እየገነባት ነው። ክብሩም፡ የእግዚአብሄር ኃይልም፡ እነዚህ ነገሮች አንድ ላይ በመበየድ፡ **በዚህ** መልኩ ያሳድጋታል። ስለዚህ፡ ሉተራንን፣ እና ዌስሊያውያንን እና ሌሎቹን ሁሉ ያወጡ፣ የጴንጤቆስጤ ህዝብ፡ አያችሁ፡ በቤተመቅደሱ **በዚህኛው** ደረጃ ስለሚኖሩ። አሁን የሚናገሩት ነገር አያዉቁትም። አንዳንድ ሰዎች፡ ወደ ላይ ደርሰው የሚፈጠፈጡት ለዚህ ነው። ይሁን እንጂ ህንጻውን እንዲጨምር የሚያደርጉ፡ እውነተኞች አሏት። ጌታም "እቃናለሁ፡" ብሏልና።

339 **የሙሽሪት ዛፍ**፡ አስታወሳችሁ? ማለት **የሙሽሪት ዛፍ** የሚለውን ስብከት ትዝ ይላቿል? በልተዋት ነበር፡ እሱ ግን ለመለማት። የህይማኖት ተቋማት ቅርንጫፎች በዝተውባት ነበር፡ እሱ ግን አራገፋቸው። ሌላ ቤተ ክርስትያን አሳደጉባት፡ ሌላ የሀይማኖት ተቋም ቤተክርስትያን ቅርንጫፍ አበቀሉባት፡ ሁሉንም አራገፈላት። የዛፊቱ ልብ ግን ያድግ ነበር። "እነሆም ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።" አይደል? ያኔ ክርስቶስ፡ መንፈስ ቅዱስ ይመጣል። ኢየሱስ እራሱ ወርዶ በቤተክርስቲያኑ ራስ ላይ ይቆማል። ቤተ ክርስትያኒቱም፡ የገዛ አካሉ ናትና ያስነሳታል። አካሉ **በዚያ** ውስጥ አለችና።

340 አሁንም እግዚአብሄር ቤተክርስትያኑ ባሳደገባት መንገድ፡ ማለት እኛን ደግሞ በግለ ሰብ ደረጃ እንድናድግ ይጠብቀናል። እያንዳንዷ የቤተ ክርስትያን ዘመን፡ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስትያን ትሆናለች። አያችሁ?

341 **እነዚህ** ሰዎች፡ **እንደነዚህ** እንዲሆኑ አይጠበቅባቸውም። **ይሄኛው** ደግሞ **የዛኛው** ሰው እንድይዝ አይጠበቅበትም። አያችሁ? ቤተ ክርስትያኑን በአንድ መንገድ ያሳድጋታል። ቤተ ክርስትያኒቱን ህዝቡን ባሳደገበት በተመሳሳይ መንገድ—ቤተ ክርስትያንን ያሳድጋታል። ስለዚህም ጴጥሮስ፡ በመጀመርያ፡ ሰባት ነገሮች ይዘረዝራል፤ እምነት፣ በጎነት፣ (እያለ፡ ያድጋል)፡ እውቀት፣ ራስን መግዛት፣ ጽናት፣ እግዚአብሄርን መማአል፣ የወንድማማች መዋደድ፣ እና ወንድማዊ መተሳሰብ፡ ከዚያም በኋላ የእግዚአብሄር ፍቅር። መንፈስ ቅዱስም፡ ማለት ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አካል፡ በእውነተኛው ጥምቀት በኩል፡ ወደ እናንተ ይመጣል፡ በዚህም ምክንያት እነዚህን ጸጋዎች ሁሉ ወደ እናንተ

ይመጣሉ። ያኔ፡ እግዚአብሄር ህንጻው ተብሎ በሚጠራው ውስጥ፡ ማለት የህያው እግዚአብሄር ህያው ማደርያ ውስጥ፡ በድንኳኑ ውስጥ ያድራል።

342 አንድ ሰው እነዚህ ነገሮች በሙላት ሲኖሩት፡ ያኔ መንፈስ ቅዱስ ይመጣለታል። ምንም ያህል፡ በልሳን ብትናገሩ፡ ምንም እንኳን የእግዚአብሄር ስጦታዎችን ብታመሳስሉ። ይህን ማድረግ ትችላላችሁ። ይሁን እንጂ **እነዚህ** ጸጋዎች በእናንተ ላይ እስኪገቡ ድረስ፡ ከትክክለኛው እና፡ ከእውነተኛው መሰረት ትስታላችሁ። እነዚህን ሁሉ ጸጋዎች በእናንተ ላይ በገቡ ጊዜ ግን፡ ዋናውን በዚኢህ ላይ ትጨምሩታላችሁ፡ ያኔ ህያው ማደርያዎች ትሆናላችሁ። ህያዋን እና፡ ተንቀሳቃሽ አማልክት ትሆናላችሁ።

343 እንደምታውቁት፡ ባዕድ—አምላኪዎች፡ በጣኦታት ፊት፡ በምናብ አማልክት ፊት፡ ይሰግዳሉና። በምናባዊ አሰራርም ምናባዊው አምላክ መልሶ እንደሚናገራቸው ያስባሉ። ያ ግን አረማዊነት ነው። ያ ሮማኒዝም ነው። በብዙ ዓይነት ቅዱሳን እና በሌሎችም ሁሉ ፊት ይሰግዳሉ። የቤት አምላክ የሚባለውን፡ ቅድስት ሴሲልያ፡ እና ብዙ የተለያዩ ነገሮች አሏቸው። ይሰግዱላታል፡ በርግጥም—ስለ ሕያው አምላክ ስለ ምሳሌነቱ በማሰብ። በምናባዊ እምነት ያምኑታል።

344 እኛ ግን፡ በምናብ ሳይሆን፡ በሕያው አምላክ ፊት ሕያው በጎነት፡ ሕያው እውቀት፡ ሕያው ትዕግሥት፡ ሕያው እግዚአብሔርን መምሰል፡ ከሕያው አምላክ በሚመጣ ሕያው ኃይል፡ የተሰራው ሕያው ሰው ሆነን፡ የእግዚአብሄር ሕያው ቁመና ምሰል ሆነን በፊቱ እንሰግዳለን። ምን እየሰራ ነው? ኢየሱስ የሰራቸው ነገሮች፡ የተጓዛቸው ተመሳሳይ መንገዶች እየተጓዘ፡ ያደረጋቸውን ተመሳሳይ ነገሮች ያደርጋል። ምክንያቱ፡ ምናባዊ ነገር አይደለም። የሚረጋገጥ እውነታ አለው።

345 አባባሌ ገብቷችኋል? እነዚህ ጸጋዎች፣ እነዚህ የግንባታ እቃዎች፣ ከቤተክርስቲያን መልእክተኞች ጋር፣ ከቤተክርስቲያን ዘመናት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰሉ አይታችኋል? በቅርብ ቀናት፡ እነዚህን ቃላት፡ አንድ በአንድ እያነሳን፡ እናጠናቸዋለን፡ ይህን እንደሚመሰክሩም እናያለን። ሁሉም አንድ ላይ ይስማማሉና። በእውነት። ኦህ፡ ማይ! እነዚህ ጸጋዎች—የሚሰሩት፡ ነገር ምን ያህል ድንቅ ነው። አይታችኋል?

346 ስለዚህ፡ እግዚአብሄር ደወል የተሰቀለበት፡ ረጅም ሾጣጣ ህንጻ ላይ አይኖርም፤ የሚያድርበት ቤት ይህ ነው። "ስጋን ግን አዘጋጀህልኝ፡" አይልምን? ጌታ የሚያድርበት፣ ጌታ የሚመላለስበት፣ ጌታ የሚያይበት፣ ጌታ የሚናገርበት፣ ጌታ የሚሠራበት ስጋ። አሜን! እግዚአብሔር በሁለት እግሮች የሚራመድበት፣ ሕያው የእግዚአብሔር መሣሪያ፣ ትሆናለህ። ክብር! "የጻድቃን እርምጃ ከጌታ ዘንድ የታዘዘ ነው።" ጌታ በአንተ ውስጥ ይራመዳል። "በሰው ሁሉ የምትነበቡ የተፃፋ ደብዳቤዎች ናችሁና።" በክርስቶስ ያለው ሕይወት በእናንተ ውስጥ ቢኖር፡ ክርስቶስ ያፈራውን ያንኑ ህይወት ታፈራላችሁ።

347 ከዚህ በፊትም ተናግሬዋለሁ። የኮክ ዛፍ ፈሳሽ፡ በትራንስፊዩዥን ማስተላለፊያ፡ ወደ አፕል ዛፍ፡ ብታስተላልፉት፡ የአፕሉ ዛፍ ኮክ ያፈራል። ያለጥርጥር። በትክክል ያፈራል። ቅርንጫፎቹ ምንም ቢመስሉ፡ በውስጡ የአፕል ዛፍ፡ ፈሳሽ ወይም የትኛውም ዛፍ ፈሳሽ ይሁን፡ እያችሁ። እያችሁ?

የአፕሉን ዛፍ ህይወት አውጥታችሁ፡ ያለውን ሁሉ ፈጽማችሁ አውጡትና፡ ፈሳሹን—ብትራንስፊውዥን፡ ከኮክ ዛፍ መጥጣችሁ በመሳወጣት ወደ አፕል ዛፍ አስተላልፋት። ምን ይሆናል? ከዛ በኋላ የኮክ ፍሬ አያፈራም። ማለቴ፡ ከዛ በኋላ የኮክ ዛፍ ህይወት ወደ አፕሉ ዛፍ ህይወት ቢገባ፡ የአፕል ፍሬ አያፈራም፡ አያችሁ? ፈጽሞ፡ አያፈራም። በጭራሽ። አያችሁ፡ ኮክን ያፈራል፡ አያችሁ፡ በዛፉ ውስጥ ህይወቱ ይኖራልና።

348 እሺ፡ ወደራሳችን ስንመለስ፡ የዱር ቅል ነን፣ ግትርነት፡ አያችሁ፡ ብቻ ነን፡ ሁላችንም በኃጢአትና በበደላችን ሙታን ነንና። ሁላችንም በዚህ አይነት ሁኔታ ላይ ነን። ከዚያም፡ እግዚአብሔር፡ የደም ማስተላለፊያ ቱቦውን፡ ማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ሰምን፡ ተጠቅሞ፡ የክርስቶስን ህይወት ወደ እኛ እስኪያስተላልፍልን ድረስ፡ “ሰው የሚድንበት ከሰማይ በታች ሌላ ስም የለምና፡” የኛ የሆነውን በመተው፡ በፈቃዳችን መስገድ ይገባናል። ያኔ በክርስቶስ ዘንድ የነበረው **ያ** እምነት፡ እኛም ይኖረናል። የክርስቶስ እምነት የተመሠረተው፡ በፈሪሳውያን፣ በሰዱቃውያን፣ ወይም በምንቸቶቻቸው፣ በድስቶቻቸው፣ መጥበሻቸው፣ ወይም በመታጠቢያቸው አይደለም። በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ነበር፡ አሜን፡ ክርስቶስ ቃል እስኪሆን ድረስ፡ ቃልም ሥጋ እስኪሆን ድረስ፡ የበረታ ነበር። እኛም በኃይሉ እጅግ ስንሞላ፣ ለራሳችን እስተሳሰብ ሞተን፣ እምነታችን እውነተኛ እምነት ሲሆን፣ ሃሌሉያ፣ ያኔ የክርስቶስ ሕይወት ይሞላናል። የእግዚአብሔር ሕያው ፍጥረታት እና፣ መንፈስ ቅዱስ የብርሃን በረከቱን የሚልክባቸው ማደርያዎች በመሆን፡ የክርስቶስ ቁመና ያላቸው እንሆናለን።

349 ኢየሱስ ሲናገር፦ “‘የእግዚአብሄር ልጅ ነኝ’ ስላልኳችሁ፡ ትሳደባላችሁን? በሕጋችሁ ውስጥ አለ። ስለ እናንተ፡ ‘አማልክት ናችሁ።’ የሚል ተጽፎ የለምን፡ ሕጋችሁስ እንዲህ አይልምን? ” እንደ ሙሴ፣ እንደ ኤልያስ፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ ራሱን እስኪያስተላልፍ ድረስ፡ ለእግዚአብሔር ቅርብ እንደነበሩት ነቢያት እናንተም ናችሁ። ስለ እግዚአብሔር እንጂ፡ ስለ ራሳቸው አልተናገሩም። “የሚናገረው፡ በእናንተ ውስጥ የሚኖረው አብ ነው እንጂ። የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና፡ ምን እንድትመልሱ አታስቡ።” እሱ ሞቷልና፡ ቃላቶቹ፡ የሱ አይደሉምና።

350 ስትሞቱ፡ ደሙ ሁሉ ከሰውየው ይወጣል፡ ትገነዙታላችሁ። ችግሩ፡ ብዙ ሰዎች አይገነዙም። ስለ ሞተ፡ ደሙን ሁሉ ታስወግዳላችሁ። ሌላ ህይወት ለመኖር ሞቷልና፡ ማድረግ የሚቻላችሁ ብቸኛው ነገር፡ ደሙን አስወግዳችሁ ሌላ ደም መተካት ነው።

351 እኛም አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም አስገብተናል፡ ይህም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እምነት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ በጎነት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ራስን መግዛት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ትዕግሥት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን መምሰል፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የወንድማማች መዋደድ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲኖረን አድርጓል። ራስ ነውና የሚገዛችሁ እሱ ነው። እግራችሁም መሠረት ነው፡ እምነት ነው። አሜን! ይሄውላችሁ... ? ... በራስ ለመመራት፡ የሚያስፈልጉን። አንድ ሰው እነዚህን ጸጋዎች ሁሉ ሲኖሩት፡ ፍጹም የእግዚአብሄር ሰው ይሆናል።

352 ከዛ፡ እግዚአብሄር፡ ቸርቹን፡ በሴት ይመስላታል፡ ሙሽራ ይላታል። እግዚአብሄር ቤተ ክርስትያንን በሙሽራ ይመስላታል። እያንዳንዱን ግለሰብ ሙሽራ ወደ መሆን፡ ወደ ልጅነት በሚያመጣበት መንገድ፡ ሙሽራይቱንም በእነዚህ ዘመናት ውስጥ አምጥቷታል፣ [ወንድም ብራንሃም በስሌዳው ላይ ሰባት ጊዜ መታ—አርታዒ።] ይህም ቤተ ክርስትያኒቱን **ወደዚህ** ወደ አንድ ሙላት እስኪያደርሳት ድረስ ነው።

353 እግሮቹ ይንቀሳቀሳሉ። ለምን? ጭንቅላት ስላዘዘው። አስተውሉ፡ እግር ስለሆነ፡ እንደ እጅ አይወዛወዝም። ሉተር እኛ ያደረግነውን ነገር ማድረግ አይችልም፡ ሜቶዲስቶችም አይችሉም፡ ምክንያቱ ሌላ ነበሩና። አያችሁ? ጭንቅላት ስላዘዘ እግሮች ይንቀሳቀሳሉ። ጭንቅላትም እግርን "እግር፡ አሁን፡ እጅ ሁን። ጆሮ፡ አይን ሁን፡" አይልም። ገብቷችኋል?

354 ነገር ግን፣ በእያንዳንዱ ዘመን፣ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አስቀምጧቸዋል፣ እና ለእያንዳንዱ ግለሰብ እነዚህን ጸጋዎች እንዳለው በማሳየት፡ በንድፍ አስቀምጦታል። እናም **ይህ** ቁመና ሲጠናቀቅ፡ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፡ ትነጠቃለች። እናም **ይህ** የእግዚአብሄር አገልጋይ፡ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ የተጠናቀቀ ቁመና ሲሆን፡ ይነጠቃል። ክብር! ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቷችኋል? አንተ ማለት ይሄው ነህ። ነገሩ ይሄው ነው።

355 ጳውሎስ የተባለውን ሰው **መጣ**፡ እርሱም፡ መሠረትን ጣለ። በላዩም ኢራንየስ **ይሄን** አፈሰሰ። የሚቀጥለው **ይሄኛውን** አፈሰሰ። ቀጣዩም **ይሄኛውን** አፈሰሰ። የሚቀጥለውም **ይሄን**፡ እና **ይሄን**፣ እና **ይሄን**፡ እንዲህ እያለ እስከዘመን ፍጻሜ ድረስ ይወጣል። ግን ምንድን ነው? ያው አንዱ መንፈስ ነው።

356 በእኔ እድሮ፡ እጅን፦ "እጅ፡ ሻንጣውን አቀብለኝ፡" የሚል ያው አንዱ መንፈስ። ያው መንፈስ እግሮችን፦ "እግር፡ አንድ እርምጃ ተራመድ፡" ይላል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቷችኋል?

357 ስለዚህ፡ አጠቃላይ ቁመናችሁ የሚመራው እና የሚቆጣጠረው በእነዚህ ነገሮች ነው፣ ነገር ግን እነዚህ ጸጋዎች በሙላት እስኪኖሯችሁ ድረስ በሙላት አይቆጣጠራችሁም።

358 ይህን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? አሁን ልንገራችሁ። በደንብ ያዙት... በሚያዳምጥ ጆሮአችሁ ጠብቁት። እሺ? የሰንሰለት ጥንካሬው ደካማ በሆነው ማስርያው ላይ ነው። ትክክል ነው። ከማስርያው የበለጠ ጠንካራ የለውም።

359 የተገነቡት **እነዚያ** ናቸው፡ **እነዚህ** የተገነቡ ነገሮች ምን ያህል ጠንካራ ቢሆኑ፡ ማስርያቸው ደካማ ከሆነ፡ ያኔ ትሰበራለች ከደካማዋ ማስርያ በላይ ጠንካራ አይኖርም። [ወንድም ብራንሃም በቾክ የስሌዳውን ሥዕል ጠቀሰ—አርታዒ።] አሁን፡ **ይሄን**፡ እና **ይሄን፡ ይሄኛውም** አለኝ ብለህ፡ **ይሄኛው** ከጎደለህ፡ ያኔ ትሰበራለች። **ይሄኛው** ኖሮህ፡ **ያኛው** ከሌለህ፡ ሩቅ ሳትሄድ ትሰበራለች። **ይሄኛው** አለህ፡ **ያኛው** ግን የለህም፡ ትሰበራለች። **ይሄን** ይዘህ፡ **ያኛው** ከሌለ፡ ትሰበራለች። **ይሄን** ይዘህ፡ **ያኛው** ከሌለ፡ ትሰበራለች። አየህ? ሌላ ደግሞ... **ይሄኛው** ሳይኖርህ **ይሄን** ሊኖርህ አይችልም።

360 ስለዚህ ፍጹም ቁመናህን በምታሰገዛበት ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ በእነዚያ ጸጋዎች፡ በውስጥህ ይመላለሳል፡ ያኔ ህያው ማደርያ ትሆናለህ። ያን ጊዜ ሰዎች አይተው፡ “ያ በጎነት እና እውቀት፡ የተሞላ ሰው (ቃሉን ይሚያምን)፡ ራስን መግዛትን፣ ትዕግሥትን፣ እግዚአብሔርን መምሰል፣ የወንድማማችነት መዋደድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር የሞላበት ሰው። ያውና፡ እዩት፡ እየሄደ ነው ይሉሃል።” ምን ማለት ነው? የማያምኑ ሰዎች ቁመናህን አይተው፡ “ክርስትያን ማለት እሱ ነው። የሚናገረውን የሚያውቅ ሰው፣ ወይም ሰው ናት። እንዲህ አይነት ደግ፣ መልካም፣ እና እግዚአብሄርን የሚፈራ ሰው አላየሁም ይላሉ።” ታትማችኋል። ማህተሙም በሁለቱ ፊት ይታያል። እየሄዳችሁም ቢሆን እየተመለሳችሁ፡ ማህተሙን እኩል ታዩታላችሁ። ይሄው ነው። አያችሁ? አንድ ሴት ወይም ወንድ እነዚህን ጸጋዎች ሲኖሩት፡ የመአዘን ድንጋዩ ይወርዳል በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ያትማቸዋል፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው።

361 ያን ጊዜ፡ **በዛ** የሚመጣ ቃል፡ በሰዎች ላይ በእያንዳንዳቸው ወርዶ እራሱን ይገልጣል፡ አያችሁ፡ ሰውየውን ፍጹም በማድረግ፡ ተንቀሳቃሽ፣ እና ህያው የክርስትያን ምሳሌ አድርጎት፡ የሕያው የእግዚአብሄር ማደርያ ያደርገዋል። ክርስቶስ የነበረውን ሁሉ፡ እነዚህ ደግሞ ይሆናሉ፡ ህይወቱ በውስጣቸው ነውና። በክርስቶስ ውስጥ ናቸው። ሕይወታቸውም በእግዚአብሄር፡ በክርስቶስ ውስጥ በሞት ተሰውራለች፡ በመንፈስ ቅዱስም የታተመች ናት። አንደኛ ቆሮንቶስ 12። ትክክል። አይደል? እራሳችሁን እንደ ሞተ ሰው ትቆጥራላችሁ፡ ከዚያም በእምነት ትወለዳላችሁ። ፍፁም እና ህያው የእግዚአብሔር መልክ እስክትሆኑ ድረስ፡ በጎነት እና እነዚህ ሌሎች ነገሮች ይጨመሩላችኋል። ድንቅ ነው አይደል?

362 ስለዚህ እግዚአብሄር፡ በዚህ ተመሳሳይ መልክ፡ ያመጣቸውን ሰባት እርከኖች ለማሳየት፡ ሰባቱ የቤተክርስትያን ዘመናት አመጣ፡ ይህም ግለሰቦችን ወደ ገዛ ምስሉ ለማሳደግ፡ እና በመልኩ ተሰርታ ያለቀላት ፍጹም ቤተክርስትያንን ለመገንባት ነው። በትንሳኤውም፡ ይህች አካል ሙሽራ ስለሆነች፡ ለዘላለም ከእርሱ ጋር ለመኖር ትነሳለች። አያችሁ? ስለዚህ በየዘመኑ፣ የሚመጣውን ዘመን ሁሉ ይቀርጻል።

363 ሌላው ደግሞ፡ ከዚህ ያለፈ ቅድመ ሁኔታ እናዳለው አስታውሱ። ጳውሎስ በዕብራውያን 11 ላይ የተናገረውን ታስታውሳላችሁ? እስቲ ከመዝጋታችን በፊት አንዴ ላንብብላችሁ። እናንተም… እኔ ሁልጊዜ፡ ይሄን ሳነብ፡ ይገርመኛል… ልዩ ስሜት እንዲሰማኝ ያደርገኛል። ዕብራውያን 11ን እከፍታለሁ፡ ከ 32ኛው ቁጥር እጀምራለሁ።

> እንግዲህ፡ **ምን እላለሁ**? **ስለ… ጌዴዎንና፡ ስለ ባርቅ፡ ስለ… ሶምሶንም፡ ስለ… ዮፍታሔም፡ ስለ**… **ዳዊትና፡ ስለ… ሳሙኤልም ስለ… ነቢያትም** እንዳልተርክ **ጊዜ ያጥርብኛልና፤**
>
> **እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፡ ጽድቅን አደረጉ፡ የተሰጠውን** የተሰፋ ቃል **አገኙ፡ የአንበሶችን** አፍ **ዘጉ፡**
>
> **የእሳትን ኃይል አጠፉ፡ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፡ ከድካማቸው በረቱ፡** በጦርነት **ኃይለኞች ሆኑ፡** የባዕድ **ጭፍሮችን**… **አባረሩ።**

**ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ፤** ... **ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ፡ የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ፡** እስከ ሞት ድረስ፡ ተደበደቡ፤

364 [ወንድም ብራንሃም በቾክ የስሌዳውን ሥዕል ጠቀስ—አርታዒ።] **እዚህ** ታች ጋር። እያችሁ? በጣም ጥሩ።

**ሌሎችም: መዘበቻ** በመሆንና... **በመገረፍ... ከዚህም በላይ... በእስራትና፡ በወኅኒ...** ተፈተኑ፤

**በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፡** ተፈተኑ፡ **በመጋዝ** ተሰነጠቁ፡ በሰይፍ **ተገድለው... ሞቱ፤ ሁሉን እያጡ፡** መከራን **እየተቀበሉ፡** እየተጨነቁ፡ **የበግና** የፍየል ሌጦ **ለብሰው ዞሩ፤**

**(ዓለም አልተገባቸውምና)**...

365 በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ፡ በቅንፍ ውስጥ አስተውላችሁ፡ ተመልከቱት።

**... በምድረ በዳና፡ በተራራ፡ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ።**

... እነዚህም ሁሉ፡ **በእምነታቸው ተመሰክሮላቸው ሳሉ፡...**

366 **እዚህ ጋር**! [ወንድም ብራንሃም በቾክ የስሌዳውን ሥዕል ጠቀስ—አርታዒ።]

**... በእምነታቸው ተመሰክሮላቸው ሳሉ፡ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም፤** (እያችሁ? )

**ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ፡ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና።**

367 ገብቷችኋል? እዚህ ጋር፡ አስቀድመው የሞቱ ሰዎች፡ በእኛ ላይ ተመርኩዘው፡ እየጠበቁ ይገኛሉ ማለት ነው። በዚህም ምክንያት፡ ትንሳኤውን ለማቀላጠፍ፡ **ይህች** ቤተክርስትያን ወደ ፍጽምና መድረስ አለባት። እነርሱ አሁን፡ ኢየሱስ ሲመጣ፡ ወደ ፍጽምና የምትደርሰውን ቤተ ክርሰትያን እየጠበቁ፡ ከመሰውያው በታች ይገኛሉ።

368 ይቺ አሁን የምታዩአት፡ ቤተክርሰትያን፡ ከጥቂቱ መንጋዋ ጋር፡ እጅግ እየጠበበች ትወጣለች። [ወንድም ብራንሃም በቾክ ስሌዳውን ሥዕል ጠቀሰ—አርታዒ።] ከዚህም እጅግ ይጠባል፡ መስቀለኛ ጽፈው እንደሚያልፉ መሰመሮች፡ እዩአቸው። የመርፌ ጫፍ እስኪሆኑ ድረስ ይጠባል። ይህም፡ ቤተ ክርሰትያን፡ ከታናሹ መንጋ ጋር፡ ወደ ቦታዋ እስክትደርስ ድረስ **ይሄኛው** የተተወው የአገልግሎት አይነት እስኪሆን ድረስ፣ ምክንያቱ፡ የመደምደሚው ድንጋይ ተመልሶ ሲመጣ...

369 በተለመደው ፒራሚድ ላይ፡ መጥቶ የሚያርፍበት፡ እንደዚህ አይነት ኪስ-መሳይ ነገር **እዚህ** ጋር አለው። መጥቶ እንደ ኮፍያ በላዩ ቁጭ የሚል ብቻ አይደለም። ዝናቡን የሚያንሸራትት ሰለሆነ፡ መጥቶ የሚቀመጥ፡ ክንፍ መሳይ ነው።

እሱ ሲመጣ፡ ቤተ ክርሰትያን የተወለወለች ትሆናለች።

370 ሌሎቹ፡ በፒራሚዱ የሚገኙ ድንጋዮች ሁሉ፡ ብዙ ቶን የሚመዝኑ፡ ተደራርበው የተቀመጡ፡ በመካከላቸው ምላጭን ማሳለፍ እስከማይቻል ድረስ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ተደራርበው ይገኛሉ። እንዴት እንደገነቧቸው፡ አይታወቅም። ይሁን እንጂ የተገነቡ ናቸው።

371 **እዚህ** ጋር ደግሞ፡ የፒራሚዱ ራስ ሲመጣ፡ ፒራሚዱ፡ ማለት የክርስቶስ አካል የተወለወለች ትሆናለች። አንዳንድ አዋልድ ወይም አስተምህሮዎች፡ ወይም ይዘን የመጣነው ብቻ አይደለም። እሱ ሲመጣ፡ እሱ እና ያ አገልግሎት፡ ፍጹም በሆነ አንድነት፡ አንድ እስኪሆኑ ድረስ እንደ ክርስቶስ መሆን አለባቸው። አያችሁ? ያኔ ወደ ቤት መሄድ፡ ወይም መነጠቅ ይሆናል።

372 አሁን የምንኖርበት፡ የሎዶቅያ ዘመን፡ እስከ ዛሬ ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እጅግ የከፋ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እግዚአብሔር ወደ ገዛ ማደርያው ለመግባት ፈልጎ፡ ከቤተክርስቲያን ውጭ ሆኖ የሚያንኳኳባት፡ ብቸኛ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ እንደሆነች እናያለን። አዋልዶች እና የሐይማኖት ተቋማት ከቤተ ክርስትያኑ አስወጥተውታል። "እነሆ፡ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ። ማንም ቢጠማና በሩን ቢከፍትልኝ፡ እኔ እገባለሁ፡ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ።" አያችሁ? ይሄውላችሁ፡ **በዚህ** ቤተ ክርስትያን ዘመን። **እዚህ** በሙላት እስኪያሰወግዱት ድረስ፡ ቀስ በቀስ ወደ ውጭ እያሰወጡት ነበር። ከእሱ ጋር ምንም መተባበር አይፈልጉም።

373 አሁን ወዴት እየሄድን እንዳለን አይታችኋል። የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ዘመን ማብቂያው በጣም ተራ በሆነበት ጊዜ፣ እሷ እና እንድትፈርስ ያደረገቻት፡ ማለትም ካቶሊካዊነት፡ **ሁለቱም** ከአብያተ ክርስትያናት ፌደሬሽን ጋር አንድ ሆነዋል። አንድ ታላቅ ቤተ ክርስትያን ለመሆን ነው፡ ይህም ያው ካቶሊካዊነት ነው።

374 ልዩነታቸውን ለማየት ቢፈልጉ፡ ልዩነታቸው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ እሱም ቁርባን ላይ ነው። በሀገረ ሰብከታቸው መካከል ያለው—ብቸኛው ልዩነት—ካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት እምነትን፡ አንድነት አንድ ከመሆን፡ የሚከለክላቸው ቁርባን ብቻ ነው። የካቶሊክ ቤተክርስትያን "ስጋው ነው፡" ትለዋለች። የፕሮቴስታንት ቸርችም "የስጋው ምሳሌ ነው፡" ትለዋለች። የካቶሊክ ቸርች ቅዳሴ ታደርግበታለች። ቅዳሴውም፡ ቁርባን፡ በወሰዱ ጊዜ፡ ይቅርታን ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ነው። ፕሮቴስታንቶች ግን በእምነት፡ ከእግዚአብሄር ዘንድ፡ ይቅርታን በማግኘታቸው፡ በቁርባን ያመሰግኑታል። ፕሮቴስታንቶች "ይቅርታ አግኝተናል፡" ይላሉ። ካቶሊክ "ይቅርታ እንደምናገኝ ተስፋ እናደርጋለን፡" ይላሉ። ቅዳሴ እና ቁርባን። እነርሱ ቅዳሴ ብለው ይጠሩታል፡ እኛ ግን ቁርባን እንለዋለን። ቅዳሴ ተስፋን ማድረግ ነው። ቁርባን ግን ማወቅ ነው፡ ለዚህም እናመሰግነዋለን። አያችሁ? አንድ ሊያደርጋቸው የማይችል ብቸኛው ነገር ይህ ነው። መሆናቸው ግን አይቀርም።

375 ኦህ፡ እጅግ ውብ መሳይ ነው። ገዢ ለመሆን... አንድ ይሆናሉ፡ ሌላው—ሌላውን ሁሉ ይገዛሉ... እንግዲህ፡ መጽሐፍ ቅዱስም "አራዊቶቹም ሥልጣናቸውን ለጋለሞታዋ ሰጡ፡" ይላል፡ ይህም፡ አንድ ሆኑ ማለት ነው። አያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ ያደርጋሉ ያለውን፡ አሁን እያደረጉት ነው። በዚሁ

ሳምንት ውስጥ፡ ሂደት ላይ ነው። ከፕሮቴስታንት ሰዎች በተለየ፡ ከካቶሊክ ህዝብ ጋር የተለየ ቅራኔ ኖሮኝ አይደለም።

376 እናንተ ሜቶዲስቶችና ባፕቲስቶች፣ እና ብዙዎቻችሁ ጴንጤቆስጤዎች፣ ቤተክርስቲያኖቻችሁ ወደዚህ የአብያተ ክርስቲያናት ፌዴሬሽን ሲጣመሩ፣ በኒውዮርክ ከተማ የአብያተ ክርስቲያናት ፌዴሬሽን ትልቅ መቃብር ሲገነቡ፣ እንደ ተባበሩት መንግስታት እና እንደ ሌላው ተረታ ተረት ተመሳሳይ ነገር ነው። ፕሮቴስታንታዊነትን በሙሉ አንድ ላይ ለማድረግ እየሞከሩ ነው።

377 በዚህ ነገር ላይ፡ ካቶሊኮች ጥበበኞች ናቸው፡ ሃያ-ሦስተኛው ይሁን ሃያ-ሁለተኛው፡ ፖፕ ጆንን፡ ብቻ ምንም ይሁን፡ ልከውላቸዋል። እርሱም፡ እጅግ ትህትና እና እርጋታ በተሞላ መንገድ፡ መጽሀፍ ቅዱስ ይሆናል ያለውን፡ የፕሮቴስታንት እምነቶች እና የካቶሊክ እምነት፡ ወደ አንድ ለማምጣት ላይ ታች እያለ ነው። ይሄው። ፕሮቴስታንቶቹም፡ መንጠቆው ውስጥ፡ ተጠምደው፡ ሰምጠው ሰግደውለታል።

378 ለምን? ለምን? **እውቀት** የላቸውም፡ እነዚህ **ነገሮች** ስለሌሏቸው ነው። "ቃሉ እውነት ነው።" **ትዕግስት**፡ "እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ።" ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ?

379 ያንን ካለፉት በኋላ፡ በቀደም አንድ የሜቶዲስት ቢሾፕ ሲናገር ነበር። በቤተ ክርስቲያን፡ ወይም በትምህርት ቤት፡ የታወቀች ጸሎት ለማሰድረግ፡ ምን አይነት ተነሳሽነት እንደነበረ፡ ሰው ሁሉ ያውቀዋል። የፕሬስባይቴሪያን የጸሎት መጽሐፍ ነገር ይመስለኛል፡ እና ፈልገዋት ነበር... ወላጆች ግን ይህንን ጸሎት በትምህርት ቤት ውስጥ ስላልተቀበሉት—ትምህርት—ቤቱን ከሰሱ። እና እኚህ የሜቶዲስት ቢሾፕ ጥበበኛ አዛውንት ነበሩና፣ ተነሥቶ፦ "ስህተት ነው" አለ። "ህገ መንግስታዊ አይደለም፡" አለ። ትንፋሹን ሰብስብ አረገና። "ለምሳሌ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ፣" አለ፤ እንዲህ አለ፦ "በሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያናችን" አለ፤ "ብዙ ሰዎች ስለ ሆሊውድ ቅሌት ሁልጊዜ ይናገራሉ። ዘጠና-አምስት በመቶ የሚሆኑት ግን እንዲሁ ለማየት ይሄዳሉ" አለ።

380 ችግሩ ምንድነው? **ይህን** ትተውታል። ትክክል ነው። ያንን ትተውታል።

381 ባለፈው እዚህ ክፍል ውስጥ፡ በፎልስ ሲቲ ከሚገኙ፡ የሜቶዲስት አብያተ ክርስትያናት መካከል የአንዲቱ መ—መ—መሪ ከሆነው ሰው ጋር፡ በፎልስ ሲቲ ከሚገኙ መንፈሳዊ የሜቶዲስት አብያተ ክርስትያናት መካከል ከሆነ ሰው ጋር እየተናገርኩት ነበር፡ ከዘመናችን፡ ከጴንጤቆስጤ ዘመን በፊት የመጣ የሜቶዲስት ዘመን እንደሚባል፡ አሳየሁት። እርሱም፦ "በሴንት ሉዊስ፡ ሚዙሪ፡ ከሦስት ወይም ከአራት ወራት በፊት፡ አንድ የጥናት ትንታኔ፡ ተደርጓል።" ሰውዬው ዛሬ ጠዋት እዚህ ተቀምጦ ሊሆን ይችላል። ይህን የሚገነባው፡ ኮንትራክተር ነው፡ ሕንፃውን የሚያስተካክልልን ሰው እሱ ነው። እነ ወንድም ሎም እና ሌሎች፡ በፓስተርነት ሲያገለግሉበት ከነበረው፡ ከሜን ስትሪት ሜተዲስት ነው። ስለዚህ በዛ ውስጥ፡ ማለት በትንተናው ውስጥ፡ ሰባ-አንድ በመቶው የሜቶዲስት ሰዎች፡ በሴንት/ ሉዊስ፡ በተደረገ ጥናት፡ በኢ-ተጋማሽ ቁጥር ሰባ እና ከዚያ በላይ መቶኛ ሜተዲስቶች ያጨሳሉ ተብሏል፡ ስልሳ-ስምንት በመቶ የሚሆኑትም የአልኮል መጠጦች ተጠቃሚ ናቸው። ሜቶዲስት ሆነው! እና የሚገርመው ነገር፡ በወንዶችና በሴቶች መካከል፡ የተደረገ ትንተና

ወይም ግምት ሲሆን፤ ከሴቶች፡ ሰባ፡ ሰባ-ከዚያ በላይ በመቶ ሲሆኑ፡ ሃምሳ በመቶው ወንዶች ናቸው። ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በብዛት ያጨሳሉ። ከወንዶች በበለጠ ሰባ በመቶ፡ ሰባና-ከዚያ በላይ በመቶ፡ ሴቶች ናቸው።

382 አሁን እያችሁ፡ እግዚአብሄርን መምሰል፡ እግዚአብሄርን እንመስላለን ቅድስናም አለን ለሚሉ ሴቶች፡ አጭር ቀሚሰ መልበስ ፀጉር መቆራረጥ፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች፡ ወደሚሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮት ብንወርድስ? በየመዝናኛው የካርታ ጨዋታዎች እና ሌላ ነገሮች የሚያደርጉ፡ እንደበታቸውን መግታት የማይችሉ፡ ሐሜተኞች፡ ወሬኞች። ዟሪዎች፡ የገዛ እንደበታቸው የማይገዙ ሐሜተኞች። ወንዶችስ? በየመዝናኛው የካርታ ጨዋታዎች፡ ጎልፍ ጨዋታ ላይ፡ ግማሽ-እርቃን፡ አስጸያፊ ልብስ ለብሰው፡ ከሴቶች ጋር የሚያሽካኩ ናቸው። ምንም አይገርምም!

383 ዛሬ ጠዋት ያሰባኪ፡ የእሰር ቤት ሰባኪው ላይ፡ የተሰራው ሴራ አይታችኋል? አዎን፡ ሴራ። ሰውዬው ጥፋተኛ ነው ብዬ አላምንም። ምን ሰላደረገ? ወንድም ማን... ሰሙ ትዝ አይለኝም... [ሌላ ሰው፡ “ዳን ጊልበርት” አለ።—እርታዒ] አዎን፡ የእሰር ቤት ሰባኪው፡ ዳን ጊልበርት። ከጥቂት ወራት በፊት፣ ያ ሰው ሮጦ ዳንኤልን የገደለ ሰው፣ ሚስቱ አሁን ልጅ ልትወልድ ነው። እርግጥ ነው፡ ዳን ሞቷል፡ አሁን ለህፃኑ ደም የሚሆን ደም ማሰተላለፍ አይችሉም። እሷ ግን ዳን አሰፈራርቶኛ ነው፡ ልጇም... “የዳን ልጅ ነው፡” ብላዋለች። ተራ ውሸት... ቁራ—የእርግብ ላባ—አበቀለ ቢሉኝ እንደማላምን ሁሉ ይሄኛውም ከዛ ለይቼ አላየውም። ፍጹም፡ ውሸት። ውሸት እንደሆነ አምናለሁ። ዳን ጊልበርት የእግዚአብሄር ሰው እንደነበረ አምናለሁ። የዲያብሎስ ሴራ ነው።

384 ልክ እንደዚያ ጸሎት የሆነ ነገር ለማድረግ በመፈለግ ነው። ሽማግሌው የሜቶዲሰት—የሜቶዲሰቱ ቢሾፕ ያንን ማለቱ እጅግ ቆቅ ነው። እንዲህ ከሆነ፡ ነገሩ ይሁንታ ቢያገኝ ኖሮ፡ በተሳሳተ መነቃቃት የመጣ ይመሰል ነበር። በትክክል።

385 በደቡብ በኩል እንደነበረው መገለል ይሆን ነበር፡ ተመሳሳይ ነገር ነው። ሰዎች ነጻ መሆን አለባቸው ብዬ አምናለሁና። ይህች አገር ሰለ ነጻነት የቆመች አገር እንደሆነች አምናለሁ። አቶ/ ኬኔዲ እነዚያን ወታደሮች መላካቸው እኔ አልወቅሳቸውም። በርግጥ፡ እኔ—“አዲሰ ደላላ” ለመሆን አይደለም፡ ክርሰትያን ነኝ። ዲሞክራት አይደለሁም። ሪፓብሊካንም አይደለሁም። ቢሆንም... በዚህ ነገር አላምንም። ጥቁሮች ወገኖቻችን፡ ብኩርናቸውን፡ ለእንደዚህ አይነት ነገሮች መሸጥ አለባቸው ብዬ አላምንም። እነሱ ነጻ የወጡት በእግዚአብሄር ሰው በአብርሃም ሊንከን ደም ነው። የሪፐብሊካን—ፓርቲ ነበር። ድምጽ ከሰጡ አይቀር ግን ቢያንሰ ከፓርቲያቸው ጋር መወገን ያለባቸው ይመሰለኛል።

386 አንድ ነገር ግን ልንገራችሁ፡ ያ ልጅ በነዚያ ትምህርት ቤቶች ምክንያት፡ አይደለም የሄደው። ልጁ ዜጋ ነው። አሜሪካዊ ነው። የሰው ቀለም ልዩነት መፍጠር የለበትም። ነጻነት ለሁሉ ነው። ሁላችንም... “ሰው ሁሉ፡ ከአንድ ሰው ደም፡ ተፈጥሯል፡” ብሏል፡ “እግዚአብሄር።” ሁላችንም አንድ ነን። ያ ልጅ ግን ወታደር ነበር። እርበኛ ነው። ሰለ እውነት ታግሏል። ትምህርት ቤት የመማር

መብት ነበረው። ትክክል ነው። ሄዶ ሊማርባቸው የሚችላቸው ብዙ ትምህርት ቤቶች ግን ነበሩት።

387 ነገሩ ይህ ነው። የነገሩን ችግር ብትመረምሩ፡ የተሳሳተው መነቃቃቱ፡ ከዚህ-ዘመን የሐይማኖት ስርዓት ሆኖ ታገኙታላችሁ። ለምን? የጥቁሮች ድምጽ ከሪፐብሊካን ወደ ዲሞክራት እንዲፈልሱ በማስደረግ፣ ብኩርናቸውን ያሸጧቸዋልና። በትክክል እውነት ነው። መንፈስ ቅዱስ የለበትም…

388 "ጥበብ ያለው።" "እውቀት ያለው።" በትክክል። ልክ እንደ አሁኗ ዘመን፡ እራሷን እንደምትሸጠው፡ ቤተክርስትያን። ምን ሊሆን እንደተዘጋጀ አይታያችሁም?

389 ይህ እየተቀዳ ከሆነም ግድ የለኝም። ነገሩ እንዲህ ነው። ኧሀ-ሀህ። አዎን። ችግሩ ምንድነው? ምንድነው ችግሩ? አሮጌትዋ እናቴ "ለዲያብሎስ ዋጋውን ሰጠው፡" ትለን ነበር።

390 የሆነውን ነገር በማስተዋል ያደረገ አንድ ሰው ብቻ ነው እሱም ታች ያለው ካስትሮ ነው። አዎን፡ ጌታዬ። ወደዚያ ወረደ። ካፒታሊስቶቹ አገዳውን እና ሁሉም ነገር ተቆጣጥረውታል… ልክ እንደ አሜሪካ፡ በወርቅ ደረጃ ላይ ነው። ምን አደረገ? ያን ሁሉ ቦንድ ገዛው። ገንዘቡን በሚችለው መንገድ ገንዘቡን አስመለሰ። ከዚያስ ምን አደረገ? ምንዛሬውን በማስመሰል፡ ለወጠው። ወደ ነበረበት መለሰው። ይህ አገር ማድረግ የሚችለው ይህ ብቻ ነው።

391 በቀደም ጧት **ላይፍ ላይንን** ሰምታቿል? ያ ማለት፡ ታውቃላችሁ፡ ቦንዶችን በወርቁ ላይ እንደመሸጥ ነው። ቦንዲ'ኮ ቀድሞውኑም ተወስዷል። ታድያ አሁን ያለው መንግስት ገንዘቡን የሚያወጣው ለምንድነው? ከአርባ ዓመታት በኋላ ለሚሰበስቡት የግብር ገንዘብ። አብቅቶላታል። ከዋሺንግተን፡ ዲሲ፡ ወደ መላው አገሪቱ የሚሰራጨው **ላይፍ ላይን** ነው። ግብሮቹን፡ እያወጡት ነው፡ ከውጭ አገርም ለመግዛት እየሞከሩ ይገኛሉ… በቃ፡ እንዲሁ እየሰጡት ነው። አይታያችሁም ወይ? ሊያደርጉት ያለው ነገር—በትክክል ይሄው ነው። አያችሁ? ምንድነው? አሁን፡ አገሪቱ ከከሰረች፡ በቃ ማድረግ የሚቻለው መክሰር ነው። የሚቻለው ሄዶ መክሰር ብቻ ነው።

392 ብቸኛው ምክንያታዊ አማራጭ፡ ምንዛሬውን መቀየር ነው። በአሁኑ አስተዳደር ግን፡ ይሄን አያደርጉም። የዓለም ወርቅ ባለቤት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነች። እና መጽሀፍ ቅዱስ እንደሚለው፡ "የምድር፡" "ባለጸጎች፡" የሚያደርጉት፡ መሸጥ ብቻ ነው። እነ ብራውን እና ዊልያምሰን ትምባሆ ኩባንያ፡ እና ሌሎች ሁሉ፡ በርግጥ፡ አብዛኞቹ፡ ካቶሊኮች ናቸው፡ ነገር ግን ከመክሰራቸው በፊት፡ ምን ያደርጋሉ? ይቀበሉታል፡ ገንዘቡም ከሮም ይቀበላሉ፡ በዚህም መንገድ ብኩርናዋን ሸጣለች። ሮም ትደግፋታለች። አዎን፡ ወዳጄ። ትደግፋታለች። አሁን ወደ ካቢኔው ለማቅረብ፡ እና ዙርያቸውን ለማጠናከር፡ በቂ ፖሊሲ እያረቀቁ ይገኛሉ። አቶ/ ኬኔዲ የሚጠይቁትን ተመልከቱ።

393 እንደ ባለፈው ቀን፡ እንዲህ ከሆነ፡ ከአሁን በኋላ ምርጫ ድምጽ መስጠት ምን አስፈለገ። የምርጫው ጥቅሙስ ምንድነው? በሕዝብ ፊት ማረጋገጣቸውን ለማሳየት፡ በጋዜጣ ካወጡት በኋላ፡ ምንም ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆኑም። በመላ አገሪቱ ያሉት ማሽኖች እንደተዘጋጁ፡ አቶ/ ኬኔዲ

በውሸት ድምፅ እንደተመረጡ አረጋግጠዋል። መጽሀፍ ቅዱስ በማታለል ይመጣል አላለምን? አዎን፡ በሐሰተኛ ምርጫ። እኔ አሁን፡ ዴሞክራቶችን ከሪፐብሊካን ፓርቲ በበለጠ እየተቃወምኩ አይደለሁም፣ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎችን እናገራለሁ። ማን እንደሚቀመጥ አስቀድመው ያውቁታል። ታድያ ድምጽ መስጠት ጥቅሙ ምንድነው?

394 ሁለት ሴቶች የተሳተፋበት የቴሌክስ ስርጭት ስንቶቻችሁ ታስታውሳላችሁ? አንደኛዋ ሴት፡ "የኔ ምርጫ አቶ.... " ፕሮቴስታንት ናት እና፡ "አቶ/ ኬኔዲን እምረጣለሁ፡" አለች።

"ለምን? " ሲሏት፤

395 "ምክንያቱም ከአቶ/ ኒክሰን በበለጠ ብልህ ሰው ነው፡ የተሻለ ፕሬዝዳንት ይሆናል ብዬ አስባለሁ።" አለች።

396 ሌላኛዋንም "ካቶሊክ ሴት ናት። 'ማንን ትመርጫለሽ? ' ብሎ ጠየቃት፤"

397 "ካቶሊክ ነኝ፡ የሮማ ካቶሊክ፡ ታማኝ ካቶሊክ ነኝ፡" አለች። ስለዚህ "የምመርጠው አቶ/ ኒክሰንን ነው፡" አለች።

"ለምን? "

398 እንዲህ አለች፡ "አቶ/ ኒክሰን በነገሮች የበለጠ ልምድ ስላለው፡ የተሻለ ፕሬዝደንት ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ስለ ኮሚኒዝም ጠንቅቆ ያውቃል።" በማለት ውሸት ተናገረች።

399 **የእምነታችን እውነታዎች፡** በሚል **ርዕስ**፡ ገበያ ላይ ያለው ትልቁ የካቶሊክ መጽሐፍ... እኔ አለኝ። በዚያ ውስጥ የሚናገሩት፡ "ምርጫ ካርድ የያዘ ካቶሊክ የሆነ ሰው፡ ፕሮቴስታንትን ከመረጠ፡ ካቶሊክ ሆኖ ፕሮቴስታንትን ከመረጠ፡ ከካቶሊክ ቤተክርስትያን ህብረት ይወገዛል ይላል።" በትክክል። "ተወዳዳሪዎቹ ሁለቱም ሰዎች ካቶሊኮች ሆነው ለአንድ ድምጽ ከተወዳደሩ ግን፡ 'ለእናት ቤተ ክርስትያን' በበለጠ ታማኝ የሆነውን በመሰየም እርሱን ምረጡ ይባላል።"

400 ምን ለማድረግ እንደሚፈልጉ ተንኰላቸውን፡ አያችሁ? ይሄን ለመግዛት፡ ገንዘባቸውን ይጥላሉ። ለምን? ሊሰብሯት ስለሚፈልጉ። ደግሞም ተሰብራለች፡ ተሳክቶላቸዋል። ይህስ ምንድነው? ከጎልዱ ስታንዳርድ ነው። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣ የሥልጣን ተዋረድም፣ የአለም ወርቅ ባለቤት ናቸው። [አንድ ሰው "መቶ ስልሳ-ሰምንት ቢሊዮን ዶላር፡" አለ።—አርታዒ።] ይሄውላችሁ። መቶ ስልሳ-ሰምንት ቢሊዮን። በጎልድ ስታንዳርድ ላይ ጥለዋታል፡ እናንተ ሰዎችም ሁላችሁ ከቤቶቻችሁ እና ከንብረታችሁ ጋር ቀርታችኋል፡ ይሁን እንጂ የካቶሊክ ቤተክርስትያን ንብረት ናችሁ። አገሪቱ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ንብረት ሆናለች። በምንዛሬአቸው በኩል፡ አጠቃላይ ይዞታ ሁሉ ተወርሷል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ነገር አይናገርምን? መጽሐፍ ቅዱስ የሚስልልን ሥዕል ይህ ነው።

401 ወንድሜ ሆይ፡ ዛሬ፡ ልነግርህ የፈለግኩት ነገር። "ይህ ፕሮቴስታንቲዝም አንድ ያደርጋል፡ እኗንም ድንቅ ቤተክርስትያን ያደርጋታል።" ይላሉ። ለሥጋዊ ዓይን መልካም ይመስላል፡ የዚህ ዓለም እውቀት ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነው።

402 “እግዚአብሄር የሚደስተው፡ የጠፉትን በሚያድን፡ በሰብከት—ሞኝነት ነው፡” ቤተክርስቲያንን፡ በመንፈሳዊ ጸጋዎች ለመገንባት፡ በገዛ ቤተክርስትያኑ ላይ በሚልካቸው መለኮታዊ አገልግሎቶች እንጂ በምድራዊ ነገሮች አይደለም።

403 ጴጥሮስ እንዲህ አለ፦ “በገንዘብ ምኞት ከዓለም መበሰበስ ሰላመለጣችሁ፡ ከጊዜአዊ ምኞት፣ ከደስታ፣ ከመብላት፣ ከመጠጣት፣ በውስጣችን ካለው መመኘት። አምልጣችኋል። አሁን በክብርና በጎነት እየተገነባችሁ ነው። ይህ ግን ለቤተክርስትያን እላለሁ፡” ብሏል። ይሄውላችሁ። አነባብችሁት? ተረድታችሁታል? ሁለተኛው ጴጥሮስ ስናነብ ሰምታችኋል ከኋላ? እንዴት ያለ ድንቅ ጽሁፍ፡ እራሱ ሲናገር—ምን ብሎ እንደተናገረ፡ ተከታተሉኝ። በጣም ጥሩ። አሁን እሱ ሲናገር ሰሙት። በጣም ጥሩ።

> **የኢየሱስ ክርሰቶሰ ባሪያና፡ ሐዋርያ፡ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፡ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርሰቶሰ ጽድቅ ካገኘነው ጋር... የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ፤**
>
> **... የመለኮቱ ኃይል በገዛ—ክብሩና** በበጎነቱ **የጠራንን በማወቅ፡ ለሕይወትና** እግዚአብሔርን **ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ሰለ ሰጠን፡**
>
> **በእግዚአብሔርና—በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ...**

404 ምድርንና ሞላዋን የሚወርሰው ማን ነው? [አንድ ሰው “ቅዱሳን፡” ብሎ ተናገረ—እርታዒ።] በትክክል። “ለምን የሚሆነውን... ” እሺ። በጣም ጥሩ።

> ... **የመለኮቱ ኃይል** በገዛ **ክብሩና በበጎነቱ** የጠራንን **በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል** የሚሆነውን፤
>
> **በክብርና በበጎነት የተከበረና** እጅግ **ታላቅ... የሆነ** ተሰፋን **ሰጠን፡** ይህም **ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድትሆኑ፡ ሰለ ክፉ ምኞት** (ይሄን ሰሙት።) **በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችኋል።**

405 ከገንዘብ ምኞት፣ ታላላቅ ነገሮችን ከመመኘት፣ ተወዳጅነትን መሻት፣ እነዚህ ነገሮች ለአማኙ የሞቱ ናቸው። ግድ የለንም። ድንኳን ይሁን ጎጆ፡ ለምን እጨነቃለሁ፤ መኖር ወይሰ መሞት፡ መሰጠም ወይም መጥለቅ? እኔ የምፈልገው፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ነው። ቤትን ብሰራ፣ የራሴ ቤተሰብ ብመሰርት፣ ወይም ምንም ነገር ባደርግ፣ የክብር ተሰፋችን የሆነውን፡ ክርሰቶሰን ልጠብቅ።

406 ጌታ ሆይ፡ በእኔ የሚሠራ ክርሰቶሰ፡ ራሰ ይሁነኝ። **በዚህ** ውስጥ፡ ሰራኝ። በመሠረቴ ላይ፣ በርሱ ዘንድ ባለኝ እምነት፣ ጌታ ሆይ፡ ጸሎቴ፡ በጎነት፣ እውቀት፣ ራስን መግዛት፣ ትዕግሥት፣ እግዚአብሔርን መምሰል፣ የወንድማማች መዋደ፣ በእኔ ይሥራ ነው። ልሙት ወይም ልኑር፣ ልጥለቅ ወይሰ ልሰጠም፤ የሐይማኖት ተቋም ይኑር፡ የሐይማኖት ተቋም አይኑር፤ ወዳጅ ይኑር አይኑር። ያ በእኔ ውስጥ ይሰራ፣ እነዚያን ለማስተማር እንድችል የክርሰቶሰ በጎነት፣ እውቀቱ፣ ይፍሰሰብኝ።

407 “የእግዚአብሔር ልጅ፣ የመምጣት ፍጻሜ፣ እና ፀጋዎች ሁሉ፣ ለመፈጸም፣ ወደ ራሱም ለመሳብ፣ እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ሐዋርያትን ነቢያትን አስተማሪዎችን እረኞችን እና ወንጌላውያንን ሰጠ።” እያንዳንዳቸው **እነዚህ** ድንጋዮች የአንዱ ግብአቶች ናቸው። **ይህም** የዚህ ግብአት ነው። እያንዳንዳቸው እነዚህ ጸጋዎች ለእርሱ የተገቡ ናቸው፡ በእነሱም ሁሉ፡ ከርሱ ዘንድ ይፈሰሳሉ። አሜን።

408 አሥራ ሁለት ሰዓት ሆኗል። ይህ ሁሉ በምን ይጠቃለላል? በአሜን። ትወዱታላችሁ ወይ? [ጉባኤው ሁሉ “ኣሜን፡” አለ።—እርታዒ።] ይሄን ታምናላችሁ? [“አሜን።”] ልጆቼ፡ ሰሙኣ።

409 ዛሬ ጠዋት፡ “ወንድም ቢል፣ እንደገና የማይህ አልመሰል አለኝ፡” አለች እህት ኪድ። አያችሁ? እርጅቻለሁ ብላ እሰባ ’ኮነው፡ ደግሞም አርጅታለች። እኔ ይሄ ነገር በጣም ይከብደኛል። እግዚአብሔር፡ ለእሷ እና ለወንድም ኪድ ረጅም ዕድሜ እንዲሰጣቸው እለምናለሁ።

410 ልንገራችሁ፡ ለምን ያህል ጊዜ እንደምንኖር አናውቅም። ከእናንተ ጋር ለምን ያህል ጊዜ እንደምቆይ አላውቅም። እግዚአብሔር ከዓለም እርቆ ሊጠራኝ ይችላል። ወደ ሌላ የአገልግሎት መስክ ሊጠራኝ ይችላል። የሆነ ቦታ ሊጠራችሁ ይችላል። አናውቅም። ግን፡ አንድ ነገር—እናድርግበት። ይሄ ነገር አይለፈን። እንጠቀምበት።

411 ንድፍ እና አሰራሩ ሁሉ፡ ተቀምጦላችኋል። መጽሐፍ ቅዱስ፡ ውስጥ ነው። ብቻ እኔም ጊዜ ባገኘሁ! ታውቁታላችሁ። በአንድ ቀን ሰርታችሁ መጨረስ አትችሉም። ይሁን እንጂ፡ ሁሉንም አንድላይ ማሰር ግን ትችላላችሁ!

412 ያኔ፡ ያንን መልእክት ሰንማር፡ መንፈስ ቅዱስ ግድግዳው ላይ ያደረገው ነገር ታስታውሳላችሁ፡ አይደል? ያኔ የነበራችሁ ሰዎች ካላችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—እርታዒ።] አያችሁ? በትክክል። ጌታ መልአክ ወርዶ፡ ያንኑ፡ ተመሳሳይ ሰዕል ሳለ።

413 አስተውሉ፡ እውነት ነው። አያምልጣችሁ። ልጆች ሆይ፡ የሙጥኝ በሉ። የሙጥኝ በሉበት። በእምነታችሁ ላይ፡ በጎነት፡ እውቀት፡ ትዕግስት፡ መገንባት አትርሱ!

414 እዚህ ወረቀት ይዤ ነበር። ስሰብክ ካልጣልኩት በቀር፡ አሁን፡ ወረቀት ይዤ ነበር። ይሄው ተገኘ። አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ። በጣም፡ አመሰግናለሁ። ማየት—ከፈለጋችሁ፡ አይታችሁ ቁምነገር ካገኛችሁበትና ምናልባት መገልበጥ ከፈለጋችሁ… በንድፉ እዚህ ከምታዩት ይልቅ ሳይሻል አይቀርም፡ ምናልባት ኮፒ ማድረግ ከፈለጋችሁ። እዚህ ጋር እሰቅለዋለሁ፡ እናንተም በርግጥ ይታያችኋል እና—ኮፒ አድርጉት።

415 እና ወሰዳችሁ እንድታስተያዩት፡ እና እንድታጠኑት፡ እንድትኖሩትም እመክራችኋለሁ። ማጥናት ብቻ አይደለም፡ አስተያይታችሁ መዝኑት፡ መዝናችሁም ኑሩበት። በትሕትና ተቀበሉት። “ሰምቼ፡ ተባርኬበታለሁ፡” ብቻ አትበሉ። እኔም ሰምቼዋለሁና። መሰማት፡ እና መቀበል ግን፡ ሁለቱ ይለያያሉ። አያችሁ? አያችሁ? ይለያያሉ። ገብቷችኋል?

416 የእግዚአብሔርን ቁመና ለመፈጸም ሰባት የብቃት ማረጋገጫዎች አሉ። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ወደዚህ ብቃት እንድትደርስ ያስደረገባቸው፡ ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት አሉት። ይሄን ለማድረግ ሰባት መልእክተኞች ተጠቅሟል። ሰባት፣ ሰባት፣ ሰባት፣ ነገሮች ናቸው። አያችሁ? ሰባት ቁጥር—የእግዚ አብሄር የሙላት ቁጥር ነው፡ ሶስት ቁጥር ደግሞ የፍጽምና ቁጥር ናት። ስለዚህ ሶስት፡ እና ሰባት ሶስቶች አሉ። ስለዚህ፡ በሒሳብ ቀመር፡ እና በመንፈሳዊ፡ በእግዚአብሄር ቃል፡ በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ጨምሮ፡ የነገሩን ሙላት በአንድነት ጨርሶታል። እናጥናው።

417 ወደ ክርስቶስ ሙሉ ቁመና እንደርስ ዘንድ፡ ሁላችንም፡ በእግዚአብሄር ፍቅር፡ እና በእግዚአብሄር ፍርሃት፡ በልባችንም እርስ በእርሳችን ከልብ በመነጨ መከባበር፡ እንዳችን ለሌላው ጥልቅ ክብር ኖሮን፡ ወንድማዊ እና እህታዊ መዋደድ ጋር፡ የመንፈስ ቅዱስ ንጽሕና በቀር፡ ፈጽመን ክፉ ቃል ሳናወጣ፡ ተሳስረን በእምነታችን ላይ እንጨምር። አይታችኋል? አብራችሁ ኑሩ። ክርስቲያን ሁኑ። በእምነት ተጓዙ። ስሕተት እና እውነትን ለመለየት፡ የእግዚአብሄር ጸጋ፡ እና የእግዚአብሄር እውቀት በመካከላችሁ ይፍሰስ። ዲያቢሎስ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ነገር ያልሆነ ነገር ሲያመጣ፡ ከዛ ሽሹ። ትክክል ነው።

418 ዋናዎቹ ሐዋርያት ውደዱን የሚል ባህርይ እንዳልነበረባቸው እሰባለሁ። መድረኩ ላይ እስኪደርሱ ድረስ፡ ብዙ ቃላት ሳይናገሩ፡ የሚመላለሱ ናቸው። ገብተው ማድረግ ያለባቸውን ካደረጉ በኋላ፡ ይወጣሉ። አዎን፡ ጌታዬ። ስልጣን ነበራቸው። በጎነት ነበራቸው። ከሰው ጋር ጥል አልነበራቸውም። የቆሙበትን ያውቃሉ። በቃ። ያመኑትን ያውቃሉ። በመንፈስ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ስራቸውን እየሰሩ...

419 ባለፈው ምሽት እንዳልኩት። እግዚአብሄር፡ ጭንቅላቱን በዋንታ መነቅነቅ ብቻ፡ ከዛ በኋላ የሚያቆማቸው ነገር የለም። አያጠኑም ወይም አይጠይቁም፡ እንደ እኛ አይጨነቁም፡ ወይም **ይሄን** ላድርግ **ያንን** ላድርግ ግራ-አይጋቡም። እንዲሁ ወጥተው፡ ይፈጽማሉ። እግዚአብሔር አንዴ ከነቀነቀላቸው፡ ወድያውኑ፡ ይጨርሳሉ። በምን ያውቃሉ? የእግዚአብሄር መነቅነቅ መሆኑ እንዴት ያውቃሉ? እዚህ የሚታዩት ጸጋዎች፡ እና ብቃቶች ሁሉ ሰላሏቸው ነው። ትንሿ እና መጀመርያዋ የእግዚአብሄር መነቅነቅ **ከእያንዳንዱ** ነገር ጋር፡ እና ከቃል ጋር ይመዝኗታል። የእግዚአብሄር ቃል መሆኑን ሰላወቁ፡ ይዘው ወጡ። ስለ ሌላው መጨነቅ አይጠበቅባቸውም። እግዚአብሄር ሲናገር፡ ወጡ። እኛ ግን...

420 እግዚአብሄር ሲናገረን፡ "እስቲ፡ እንጀምርና፡ ይሄን ህይወት መኖር የምንችል ከሆንን እናያለን።" እንላለን። ከሁሉ በፊት ማወቅ ያለባችሁ፡ አንድ ሰው ቢያናድዳችሁ። ዲያብሎስ እንደሆነ፡ መታወቅ፡ አለበት።

421 ዛሬ ማለዳ ከጉባኤ ሊያስቀረኝ ፈልጎ እንደሆነ መረዳት አለባችሁ። ይሄ ነገር አንዴም ቢሆን ሊኖራችሁ ያስፈልጋል። አቤቱ፡ ማረን! ጉባኤ ባልኩ ቁጥር ሁሌ ትግል እታገላለሁ። እየሞተ ላለ እና ላልዳነ፡ ህመምተኛ ሰው ለመጸለይ ስፈልግ፡ ከዚያ ሊያስቀረኝ ፈልጎ፡ በቻለው ፍጥነት፡ በአሰር ደቂቃ ውስጥ ሰላሳ ስልኮችን ያስደውላል። በእውነት። አዎን። ሊሞት የተቃረበ ነፍስ እያለ። "ወንድም ብራንሃም፡ ሆይ፡ **ይሄን** ማድረግ አለብህ።"

422 በቀደም ማታ፡ ወደ አንድ ቦታ ተጠራሁ። አንድ ወጣት ነው፡ ከዚህ በፊት ከጥቂት አመታት በፊት በ-ምን-ድነው-የምትሉት፡ በሱፐርማርኬት ውስጥ፡ አነጋግሬው ነበር። ወጣቱን ሰው እውቀዋለሁ፡ ሐጥያተኛ ነው። የአልኮል ሱሰኛ ሆኗል። እናቱ ሁለት ጊዜ ዶክተር ከጠራች በኋላ ይመስለኛል። ወደ እኔ ደወለች። እኔም... ሲደወል፡ ቢሊ ጋር ደውለው፡ መጨረሻ ላይ—መልእክቱ እኔ ጋር ደረሰ። መልእክቱ እኔ ጋር እንደደረሰ፡ ወጥቱ ጋር ለመሄድ፡ ሳልጨምር ሳልቀንስ ነው የምላችሁ፡ በህይወቴ እንዲህ አይነት ውግያ ደርሶብኝ አያውቅም።

423 እና እዚያ ሰደርስ፡ ምስኪኑ እኔን ያውቀኛል። ራሱን አያውቅም፡ ተኝቷል፡ ለመነሳት ይሞክራል። አባቱ ነካ ነካ አረገው፡ እና “ልጄ፡” አለው። ሰውየው ሐምሳ፡ ወደ ሐምሳ-አንድ አመት ይሆነዋል። “ጸጥ ብሎ ተኝቷል፡” እና “ልጄ፡” **ይሄው**፡ ብሎ በነገረው ጊዜ። ለመነሳት ሞከረ። **እነዚያን** ያረጁ ትልልቅ ክንዶቹ በዙርያው አቅፎ። እና ልጁ ምንም እስከማይቀረው ድረስ ሙሉ ለሙሉ ካንሰር ተበልቷል። ሁሉም የሰውነት ክፍሉ በካንሰር ተወሯል። የደም ማስተላለፊያው ሳይቀር፡ በሙሉ ካንሰር ነው። በዛ ሆኔታ ውስጥ ሆኖ፡ ለመነሳት እየሞከረ፡ እንደዚሁ ቀጠለ።

424 እጁን ያዝኩትና፡ “ዉድሮው፣ ዉድሮው፡ ወንድም ብራንሃም ነኝ፡” አልኩት።

425 አባቱም “ወንድም ቢልን፡ አላወቅከውም’ዴ? ዉድሮው፡ ወንድም ቢል’ኮ ነው።” አለው።

**እንዲህ** ብሎ፡ “ኧህ። አህ። ኧህ-አህ-አህ።” አለ።

426 አባቱም አይቶ፡ “ቢሊ፡ ትንሽ ዘግይተሃል፡” አለኝ።

እኔም፡ “በፍጹም አልረፈደም። እሱ እዚህ አለ።” እኔ ግን ውግያ ነበረብኝ አልኩት።

427 በዛም ሌሎቹ ወጣቶች፣ አንዳንድ ወጣት ወንዶች፡ ኃጢአተኞች፡ ዘመዶቹ እዚያ ቆመው ነበር። እና እንዲህ አልኳቸው፡ “እያችሁ፡ ወጣቶች፡ እናንተም ተራችሁን ጠብቁ፡ እናተም እንዲህ መሆናችሁ አይቀርም። እዚሁ ትመጣላችሁ። ተረድታችኋል? ምናልባት—በዚህ ካንሰር ላይሆን ይችላል። ምናልባት በጎዳናው፡ እስከሞት ድረስ፡ ደምታችሁ፡ ወይም በሌላ ምክንያት ይሆናል። መምጣታችሁ አይቀርም።” ብለን ገሰጽናቸው።

428 እስከዚያ የመንፈስ ምሪት እየተጠባበቅኩ ነበርኩ። ጠበቅኩት። በመጀመርያ ነገር፡ “እጅህን ጫንበት።” የምትል ትንሿን መነቅነቅ ሰማሁ።

429 ዞር ብዬ፡ ጠጋ አልኩና “ሁላችሁም አንገታችሁን ዝቅ አርጉ፡” አልኳቸው። ሁለት ወይም ሶስት ወጣቶች ነበሩ፡ ሁሉም አንገታቸውን ዝቅ አደረጉ።

430 እጆቹን በእሱ ላይ ጫንኩበት። እንዲህ አልኩ፦ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ልጁ ከዚህ ነገር ጋር ከመገናኘቱ በፊት፡ ማድረግ ያለበትን እንዲያውቅ ወደ ራሱ ይመለስ። እየሞተ ነውና። ዲያብሎስም ፈጽሞ አቊስሎታል፡ መሄዱ ነውና። እስከሞት ድረስ ጠጥቶ፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ደርሷል። አሁን ግን ምሕረትህ ይሁንለት” እጸልያለሁ አልኩ። ከጸለይኩለት በኋላ፡ በማግስቱ ጠዋት ነቅቶ ከአባቱ ጋር ቁጭ ብሎ፡ ማውራት ጀመረ።

431 እነ ባስቲ ሮጀርስ፡ የሆነ ጊዜ ነው… እዚህ፡ ሆስፒታሉ ድረስ ጠሩኝ። ጆርጂ ካርተር በተፈወሰችበት በሚሊታውን ከሰብኩ በኋላ፡ ያን ቀን እዚያው ነበርኩ። ሁላችሁም ታስታውሱታላችሁ። ያኔ የሜቶዲስት ሰባኪው፡ ወንድም ስሚዝ፡ እንዲህ ሲል፦ "ማናችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከተጠመቃችሁ፡ ማንም ሰው ከጉባኤዬ ይውጣ፡" እንደዛው አለ። ያንን ጉባኤ በማካሄድ፡ በቶተን ፎርድ ላይ ነበርን። አቤት፡ በቃ፡ አለ በሚባል ኩነኔ ሁሉ ኰነነኝ። የተጠራሁበት ሰላለኝ፡ ዝም አልኩት፡ ዝም ብዬ መንገዴን ቀተልኩ። ያኔ ጌታ ራእይ አሳየኝ። በበረሃ ውስጥ የሆነ ቦታ ላይ፡ የታገተ ጠቦት አሳየኝ። ሁላችሁም፡ ራእዩን ታስታውሱታላችሁ። ታስታውሳላችሁ ብዬ አስባለሁ። ታስታውሳላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡"አለ።—አርታዒ።] በእርግጠኛነት። እሺ። ከዚያም አደን ለማደን፡ ወደዚያ ምድረ በዳ እየሄድኩ ነበር።

432 ወደ ቶተን ፎርድ ሄድኩ። እዚያ ጋር ያለው ወንድም ራይት ያውቀዋል። እና ተሻገርን፡ ምን ማድረግ እንዳለብን አላወቅንም። በአንድ ሳንቲም፡ አንድ የሳሙና ሳጥን ገዛሁ። ወደዚያ ወጥቼ፣ ደረጃው ላይ ቆሜ ልሰብክ ነበር። አንዳንድ ነገሮች ለመነገድ ወደ ተራራው ጫፍ እየወጣሁ ነው አለ። እኔም አብሬው ሄድኩ። እዚያም በደረስን ጊዜ ባዶ የሆነ ትልቅ አሮጌ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ነበረ። ጌታም፡ "እዚህ ቁም" አለኝ።

433 "ወንድም ራይት፡ እዚህ ልጠብቅህ፡" አልኩትና። ቆምኩኝ። እርሱ ግን እላይ ደርሶ ተመለሰ።

434 ወደዚያ ጠጋ አልኩ፡ እና በሩን መክፈት አልቻልኩም። "ጌታ ሆይ፡ በዚህ ነገር ላይ አንተ ከሆንክ፡ ወደ ቤተክርስቲያኑ እንድገባ ከፈለግከኝ፡ በሩን ክፈትልኝ፡" አልኩት። እዚያ ተቀምጬ እያሰብኩ ትንሽ ቆየሁ።

435 አንድ ሰው እያዘገመ፡ ሲመጣ ሰማሁት፡ እንዲህ አለኝ፦ "ጤና ይስጥልኝ? ባልሳሳት፡" "ቤተ ክርስትያን መግባት ፈልገሃል? " አለኝ፤

"እዎን፡ ጌታዬ፡" አልኩት።

"ቁልፉ እኔ ይዣለሁ፡" አለኝ።

436 ጉባኤ ጀመርን። በአንደኛው ምሽት፡ ወንድም ራይት እና ቤተሰቡ፡ ሆነን ጉባኤ አደረግን፣ የመጀመርያው ሳምንት፡ ሰው አልነበረም። ታውቃላችሁ፡ በሳምንቱ መጨረሻ፡ በጓሮው ውስጥ እንኳን፡ ቦታ እስኪታጣ ድረስ ሆነ። አሁንም ያንን ጠቦት አልተገለጠም። አሁን እዚያ ያለው ፓስተር ወንድም ሆል፣ እና ሌሎች ሁሉ ያኔ የዳኑ ናቸው። ጠቦቱን ማግኘት አልቻልኩም። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ ከኮረብታው በታች ካለው፡ ከቸርች ኦፍ ክራይስት ሰንወርድ፡ ያቺ ዘጠኝ አመት ከሰምንት ወር ሙሉ ሳትንቀሳቀስ ተኝታ የኖረች ትንሽ ሴት። አገኘናት። ታሪኩን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ። አዎን፡ ይታወቃል።

437 ያን ቀን ከሰዓት ባስቲ ሮጀርስ፡ ባለ ወፍራም ድምጽ አርበኛ ቆሟል… እኔም ወደዚያ አመራሁ። በኢየሱስ ስም በማጥመቁ፡ በእኔ ላይ ለማፌዝ፡ ከወንድም ስሚዝ ጉባኤ ብዙዎች ተሰብሰቧል። ወደ ወራጅ ውሃ፡ ወደ ቶተን ፎርድ ድፍርስ ውሃ ወደነበረበት… [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]… ውስጥ ገባሁ፡ ወራጅ ውሃው የቻለውን ያህል ይጮሃል። ሁለት ዲያቆናት አብረውኝ ወጥተው ነበር።

438 “ዛሬ ከሰዓት እዚህ የቆምኩት የእግዚ አብሄርን ቅዱስ ቃል በመወከል ነው፡” ብዬ ተናገርኩ። እንዲህ አልኩ፦ “እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጴጥሮስ የተናገረው ክፍል አነባለሁ፡ ‘ንሰሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።’” ዘወር አልኩና፡ መጽሐፉን ከዲያቆናት ለአንዱ ሰጠሁት።

439 ወደዚያ ተንቀሳቀስኩና፡ “ከሐጥያቱ ንሰሐ የገባ፡ ማንም ቢኖር፡ መምጣት ይችላል፡” አልኳቸው። በውሃው ውስጥ እየተንቀሳቀስኩ። “መላእክቶች፡ በየቦታው ሆነው የሚታዘቡ ይመስለኛል፡” አልኳቸው። ኦህ፡ ማይ! ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ካጠመቅኩ በኋላ፡ ጉባኤው በሙሉ፡ ቆንጆ ሲልክ ቀሚስ የለበሱ ሴቶች፡ ውሃውን እየዘለሉ፡ በታላቅ ድምጽ እልል ማለት ጀመሩ። ጉባኤውን በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቅሁት። ታውቃላችሁ። ፎቶውን ሁሉ አንስቻለሁ። እዚያ ጋር ነበርና።

440 ምን ነበር? በጎነት ላይ መጨመር። አያችሁ? እናንተ ዝም በሉ። እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሰራ ያውቃል። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደሚፈጽማቸው ያውቃል። የፈለጉትን ይናገሩ። ምንም ለውጥ አያመጡም። ዝም ብላችሁ ቀጥሉ።

441 ባሰቲ ሮጀርስ እዚያ ቆሞ፡ ያንን ሲያይ፡ “እኔም በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡” አለ። እሰከነ ጥሩ ልብሱ፡ ወደ ውኃው ገባና፡ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቀ።

442 ከሦስት ወይም ከአራት ዓመታት በፊት፡ ወደ ኒው አልባኒ ሆስፒታል ደውለው ጠሩኝና። ካንሰር፡ እጅግ አጥቅቶት፡ ሞት አፋፍ ደርሶ፡ አገኘሁት። ዶክተሮች፡ እስከ ነገ ጠዋት ድረስ ብቻ በህይወት ትቆያለህ ብለውታል። እንዲህ አሉኝ፦ “አሁን እየሞተ ነው።” “ቶሎ ድረስ፡” አሉኝ።

443 ወደ ክፍሉ ገብቼ፡ ቆሜ ለመጸለይ፡ ወደ ውስጥ እንደገባሁ። እንዲህ አለኝ፦ “ቢሊ፡ እዛ ጥግ ላይ የሚሽከረከር ቀስተ ደመና እያለሁ አለኝ።”

444 እኔም ለማየት፡ ዞር አልኩ። “ባሰቲ፡ ቃል ኪዳን ነው። አንተ አትሞትም። የደሙ ቃል ኪዳን አድኖሃል፡” አልኩት።

445 እጆቼን በእሱ ላይ ጫንኩ እና እንዲህ አልኩ፦ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ እዚህ መሆንህን የሚያረጋግጥ ራእይ ነው። ቃል ኪዳንህም፡ ይህ ነው፦ ‘በእርሱ ቁሰል እኛ ተፈወስን።’” እጄን ጫንኩበት፡ ወድያውም ዳነ። ወደ ቤቱ ላክነው።

446 ከአምስት ወይም ከአራት አመት በኋላ፡ አራት ዓመታት ገደማ፡ ወንዙ ላይ ወደ-ታች- ወደ ላይ እያለ፡ ሲንቀሳቀስ ቆየ። እና ካንሰሩ ምግብ አስተላላፊው ቱቦ ላይ ስለነበረ፡ ትልቅ እና ጠንካራ ጠባሳ፡ ትቶበት ነበር። ዶክተሮቹ፡ የሆስፒታሉ አርበኞች፡ ያንን ሊዘረጋለት የሚችል የኮባልት ህክምና ማግኘት ትችላለ፡ ብዙ ምግብ በአንድ ጊዜ ማስተላለፍ ይችላል ብለውታል። ምግብ ላይ ከባድ ጊዜ አሰላፏል፡ አመጋገቡ እጅግ በቀስታ ነው። ለካ ሊታከመው ወርዷል። እኔ ይሄን አላውቅም እሱ ግን ገብቷል።

447 ቀዶ ጥገና ሲያደርጉለት፡ የጡንቻ መናድ እንደገጠመው አስተዋሉ፡ ስትሮክም ነበረበትና። አንደኛውን ጎኑ ሽባ አድርጎታል። ማድረግ የሚችለው

ብቸኛው ነገር ቀሰ-ብሎ መናገር ብቻ ነው። መጻፊያ እርሳስ **እንዲህ፡** ይዟል፡ እና "እህ፡ እህ፡ እህ፡" ይላል። **እንዲህ** እየተንቀጠቀጠ፡ በጤነኛው እጁ፡ ለመጻፍ ሞከረ። ግራው፡ በስትሮክ ተመቷል። በእጁም፦ "ኢየሱስ ያድናል፡ 1900 የመሳሰለ ነገር፡" ጻፈ። አልገባቸውም።

448 ስለዚህ ሚስቱም "ወንድም ብራንሃም፡ ምን ለማለት እንደፈለገ አላወቅኩም፡" አለችኝ።

449 እኔም፦ "ወይዘሮ/ ሮጀርስ፡ ማለቱማ፡ በ 1900 የሆነ ነገር፡ በኢየሱስ ሰም ተጠምቆ እንደዳነ። አሁንም እየመሰከረ ያለው ይህ ነው። ሞት አልፈራም እያለ ነው።"

450 "ጌታ አምላክ ሆይ፡ ህይወቱን ታደጋት። ህይወቱን እንድትታደጋት፡ በኢየሱስ ሰም፡ እጸልያለሁ፡" ብዬ ጸለይኩለት። እጆቼን ጫንኩበትና። ስትሮኩ ለቀቀው። የጡንቻው መናድ ቆመ። ከአልጋው ላይ ተነሳ። አሁንም ተነስቶ፡ ምስክርነቱን እየተናገረ ይገኛል።

451 በእምነታችሁ ላይ፡ በጎነትን፡ በበጎነታችሁም፡ እውቀትን፡ በእውቀታችሁ ላይ፡ ራስን መግዛት ጨምሩ፡ ራስን በመግዛት፡ ትዕግስትን፡ በትዕግስትም፡ እግዚአብሔርን መምሰል፡ እግዚአብሔርን በመምሰል፡ የወንድማማች መዋደድ፡ በወንድማማች መዋደድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ክርስቶስም ይመጣል። ምክንያቱ፡ ከእርሱ በታች... እነዚያን ጸጋዎች ለማጉላት ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ መንፈስ ቅዱስ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ነው። ኦህ፡ ማይ!

አሁን፡ አስራ ሁለት ከሩብ ሆኗል።

> እወደዋለሁ... እወደዋለሁ
> ቀድሞ ወዶኛልና

**እዚህ** ጋር፡ ገና ምንም የሌለን ሳለን።

> ገዛ... (ምን አደረገ? )... መዳኔን ገዛ
> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

እንዴት **እንዲህ** ሆንኩ? አስቀድሞ፡ ስለወደደኝ ነው።

> እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
> ቀድሞ ወዶኛልና (ምክንያቱ አለ)
> መዳኔንም ገዛሁ
> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

452 ዛሬ ጠዋት፡ በፍጹም ልቤ፡ ቃል እገባለታለሁ፣ ይህም፡ በጸጋው እና በረድኤቱ፡ ዘወትር ያለማቋረጥ፡ እነዚህ መሰፈርቶች ሁሉ፡ በትንሻ አሮጌ ቁመናዬ ውስጥ እንደሚፈስሱ እስኪሰማኝ ድረስ፡ የሕያው ክርስቶስ መገለጫ እስክሆን ድረስ ሳላቋርጥ እፈልጋለሁ። እነሆ፡ እኔ በእርሱ፡ የእግዚአብሄር ጽድቅ እሆን ዘንድ... እርሱ፡ በእኔ ቦታ ሐጥያት ሆኗልና። እሱ የሞተለት አላማ ይህ ነውና። "ጌታ ሆይ፡ እሱ በእኔ ፋንታ እንደሆነ፡ እኔም በእሱ ፋንታ ልሁንለት።" በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ስንቶች ይሄን ቃል ትገባላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አሁን አንገታችንን ደፍተን፣ እጆቻችንም ወደ ላይ።

> እኔ...

453 ጌታ ሆይ፡ ቃል ገብቻለሁ፡ ይህች ቤተ ክርስቲያንም ቃል ገብታለች፡ “የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ቁመና!”

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮው ዛፍ ስር

**የፍጹም ሰው ቁመና** AMH62-1014M

(The Stature Of A Perfect Man)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ጠዋት፡ ጥቅምት 14፡ 1962፡ በዩ/ኤስ/ኤ/ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ከሚገኘው፡ብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።


ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡


VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org